# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

## የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በንግድ ሚኒስቴር መ/ቤት የገቢና ወጪ ዕቃዎች እና የህጋዊ ሥነ-ልክ ደረጃዎች ፍተሻ አፈፃፀምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት/2008

አዲስ አበባ

ማውጫ ገጽ


መግቢያ.......................................................................................................1

የንግድ ሚኒስቴር ዓላማ .................................................................................1

የንግድ ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር....................................................................2

የንግድ ሚኒስቴር ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ሀይል ..............................................3

ድርጅታዊ መዋቅር.........................................................................................3

የሰው ኃይል..................................................................................................3

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ......................................................................4

አሰራር ሥርዓት መግለጫ /Process description/....................................................4

የኦዲቱ አላማ ...............................................................................................5

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ .........................................................................................5

ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው አከባቢ ...........................................................................6

የኦዲቱ ዋና ትኩረት አቅጣጫዎች .........................................................................6

የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች ..............................................................................7

ክፍል ሁለት ..................................................................................................8

የኦዲት ግኝቶች ...............................................................................................8

የገቢና ወጪ ዕቃዎች የደረጃ ፍተሻ እና የህጋዊ ስነ ልክ ስራዎች ደረጃ ፍተሻ ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ መሆኑን በተመለከተ፣.........................................................................................8

በገቢና ወጪ ዕቃዎች እና ህጋዊ ስነ ልክ ስራዎች ላይ እስትራቴጂክ ዕቅድና አመታዊ ዕቅድ ያዘጋጀና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣.........................................................................................8

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአሠራር መመሪያ አውጥቶ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ማሳወቁንና ተግባራዊ መደረጉን ያረጋገጠ መሆኑን በተመለከተ፣.......................................................................................11

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች በሰው ኃይል እንዲደራጁ በማድረግና ለሥራው የሚሆኑ መገልገያዎችን በማሟላት አፈጻጸማቸውን ክትትል እና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ፣ .......................................13

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ የገቢ ምርቶች ከአገር ከመውጣታቸው በፊትና ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው ገበያ ላይ ከመዋላቸው በፊት ደህንነታቸው እና ጥራታቸው የጠበቀ መሆኑን ማረጋገጡን በተመለከተ፣ ..............................

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተፈላጊውን የደረጃ መስፈርት የማያሟሉ የንግድ ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም ከሀገር እንዳይወጡ ያገደ መሆኑን፣ ከተዘጋጀላቸው ደረጃ በታች ሆነው በተገኙት ላይ እርምጃ መውሰዱን በተመለከተ..........21

የደንበኞችን የላብራቶሪ የፍተሻ ውጤት መገለጽ ባለበት ጊዜና ሰዓት ማሳወቁንና ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን፣ ናሙናዎች ከተወሰዱበት ሰዓት ጀምሮ በ48 ሰዓት ላብራቶሪ እንዲቀርቡ ማድረጉን በተመለከተ፣...........................................25

ምርትን ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገቡ አስመጪዎች አለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው የላብራቶሪ ሰርተፊኬት እንዲያቀርቡ ማድረጉንና፣ የሦስተኛ ወገን ሰርተፊኬት ያላቀረቡ አስመጪዎች የላብረቶሪ ውጤት እስከሚገለጽ ድረስ በጉምሩክ እንዲጠብቁ ማድረጉን በተመለከተ፣.........................................................................................27

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሀገሪቱን የስነ ልክ ሥርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን ቁጥጥር ማድረጉን፣ የመለኪያ መሣሪያዎች በክልል ንግድ ቢሮዎችና በፌዴራል ተጠናከረው መሥራታቸውን የሚያረጋግጥ መሆኑን በተመለከተ፣ ........ 29

የመለኪያ መሣሪያዎች ወደ ገበያ ከመግባታቸው በፊት ደረጃቸውን የጠበቁ መሆኑን ማረጋገጡን በተመለከተ፣ ........ 32

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተገልጋዮች ቬሪፊኬሽን ለማስደረግ የክብደት ማነፃፀሪያዎች ወስደው እንዳያዘገዩ ውል በማስገባት መሣሪያዎቹ በወቅቱ እንዲመልሱ ማድረጉን በተመለከተ፣ ........ 33

የአውቶ ቡቴ የቬሪፊኬሽን የአገልግሎት ክፍያ ተመን ከሚሰጠው አገልግሎት አንጻር መሆኑን፣ የፈሳሽ ማጓጓዣ ታንከር( ቦቴ) የቬርፊኬሽን ሰርተፊኬት የሚሰጥና ተግባራዊ መደረጉን ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ፣ ........ 35

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላትስ ጋር ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር እና ቀልጣፋ የሆነ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፣ ........ 37

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልሎች፣ ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና ከተገልጋዮች ጋር ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር ያለው መሆኑን በተመለከተ፣ ........ 37

ከተገልጋዮች የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት በየ6 ወሩ ቋሚ የምክክር መድረኮች ያዘጋጀ መሆኑን፣ ከክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች ባለሙያዎች ጋር በየሩብ ዓመቱ ውይይት ማድረጉንና በየስድስት ወሩ ግምገማ ማካሄዱን በተመለከተ፣ ........ 40

ከላብራቶሪ ፍተሻ ውጤት ጋር በተያያዘ ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር ውይይት ያደረገና መፍትሄ ያስቀመጠ መሆኑን በተመለከተ፣ ........ 42

ናሙናዎች መረጃ በመረጃ ቋት ተመዝግቦ እንዲያዝ መደረጉን፣ ወቅቱን የጠበቀ መረጃ ለቅ/ጽ/ቤቶችና ለተገልጋዮች እንዲሰራጭ ማድረጉንና ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር መረጃ የሚለዋወጥና መሆኑን በተመለከተ፣ ........ 44

ሁሉንም የሥራ አመራር ያካተተ መደበኛ እና ተከታታይ የማናጅመንት የውይይት መድረክ ያለው መሆኑን በተመለከተ፣ .. 46

በክልል የሚካሄደውን የሕጋዊ ሥነ ልክ አተገባበር ገምግሞ ድጋፍ የሚያደርግ መሆኑን፣ በቅ/ጽ/ቤቶችና በክልሎች በአካል በመገኘት የጋጠሙ ችግሮችን ገምግሞ መፍትሄ የሰጠ መሆኑ በተመለከተ፣ ........ 47

የቅርንጫፍ ጽ//ቤቶች የሚያቀርቡትን ወርሀዊ፣ ሩብ ዓመት፣ ግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርታቸውን ከገመገመ በኋላ ግብረ መልስ የሰጠ መሆኑን በተመለከተ፣ ........ 49

ክፍልሦስት ........ 51

የመደምደሚያ ሃሳቦች ........ 51

ክፍል አራት........ 55

የማሻሻያ ሀሳቦች ........ 55

39. አባሪ 1 መመዘኛ መስፈርት........ i
40. አባሪ 2 ደረጃቸውን ሳያሟሉ የተለቀቁ ዕቃዎች........ ii
41. አባሪ 3ኛ ወገን ሠርተፊኬት ሳያመጡ የተለቀቁ........ iii
42 አባሪ 4 በተጭበረበረ ሠርተፊኬት ሲሰሩ ቢገኙም እርምጃ ያልተወሰደባቸው........ iv

## መግቢያ

1. ቀድሞ የንግድ፣ ኢንዱስትሪና ቱሪዝም ሚኒስቴር በመባል ይታወቅ የነበረው መ/ቤት የአገር ውስጥ ንግድ ሚኒስቴር፣ የውጭ ንግድ ሚኒስቴር፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴርና የቱሪዝም በሚል በ4 መ/ቤቶች ተከፋፍሎ እንዲዋቀር ተደርጎ ነበር፡፡

2. ከዚያም የአገር ውስጥ ንግድ ሚኒስቴር እና የውጭ ንግድ ሚኒስቴር እንደገና በ1983ዓ.ም የንግድ ሚኒስቴር በሚል ስያሜ እንዲዋሃዱ የተደረገ ሲሆን፤በ1987 ዓ.ም ደግሞ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጋር በአዋጅ ቁጥር 4/1987 ዓ.ም በማዋሃድ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እንዲደራጅ ተደረጓል፡፡ ይህ መ/ቤት በ1994 ዓ.ም 10 ተጠሪ መቤቶችን በስሩ ይዞ እንዲያስተባብር እና እንዲመራ በአዋጅ ቁጥር 256/1994 ተደራጅቶ ነበር ከዚያም እንደገና በአዋጅ ቁጥር 411/1996 የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በስሩ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ፣ የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጠሪ ኤጀንሲ፣ የኢትዮጵያ ጥራትና ደረጃዎች ባለስልጣን፣የፌደራል ጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ስራዎች ኤጀንሲና የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ለእርሱ ተጠሪ ሆነው እንዲደራጁ ተደርጓል፡፡

3. በአሁኑ ወቅትም የቀጣዮቹን አምስት አመታት መሰረታዊ የዕቅድ አላማዎች፣ የማክሮ ኢኮኖሚ እና የዋና ዋና ዘርፎች ግቦችን፣ የአቅም ግንባታና የመልካም አስተዳደር ተግባሮችን እውን ለማድረግ የፌደራል አስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ 691/2003 የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በሚል ስያሜ በጋራ ሲሰሩ የነበሩ የስራ ዘርፎች በሁለት ሚኒስቴር መቤቶች በተናጥል እንዲደራጁ ተደርጎ የንግድ ሚኒስቴር ተቋቁሟል፡፡ በወቅቱም ራሱን ችሎ በሚኒስቴር ደረጃ እንዲደራጅ የተደረገው ቀደም ሲል በግብርናና በገጠር ልማት ሚኒስቴር፣ በኢትዮጵያ ጥራትና ደረጃዎች ባለስልጣን እና በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሲከናወኑ የነበሩ እና ከንግድ ጋር የተያያዙ ተግባራት ወደ አንድ በማምጣት ቀደም ሲል ለሌሎች ተቋማት ተጠሪ የነበሩት የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት፣ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን፣ የኢትዮጵያ ምርት ገበያንና የንግድ አሰራር ሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን ለሚኒስቴር መስርያ ቤቱ ተጠሪ እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡

## የንግድ ሚኒስቴር ዓላማ

4. የንግድ ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 691/2003መሰረት የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት፡፡
   - ግልጽነትን፣ ተደራሽነትንና ውድድርን መሠረት ያደረገ ሸማቹን፣ የንግዱን ማህበረሰብና አምራቹን ያረካ የተረጋጋ ገበያና ፍትሐዊ የንግድ ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ፣

- ሀገሪቱን ከዓለም አቀፍ የንግድ ሥርዓት ተጠቃሚና ተዋናይ በማድረግ የውጭ ምንዛሪ ገቢያችንን ማሳደግ፣
- የሚኒስትር መ/ቤቱን ተልዕኮ ለማሳካት በሚያስችል ደረጃ የማስፈፀም አቅምን ማጐልበት፣

**የንግድ ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር**

5. **ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 961/2003 የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ተሰጥቶታል:-**
   - የሀገር ውስጥ ንግድ እንዲስፋፋና ህጋዊ የንግድ አሠራር እንዲሰፍን ተገቢነት ያላቸውን እርምጃዎች ይወስዳል፣
   - የአገሪቱ የወጪ ንግድ የሚስፋፋበትንና የሚጠናከርበት ሁኔታ ያመቻቻል ለላኪዎች ድጋፍ ይሰጣል፣
   - የወጪና ገቢ እዕቃዎች በትክክለኛ ዋጋ ስለመሸጣቸው ወይም ስለመግዛታቸው ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ክትትል ያደርጋል፣ ዋጋ አሳንሰው በሚልኩ ወይም በሚያስመጡ ላይ በህግ አግባብ እርምጃ ይወስዳል፣
   - የወጪ ንግድ ግንኙነቶችን ይመሰርታል የንግድ ድርድሮችን ያስተባብራል ስምምነቶችን ይፈርማል፣ ያስፈጽማል፣
   - ፀረ ውድድር ተግባራትን ለመከለከል የሚያስችል የተሟላ ሥርዓት ይዘረጋል አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ በህግ አግባብ ለሸማቾች ጥበቃ ያደርጋል፣
   - አግባብ ካላቸው ህጐች መሠረት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎቶች ይሰጣል፣ የተሰጡ የንግድ ሥራ ፈቃዶች ለተሰጡበት ዓላማ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፣
   - የዋጋ ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚገቡ መሠረታዊ የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶችን ዋጋ እያጠና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀርባል ሲፈቀዱም ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፡፡
   - የሀገሪቱን ሕጋዊ ሥነ ልክ ሥርዓት ይዘረጋል፣ መተግበሩን ይቆጣጠራል፣ የሚመለከታቸው አስፈፃሚ አካላትን ያስተባብራል፣
   - የወጪና ገቢ ንግድ ዕቃዎችን ጥራት ይቆጣጠራል፣ ተፈላጊውን የደረጃ መስፈርት የማያሟሉ የንግድ ዕቃዎች ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም ከአገር እንዳይወጡ ያግዳል፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር በትብብር ይሠራል፣

- አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ያላቸው የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የደረጃውን መስፈርት ማሟላታቸውን ይቆጣጠራል፣ ከተዘጋጀላቸው ደረጃ በታች ሆነው በተገኙበት ላይ እርምጃ ይወስዳል፣
- በሌሎች አስፈፃሚ መ/ቤቶች የሚሠራባቸው አስገዳጅ ደረጃዎች በተቀናጀ መልኩ እንዲተገበር ያደርጋል፣ በአፈፃፀም ላይ የሚወያይ ጉባኤ ይጠራል መድረኩንም ይመራል፣
- የሀገሪቱን የንግድ መረጃዎች ያደራጃል ለሚመለከታቸው አካላት ያስራጫል፣
- የሸማቾችን ጨምሮ የህብረት ሥራ ማህበራት እና የንግድ የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች እንዲቋቋሙ ያበረታታል፣ የተቋቋሙትንም እንዲጠናከሩ ያደርጋል፣

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## የንግድ ሚኒስቴር ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ሀይል

### ድርጅታዊ መዋቅር

6. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአንድ ሚኒስትር እና በሁለት ሚኒስትር ዴኤታ የሚመራ ሲሆን በሁለት ዋና ዋና ዘርፎች የንግድ ማስፋፊያ ዘርፍ እና የንግድ አሰራርና ሬጉላቶሪ ዘርፍ ተደራጅቷል፡፡ ለንግድ ማስፋፊያ ዘርፍ ተጠሪ የሆኑት የቁም እንስሳት፣ የቆዳና ሌጦ ግብይት ዳይሬክቶሬት፣ የንግድ ግኑኙነትና ድርድር ዳይሬክቶሬት፣ የሰብል ምርት ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት፣ የግብርና ምርቶች ግብይት መረጃ ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት፣ ናቸው፡፡ የንግድ አሰራርና ሬጉላቶሪ ዘርፍ ተጠሪ የሆኑ ዳይሬክቶሬቶች የኢንስፔክሽንና ሬጉላቶሪ ዳይሬክቶሬት፣ የምዝገባና ፈቃድ ዳይሬክቶሬት፣ የወጪና ገቢ ዕቃዎች ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ተደራጅቷል፡፡

7. በድጋፍ ሰጪ ዳይሬክቶሬቶች ደግሞ የዕቅድና መረጃ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት፣ የህግ ዳይሬክቶሬት፣ የፋይናንስ አቅርቦት ዳይሬክቶሬት፣ የስርዓተ ፆታ ዳይሬክቶሬት፣ የኦዲት ዳይሬክቶሬት፣ የአሰራር ማሻሻያና የሰው ሀብት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት፣ የኢንፎርሜሽንና ቴክኖሎጂ ስራ አመራር ማዕከል፣ የህዝብ ግኑኙነት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አንድ ቅ/ጽ/ቤትና አራት ተጠሪ ተቋማት ማለትም የኢትዮጵያ ምርት ገበያ፣ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን፣ የኢትዮጵያ የእህል ንግድ ድርጅት፣ የንግድ አሰራርና ሸማቾች ጉዳይ ባለስልጣን በማካተት እንዲደራጅ ተደርጓል፡፡

### የሰው ኃይል

8. የንግድ ሚኒስቴር መ/ቤትና የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አደረጃጀትና መዋቅር መሠረት የተፈቀደው አጠቃላይ የሥራ መደብ ብዛት 927 ሲሆን እስከ ታህሳስ 30 2008 ዓ.ም ድረስ የተሸፈነ

የሥራ መደብ ብዛት 580 ( 63% በመቶ) ሲሆን፣ ክፍት የሥራ መደቦች ብዛት 347 (37%በመቶ) ነው፡፡ የሰራተኞች ፕሮፋይል በትምህርት ደረጃ ሲታይ በዶክተሬት ደረጃ 1 በ2ኛ ዲግሪ ደረጃ ያሉ 28(5%) በመጀመሪያ ዲግሪ 265 (46%) ዲፕሎማ 87 (15%) እንዲሁም ከዲፕሎማ በታች 199(34%) ናቸው፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ

9. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የገንዘብ ምንጭ ከመንግስት የሚመደበለት ለደመወዝ፣ ለሥራ ማስኬጃና ካፒታል በጀት ሲሆን በ2005፣ በ2006 እና በ2007 በጀት ዓመታት ለሚያከናውናቸው ተግባራት ማስፈጸሚያ እንደቅደም ተከተላቸው መደበኛ በጀት 53,264,063.80፣ 62,907,502.30 እና ብር 65.413.676.2 በድምሩ ብር 181.585.242 ሲሆን ከመንግሥት ፀድቆ ለሚተገብራቸው ተግባራት ማስፈፀሚያ ከተመደበለት በጀት ውስጥ እንደ ቅደም ተከተሉ ብር 35,612,932.20 ብር (66.8% ) 49,292,828.7 (78%) ብር 58.892.737.5 (90%) በድምሩ ብር 143.798.498 በስራ ላይ አውሏል፡፡ እንዲሁም ለካፒታል ስራ ማስኬጃ በ2005፣ 2006 እና 2007 እንደ ቅደም ተከተሉ የተመደበው 23,686,970፣ 31,645,832 እና 26561320 በድምሩ 81,894,122 የጸደቀለት ሲሆን ከዘሁ ውስጥ ከ2005 ጀምሮ በቅደም ተከተል ብር 14,966,724 (63% )፣ 19,495,174.2 (61%) እና 21597557.2(81%) በድምሩ ብር 56.059.455.40 ስራ ላይ አውሏል፡፡

## አሰራር ሥርዓት መግለጫ /Process description/

10. የገቢና ወጪ ዕቃዎች ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ዕቅድ ያቅዳል፣ የወጪ ምርቶች ከአገር ውስጥ ከመውጣታቸው በፊት ደህንነታቸው እና ጥራታቸው እንዲሁም የአገሪቱ ህግ በሚፈቅደው መሠረት የሚወጡ መሆኑን ያረጋግጣል፣ ገቢ ምርቶች ወደ ገበያ ከመግባታቸው በፊት በጉምሩክ ጣቢያዎች ደህንነታቸውና ጥራታቸው እንዲሁም ተገቢውን መስፈርት ያሚሉ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣ የቅድመ ጭነት ኢንስፔክሽን ያካሄዳል፣ የገቢ እና ወጪ ምርቶች የሀገሪቱን ህግና ደንብ ተከትለው መግባታቸውን ወይም መላካቸውን በማረጋገጥ ይሁንታ ይሰጣል፣

11. የሕጋዊ ሜትሮሎጂ አዋጅ/ደንብ የሚመለከታቸውን በግብይት ውስጥ የሚገኙትን የመለኪያ መሳሪያዎችና የቅድመ እሽጋ ትክክለኛነት ያረጋግጣል፣ የመለኪያ መሣሪያዎችን ዲዛይንና ፓተርን ትክክለኛነት ያረጋግጣል፣ የሚወሰኑ ውሳኔዎች አፈጻጸማቸውን በቅርብ ይከታተላል፣ ከግምገማው ውጤት በመነሳት በአሠራር ላይ ወይም በአፈጻጸም ላይ ችግር ያለባቸውን

ህጉችና ደንቦች እንዲሻሻሉ ያስደርጋል፣ በገቢና ወጪ ምርቶች ክትትል የአፈጻጸም ግምገማና ግብረ መልስ በመገምገም ተቋሙ የሚጠበቅበትን ውጤት በግብረ መልስ ይሰጣል፡፡

12. የገቢና ወጪ ዕቃዎች ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት በስሩ ሁለት ቡድኖች የሚገኙ ሲሆን፣ የገቢና የወጪ ዕቃዎች ጥራት ቁጥጥር ቡድን እና የህጋዊ ስነ ልክ ቡድን ናቸው፡፡

13. የገቢና ወጪ ዕቃዎች ቁጥጥር ቡድን ፡- የገቢና ወጪ ዕቃዎች ጥራት ቁጥጥር የደንበኞች ጥያቄ ይቀበላል፣ የደንበኞች የኢንስፔክሽን ጥያቄ በአስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ወሰን ውስጥ መሆኑን ያረጋግጣል፣ ተቀባይነት ያላገኘውን የአገልግሎት ጥያቄዎች ለደንበኛ ያሳውቃል፣ ተቀባይነት ያገኘውን አገልግሎት ጥያቂ በደንቡ መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ያስከፍላል፣ በደረጃው መሰረት ተገቢውን የኢንስፔክሽን ስራ በማከናወን እንደአስፈላጊነቱ ናሙና ይወስዳል፣ በላብራቶሪ ፍተሻ ውጤት የጥራት ደረጃቸውን ማረጋገጥ የሚገባቸውን ያስፈትሻቸዋል፣ የላብራቶሪ ውጤት መቀበልና ከተገቢው መስፈርት ጋር ያነጻጽራል፣

14. ሪፖርት ያዘጋጃል ሪፖርቱ በተቀመጠው ቅደም ተከተልና መመሪያዎች መሰረት አድርጎ መሰራቱን ያረጋግጣል፣ የፊዚካልና የላብራቶሪ ፍተሻ መሰረት የተፈላጊውን ደረጃ መስፈርት ያላሟሉ ምርቶች ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ያግዳል፣ በፊዚካልና ለብራቶሪ መስፈርት ያሟሉ ምርቶች ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ ፈቃድ/ይሁንታ/ ይሰጥቸዋል፣ መስፈርት የማያሟሉ ምርቶች እገዳ ይጣልባቸዋል ሆኖም ደንበኛው በሚያቀርበው ጥያቄ መሰረት ድጋሚ የኢንስፔክሽን ስራዎች ያከናውናል፡፡

## የኦዲቱ አላማ

15. የኦዲቱ ዓላማ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የገቢና ወጪ ዕቃዎችና የህጋዊ ስነ ልክ ስራዎች የደረጃዎች ፍተሻ ቀልጣፋ እና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ስርአት መዘርጋቱን እንዲሁም ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን በመገምገም አፈፃፀሙ አጥጋቢ ሆኖ ካልተገኘ ያልሆነባቸውን ምክንያቶች ለይቶ በማውጣት የማሻሻያ ሃሳብ ለማቅረብና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

16. ኦዲቱ የተከናወነው በንግድ ሚኒስቴር መ/ቤት ሲሆን ከአዲስ አበባ ቅ/ጽ ቤት፣ ከኮሜት ተወካይ ጽ/ቤት፣ ሞጆ ተወካይ/ጽ/ቤት፣ አዳማ ቅ/ጽ/ቤት/ሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት፣ ሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት፣ አዲስ አበባ ቃሊቲ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት፣ ሞጆ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት፣ አዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት፣ ሞያሌ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት፣ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት ዋና መ/ቤት፣ አዳማ ቅ/ጽ/ቤት ተስማሚነት ምዘና ድርጅት፣ ሃዋሳ ቅ/ጽ/ቤት

ተስማሚነት ምዘና ድርጅት፣ አዲስ አበባ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ፣ ኦሮሚያ ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ እና ሀዋሳ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ጋር የኦዲት ቡድኑ ቃለ መጠይቅ በማድረግና በአካል ተገኝቶ ምልከታ በማድረግ ከገቢና ወጪ ዕቃዎችና ከህጋዊ ስነ ልክ ደረጃዎች ፍተሻ ጋር በተያያዘ አግባብነት ያላቸው ዶክመንቶች በመከለስ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ ኦዲቱ የሸፈነው ሦስት የበጀት ዓመታትን ማለትም ከ2005 እስከ 2007 ዓ.ም ባለው ጊዜ የገቢና ወጪ ዕቃዎችና የህጋዊ ስነ ልክ ስራዎችን በተመለከተ የተከናወኑ ስራዎችን ነው፡፡

## ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው አከባቢ

17. ከላይ የተመለከቱትን የኦዲት ዘዴዎች በመጠቀም የተሰበሰቡ መረጃዎችና ማስረጃዎችን መሰረት በማድረግ ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ የገቢና ወጪ ዕቃዎች የደረጃ ፍተሻ አፈጻጸም እና የህጋዊ ስነልክ ደረጃዎች ፍተሻ አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፣

## የኦዲቱ ዋና ትኩረት አቅጣጫዎች

18. ከላይ በተገለፀው የኦዲት አካባቢ ሥር ሁለት ዋና የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች የተለዩ ሲሆን በሁለቱ የትኩረት አቅጣጫዎች ሥር አራት ንዑስ የትኩረት አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል፡፡ እነሱም፣

   1. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የገቢና ወጪ ዕቃዎች እና የመለኪያ መሣሪያዎች ደረጃ ፍተሻ አፈጻጸምን ኢኮኖሚያዊ ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ የሚከናወን መሆኑን መገምገም፣፡

      1.1 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የገቢና ወጪ ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ ሲገቡና ሲወጡ ቀልጣፋና ውጤታማ የደረጃ ፍተሻ ማድረግ የሚያስችል፣ የክትትል እና ቁጥጥር ስርዓት እንዲዘረጋና ተግባራዊ እንዲሆን ያደረገ መሆኑን መገምገም

      1.2 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ህጋዊ የመለኪያ መሣሪያዎች ወደ ሀገር ሲገቡ የደረጃ ፍተሻ የሚደረግላቸው እና ስራ ላይ ሲውሉ ደረጃቸውን ጠብቀው እየሠሩ ስለመሆኑ ማረጋገጥ የሚያስችል የክትትል እና ቁጥጥር ስርአት እንዲዘረጋና ተግባራዊ እንዲሆን ያደረገ መሆኑን መገምገም፣

   2. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የገቢና ወጪ ዕቃዎች እና የህጋዊ ስነ ልክ ደረጃዎች ፍተሻ በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር እና ቀልጣፋ የሆነ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም፡

2.1 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልሎች፣ ከቅ/ጽ/ቤቶች፣ እና ከተገልጋዮች ጋር ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ በትብብር ለመስራት የሚያስችል የቅንጅታዊ አሰራር ስርአት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፣

2.2 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ቀልጣፋ የመረጃ አያያዝ፣ ልውውጥ እና ግብረ መልስ አሰጣጥ ሥርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ የሚሉ ናቸው፡፡

የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች

19. በኦዲት ቡድኑ ለተመረጡት ሁለት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች እና አራት የኦዲት ንዑስ ትኩረት አቅጣጫዎችን ለመመዘን የሚረዱ (36) የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶችን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት የንግድ ሚኒስቴር ማቋቋሚያ አዋጅ፣ የተለያዩ የአሰራር ማንዋሎች፣ BSC ዕቅድ ፣ የመግባቢያ ሰነድ እና መልካም ተሞክሮዎች ናቸው፡፡ በተዘጋጁት የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ላይ የንግድ ሚኒስቴር የስራ ኃላፊዎች አስተያየት ሰጥተውበታል፡፡መመዘኛ መስፈርቱ ከዚህ ሪፖርት በአባሪ 1 ተያይዟል፡፡

# ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

1. **የገቢና ወጪ ዕቃዎች የደረጃ ፍተሻ እና የህጋዊ ስነ ልክ ስራዎች ደረጃ ፍተሻ ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ መሆኑን በተመለከተ፣**

**በገቢና ወጪ ዕቃዎች እና ህጋዊ ስነ ልክ ስራዎች ላይ እስትራቴጂክ ዕቅድና አመታዊ ዕቅድ ያዘጋጀና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣**

20. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የገቢና ወጪ ዕቃዎች እና የህጋዊ ስነ ልክ ስራዎች ደረጃ ፍተሻ ላይ የሚመለከታቸውን የክልልና የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በማሳተፍ እስትራቴጂክ ዕቅድ ሊያዘጋጅና ስትራቴጂክ ዕቅዱን መሰረት አድረጎ አመታዊ ዕቅድ ሊያዘጋጅ፣ ዕቅዱን በየደረጃው ማለትም በሚ/ር መ/ቤቱ፣ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች፣ በክልሎች ተግባራዊ እንዲሆን ድጋፍ በማድረግ በየደረጃው የሚገኙ አካላትም የእቅድ ክንውን ሪፖርት ሊያቀርቡና በዕቅድ ክንውን ላይ ለሚታዩ ክፍተቶች በመለየት አፋጣኝ የመፍትሄ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

21. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በህጋዊ የስነ-ልክ የሚዛን ልኬት ትክክለኛነት ማረጋገጫ አሠራር ማኑዋል ላይ የሥነ-ልክ ቡድን የትክክለኛነት ማረጋገጫ ሥራ ዓመታዊ ምርመራ እና ድንገተኛ ፍተሻ ሥራ መሠራት እንዳለበት ቢገለጽም በዕቅድ አካቶ የማይሰራ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የህጋዊ ሥነ ልክ ስራዎችን በተመለከተ በግብይት ላይ የሚውሉ የመለኪያ መሣሪያዎችን የመቆጣጠር ተግባር የሚኒስቴር መ/ቤቱ ቢሆንም ሥራው በተሻለና ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲከናወን ለክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች ውክልና የሰጠ ቢሆንም በክልሎች የሚካሄዱ የስነ ልክ ስራዎች የመከታተል የመደገፍ ስራ መስራት ያለበት ሲሆን የስነ ልክ ስራዎችን በእስትራቴጅክ ዕቅድ በማካተት ወደ ክልል በማውረድ ለክልሎች እንዲያውቁት አልተደረገም፡፡

22. ክልሎችም የሥነ ልክ ሥራዎችን በተመለከተ ዕቅድ አቅደው የዕቅድ ክንውን ሪፖርታቸውን በየሶስት ወሩ ውክልናው ከተሰጠበት ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ እንዲልኩ ቢገልጽም በኦዲቱ በናሙና በታዩ የክልል ንግድ ቢሮዎች የአዲስ አበባ ፣ የደቡብ ክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ እና የኦሮሚያ ንግድ ገበያ ልማት ቢሮ ውስጥ የኦሮሚያ ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ ብቻ በየ3 ወሩ የሥነ ልክ ሥራዎችን በተመለከተ ዕቅድና የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ከ2005-2008 ህዳር መጨረሻ ድረስ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚልክ ሲሆን የአዲስ አበባና የደቡብ ክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች ዕቅድና አፈጻጸማቸውን

እንደማይልኩ  ለክልል ንግድ ቢሮች እና ሚኒስቴር መ/ቤት የሥራ ኃላፊቻች በቀረበ ቃለ መጠይቅ እና ቢሮው ከላከው የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ  ለማወቅ ተችሏል፡፡

23. እንዲሁም በገቢና ወጪ ዕቃዎች እና በህጋዊ መለኪያ መሳሪያዎች ደረጃ ፍተሻ አፈጻጸም ዕቅድ ክንውን ላይ  የሚታዩ ክፍተቶች ማለትም ሥራው የሚፈለገውን ያህል  እስከ ወረዳ ድረስ ወርዶ መሥራት አለመቻልና በቂ የመለኪያ መሣሪያዎች አለመኖር እንደ ችግር ታይቶ የመፍትሄ እርምጃ እየወሰደ አለመሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

24. የኦዲቱ ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ በናሙና ተመርጠው በታዩት የክልል ንግድ ቢሮ ኃላፊዎች ለቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ዕቅድና የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት የማያቀርቡበት ምክንያት የሶስት ወር እና የስድስት ወር ሪፖርት እንዲቀርብ በሚኒስቴር መ/ቤቱ  ያልተጠየቀ መሆኑና እንዲሁም የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ የስራ ሂደቱ ከሚ/ር መ/ቤቱ ጋር ቀጥተኛ የስራ ግኑኝነት  የሌለውና ራሱን የቻለ መነሻ ዕቅድ  ተዘጋጅቶ ከላይ ወደታች ያልወረደ በመሆኑ  ዕቅድና የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት የማይልኩ መሆኑን ለኦዲት ቡድኑ ገልጸዋል፡፡

25. በገቢና ወጪ ዕቃዎች ደረጃ ፍተሻ አፈጻጸምን በተመለከተ በኦዲቱ ወቅት በሙና ተመርጠው የታዩ የአዲስ አበባ፣ ኮሜት፣ አዳማ፣ ሞጆ፣ ሀዋሳና ሞያሌ  ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ዕቅድ በማቀድ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚልኩ ቢሆንም ሚ/ር መ/ቤቱ የነዚህን የተጠቀሱ ቦታች በአፈፃፀም ያጋጠሟቸውን ችግሮች ለመፍታት አፋጣኝ የመፍትሄ እርምጃ እየወሰደ ባለመሆኑ የታዩ ክፍተቶች በወቅቱ እየተቀረፉ አለመሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

26. በገቢና ወጪ ዕቃዎች ደረጃ ፍተሻ አፈጻጸም  በዕቅድ ክንውን ላይ  የሚታዩ ክፍተቶችን በተመለከተ የኦዲት ቡድኑ ቃለ መጠይቅ ያደረገላቸው አዲስ አበባ፣ ቃሊቲ ኮሜት ተወካይ፣ አዳማ፣ ሞጆ፣ አዋሣ እና ሞያሌ ቅርንጫፍ የሥራ ኃላፊዎች ወርሀዊ፣ የሶስት ወር፣ የስድስት ወር፣ ዓመታዊ  እና አንድ ለአምስት ሪፖርት ለሚ/ር መ/ቤቱ ቢልኩም ነገር ግን  በአሠራር ላይ የጋጠማቸውን ክፍተቶች ማለትም /የመገልገያ መሣሪያዎች ችግር፣ የተሽከርካሪ አለመኖር ችግር፣ ለሥራ ብቁ የሆነ ሰው ኃይል መድቦ ያለማሠራት ችግር፣ ፒቲ ካሽ በወቅቱ አለመለቀቅና ማነስ ችግር፣ ለጥያቄዎች አፋጣኝ መልስ አለማግኘት፣ የላብላቶሪ መዘግየት ችግር፣ በሥራ ላይ ለሚታዩ ችግሮች በመለየት የመፍትሄ እርምጃ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በወቅቱ እየወሰደ አለመሆኑን የቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡

27. ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ከሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ  የስራ ኃላፊዎች ጋር ባደረገው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ድንገተኛ ፍተሻ እና

አመታዊ ምርመራ ስራ በእስትራቴጂክ ዕቅዱ አካቶ የማያቅድና ለክልሎች ውክልና የተሰጠ በመሆኑ ድጋፍ የማድረግ ስራ ብቻ የሚሰራው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

28. እንዲሁም ክልሎች አመታዊ ምርመራ ማድረግ ስራቸው መሆኑንና ሚኒስቴር መ/ቤቱ እንዳትመጡብን ብለዋል በማለት አስረድተዋል፡፡ እንዲሁም መ/ቤቱ የህጋዊ ስነ ልክ ስራዎች በእስትራቴጂክ ዕቅዱ አካቶ ለክልሎች በማውረድ ክልሎችም ከዕቅዱ ተነስተው የራሰቸውን ዕቅድ በማቀድ የአፈጻጸም ሪፖርት የማያቀርቡ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

29. ይህም የሆነበት አንደኛው ሁሉም ክልሎች የተለያየ አደረጃጀት ያላቸው በመሆኑና ሁሉም ክልሎች ጋር ያሉ የመለኪያ መሳሪያዎች አንድ አይነት አለመሆንና መዋቅር የሌላቸው ክልሎች በመኖራቸው ዕቅድ አቅደው የአፈጻጸም ሪፖርታቸውን በየሶስት ወሩ እንዲያቀርቡ መመሪያ የተላለፈ ቢሆንም ዕቅዳቸውና አፈጻጸማቸውን የማይልኩ መሆኑ፣ ዕቅድና የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ላኩ ሲባሉ ሚኒስቴር መ/ቤቱን እንደ ጣልቃ ገብነት በመቁጠር በስራችን እንዳትገቡ በማለት የማይልኩ መሆኑ፣ ለምሳሌ አማራ ክልል፡፡ ክልሎች የዕቅድ አፈጻጸማቸውን በተገለጸው ጊዜ ባለመላካቸው ተገቢው የእርምት እርምጃ አልተወሰደም፡፡ ምክንያቱም የግብዓትና የአደረጃጀት ችግር በመኖሩ፣ በአሁኑ ጊዜ ከክልሎች ጋር በየስድስት ወሩ አንድ ጊዜ ውይይት በማድረግ ግምገማ እየተሰራ የሚገኝ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

30. እንዲሁም በዕቅድ ክንውን የሚያገጥሙ ችግሮችን ለመፍታት ናሙና ለመውሰድ የተሸከርካሪ ችግር መኖሩ፣ ሁልጊዜ ጥያቄው የሚቀርብ ችግሩ በተደጋገሚ ተጠይቆ ሊፈታ አለመቻሉና የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ አመራርም የሚመለከተው አካል ጠይቆ ምላሽ ማግኘት ያልተቻለ መሆኑንና፣

31. ይህ በመሆኑ የደንበኛን ተሸከርካሪ መጠቀምና ናሙናዎች ከተወሰዱበት ሰዓት ጀምሮ በ48 ሰዓት ውስጥ ላብራቶሪ ማቅረብ አለመቻል፣ የፒቲ ካሽ አነስተኛ መሆንና ቶሎ አለመለቀቅ ችግር በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች የነበር ነገር ግን አሁን ችግሩ የተቀረፈበት ሁኔታ መኖሩን በመግለጽ የላብራቶሪ መዘግየት ችግርን በተመለከተ ችግሩ በፊት በጣም በከፍተኛ ሁኔታ የነበረ ነገር ግን አሁን ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር በመወያየት ችግሩን ለመቅረፍ ጥረት እየተደረገ የሚገኝ መሆኑ፣ ይህም ከሩቅ ቦታ የሚላኩ ናሙናዎች በአስቸኳይ እንዲሰሩ እየተደረገ የሚገኝና ችግሩ ሙሉ በሙሉ ባይሆንም በተወሰነ መልኩ ሊቀረፍ መቻሉን ገልጸዋል፡፡

32. ይሁን እንጂ ዓመታዊ ምርመራ እና ድንገተኛ ፍተሻ በማንዋሉ ላይ መሰራት እንዳለበት በተገለጸው መሰረት ባለመሰራቱ ክልሎችን የመደገፍ ስራ ነው ተብሎ በዕቅድ ተካቶ

የማይሰራ መሆኑ፣ ክልሎችም በተሰጣቸው ውክልና መሰረት ዕቅድና የዕቅድ የአፈጻጸም ሪፖርታቸው ውክልናው ሲሰጣቸው በየሶስት ወሩ እንዲልኩ በተቀመጠው መሠረት ባለመላካቸው ሚኒስቴር መ/ቤቱ እንደ ተቆጣጣሪነቱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር እንደማያደርግ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

33. በመሆኑም የህጋዊ ስነ ልክ ስራዎች ድንገተኛ ፍተሻ እና አመታዊ ምርመራ በዕቅድ ተካተው ተግባራዊ ባለመደረጉ ችግር ያለባቸው (ትክክለኛ ያልሆኑ) የመለኪያ መሳሪያዎች በገበያ ላይ በስፋት እንዲገኙ ማድረጉና፣ የህጋዊ ስነ ልክ ስራዎች በእስትራቴጂክ ዕቅዱ አካቶ ለክልሎች በማውረድ ተግባራዊ በማድረግ የአፈጻጸም ሪፖርታቸው በተቀመጠው ጊዜ እንዲያቀርቡ ባለመደረጉ በህጋዊ ስነ ልክ ስራዎች በሚፈለገው መልኩ አለመከናወኑና እንዲሁም በአፈጻጸም ላይ ለሚታዩ ክፍተቶች በመለየት የመፍትሄ እርምጃ ባለመውሰዱ የላብራቶሪ መዘግየት፣ የናሙና መቀየርና መሰባበር፣ በተገልጋዮች ላይ መጉላላትና ቅሬታ እንዲፈጠር አድርጓል፡፡ እንዲሁም የገቢና ወጪ ዕቃዎች ዕቅድ አፈፃፀም ወቅት በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ለሚያጋጥሙ ችግሮች ሚ/ር መ/ቤቱ ወቅታዊና አፋጣኝ መልስ አለመስጠቱ ከላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች እንዲከሰቱ አድርጓል፡፡

**ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአሠራር መመሪያ አውጥቶ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ማሳወቁንና ተግባራዊ መደረጉን ያረጋገጠ መሆኑን በተመለከተ፣**

34. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የደረጃዎች ፍተሻ አፈፃፀምን ውጤታማና ቀልጣፋ ለማድረግ የሚያግዝ የአሠራር መመሪያ አውጥቶ በሥሩ ለሚገኙ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ሊያሳውቅና ተግባራዊነቱን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

35. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የደረጃዎች ፍተሻ የአሰራር መመሪያ ታህሳስ 8 / 2005 በደብዳቤ ቁጥር 011.34/1089 ስለማውጣቱ የሚያሳይ ማስረጃ ከመውጫ ስብሰባ በኋላ ያቀረበ ቢሆንም፡፡

36. በሚኒስቴር መ/ቤቱ ስር ከሚገኙ ቅ/ጽ/ቤቶች መካከል በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው ከታዩት ቅ/ጽ/ቤቶች የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ጉዳዩን አስመልክተው በሰጡት መልስ የአዳማ ቅ/ጽ/ቤትና የሞጆ ተወካይ ጽ/ቤት ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ዝርዝር የሆነ የአሰራር መመሪያ ተዘጋጅቶ ያልተላከላቸው በመሆኑ ስራን ለይቶ ለማከናወን ችግር የፈጠረባቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ለምሳሌ የጋራ ስም በመጠቀም ኬብል ተብሎ የኤሌክትሪክ ይሁን የቴሌፎን መሆኑን ለመለየት የሚቸገሩ መሆናቸው፣ በተመሳሳይ ሚስማር የሚለው የቆርቆሮ ይሁን የእንጨት በግልጽ ያልተለየ በመሆኑ በአፈፃፀም ወቅት አስቸጋሪ መሆኑና አስገዳጅ ለሆኑ ምርቶች ወጥ በሆነ መልኩ ለመስራት መቸገራቸውን አስረድተዋል፡፡

37. መመሪያው ባለመኖሩ የደንበኛው የናሙና ውጤት እስከሚገለጽ ድረስ በውዴታ ግዴታ ዕቃው እንዲለቀቅ ከዋናው መ/ቤት ቢላክም ግዴታው እስከምን ድረስ መኬድ እንዳለበት /የእርምጃው አወሳሰዱ እስከ ምን እንደሆነ/ የማይታወቅ መሆኑ፣ በውዴታ ግዴታ ተለቀው የፍተሻ ውጤት የማያሟሉ ምርቶች ገበያ ውስጥ ቢገቡም እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል መመሪያ አለመኖሩ በአፈፃፀም ወቅት ችግር የፈጠረባቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሁሉም እንስፔክተሮች በመሰላቸው መንገድ ናሙና የሚወስዱ መሆኑ፣ ቴክኒካል የሆነ በቂ ሥልጠና ኢንስፔክቶሮቹ ያልተሰጣቸው መሆኑና በደብዳቤ ሥራው እንዲሠራ ከማሳወቅ ውጪ ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ አለመኖሩና የአሠራር ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ባለመሠራታቸው ምክንያት በናሙና አወሳሰድ ላይ ችግር እየፈጠረባቸው መሆኑን አስረድተዋል፡፡

38. የሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት የወጪ ምርትን በተመለከተ ከናሙና አወሳሰድ እስከ ውጤት ማሳወቅ ድረስ ያለው ሥራ በኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት የሚሠራ መሆኑን ገልፀው፣ ይሁን እንጂ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት ለወጪ ዕቃዎች ራሱ ናሙና ወስዶ ራሱ ፈትሾ ውጤቱን በባለጉዳዩ ለጽ/ቤታቸው የሚያመጡበት አሠራር የተሳሳተ አሠራር መሆኑን እንደሚያምኑ አስረድተው ወደ ቅርንጫፍ ጽቤቱ ባለጉዳዮች ራሳቸው ይዘውት የሚመጡት ውጤት ትክክል ይሁን አይሁን ለማረጋገጥ በማይቻልበት ሁኔታ እየሠሩ መሆኑንና ይህም ችግር ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ ካለመኖሩ የሚፈጠር መሆኑን ደንበኞች ያመጡትን ውጤት በመቀበል የይሁንታ ፈቃድ የሚሰጥ መሆኑን ለኦዲት ቡድኑ አስረድተዋል፡፡

39. በሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአሠራር መመሪያ ቀርጾ ለቅ/ጽ/ቤቱ አለመላኩን የጽ/ቤቱ ኃላፊ በመግለጽ መመሪያ ባለመኖሩም በሥራ አፈፃፀማቸው ላይ ተጽዕኖ እየፈጠረ እንደሚገኝና ሥራውን የሚሠሩት የደረጃዎች ዝርዝር በመጠቀም ከዳይሬክቶሬቱ ጋር በመነጋገር መሆኑ የስራ ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

40. ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ከሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ጋር ባደረገው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የናሙና ፍተሻ ሥራ ለተስማሚነት ምዘና ድርጅት ናሙና እራሱ ወስዶ እራሱ ፈትሾ ውጤቱን ለቅ/ጽቤታችን ሲልክ ትክክለኛነቱን የሚያረጋግጥበት መመሪያ ያለ መሆኑንና የተላከው ውጤት ጥርጣሬ የሚያስከትል ቢሆንም እንኳን ማረጋገጥ እንደሚቻል መመሪያ ለቅ/ጽቤቶቹ የተላከ መሆኑን እንዲሁም የውዴታ ግዴታ በራሱ ችግር ያለበት አሰራር ነው ሆኖም ግን እስከ ምን ድረስ ይኬዳል ለሚለው የሚወሰነው የተስማሚነት ምዘና ድርጅት ውጤቱን አይቶ ሲልክ ብቻ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

41. ይሁን እንጂ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች መመሪያ ልከናል ቢሉም የኦደት ቡድኑ በናሙና ባያቸው ቅ/ጽ ቤቶች መመሪያው የሌላቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሎል፡፡

42. በመሆኑም የገቢና ወጪ ዕቃዎችና የአሰራር መመሪያ በዝርዝር ግልጽ በሆነና በማያሻማ መልኩ ተዘጋጅቶ ለቅ/ጽ/ቤቶች ተሰራጭቶ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ባለመደረጉ እና ባለመከታተሉ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶች አስገዳጅ ደረጃዎችን በአግባቡ ያሟሉ ወይም ያላማሉ መሆኑ ሳይረጋገጥ የገቢ ዕቃዎች ከጉምሩክ እንዲለቀቁ በማድረግ ተጠቃሚው ህብረተሰብ ጥራታቸውን ያልጠበቁና ለጉዳት የሚዳርጉ ምርቶች ወደ ገበያ እንዲሠራጩ ያደረገ ሲሆን እንዲሁም የናሙና አወሳሰድ እንዳይታወቅ ማድረጉና የወጪ ምርቶች ትክክለኛነትን ተገቢውን ደረጃ ስለማሟላታቸው ርግጠኛ ማረጋገጫ ለመስጠት ስለማያስችል የአሠራር ክፍተቶችን እንዲፈጠር በማድረግ የሀገራችን የወጪ ምርት በጥራት ተወዳዳሪ እንዳይሆን ሊያደርግ ይችላል፡፡

**ሚኒስቴር መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች በሰው ኃይል እንዲደራጁ በማድረግና ለሥራው የሚሆኑ መገልገያዎችን በማሟላት አፈጻጸማቸውን ክትትል እና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ፣**

43. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሥሩ ያሉትን ቅ/ጽ/ቤቶች በሰው ኃይል በማደራጀትና ለሥራው የሚሆኑ መገልገያዎችን በማሟላት አፈጻጸማቸውን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

44. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በእስትራቴጂክ ዕቅዱና ዓመታዊ ዕቅዱ ላይ የሰው ሃብት በቁጥር፣ በዕውቀት፣ በክህሎት እና አመለካከት በማጐልበት የማስፈፀም አቅምን ወደ ተሻለ ደረጃ ለማድረስ ቢያቅድም በዕቅዱ መሠረት በሥሩ ያሉትን ቅ/ጽ/ቤቶች በሰው ኃይል በማደራጀት፣ ለሥራው የሚሆኑ መገልገያዎችን በማሟላት እና በቂ በሆነ ሥልጠና ክህሎታቸውን በማሳደግ አፈጻጸማቸውን እየተከታተለ አለመሆኑ ታውቋል፡፡

45. በኦዲቱ ወቅት ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለማረጋገጥ እንደተቻለው በአዲስ አበባ፣ ኮሚት፣ አዳማ፣ ሞጆ፣ ሀዋሣ እና ሞያሌ ቅ/ጽቤቶች ለሥራ የሚያስፈልጉ በቂ የሰው ኃይል ያልተደራጀ መሆኑ ታውቋል፡፡ በሚኒስቴር መ/ቤቱ አዳማና ሞጆ ጽ/ቤቶች ባለው የሰው ኃይል ክፍተት ምክንያት አንድ ባለሙያ ከሥራው ሥነ ምግባር ውጪ ተደራራቢ ሥራዎችን ማለትም የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ በኃላፊነታቸው ሥራ ላይ ደርበው ገንዘብ የሚቀበሉና የናሙና ውጤት ከተስማሚነት ድርጅት የሚያመጡ መሆኑ ታውቋል፡፡ በተጨማሪ በቂ የሆነ የመገልገያ መሣሪያዎች ባለመሟላታቸው ምክንያት የወጪ ዕቃዎች የጥራት ቁጥጥር ከቦታ ቦታ በመዘዋወር የሚከናወን በመሆኑ ከ2005-2007 በጀት ዓመት ያሉ አንዳንድ የሥራ

መደቦች በሰው ኃይል ባለመሸፈናቸው ምክንያት ለደንበኞች ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት እንዳልተቻለ ለመረዳት ተችሏል፡፡

46. እንዲሁም በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ግብዓቶችን ለማሟላት የተመደበው የሥራ ማስኬጃ ማነስ እና በወቅቱ እንዲደርስ አለመደረጉ፣ የገቢ ምርቶችን በወቅቱ ለፍተሻ ላቦራቶሪ ለመላክም ሆነ የፍተሻ ውጤቶችን በወቅቱ ለመቀበል የተሽከርካሪ ችግር መኖሩ፣ በነዳጅ እጥረትና በቅጾች አለመባዛት ችግር በሥራ ላይ ተፅዕኖ መፍጠሩ፣ ናሙና ለመውሰድ ደንበኞች በሚያቀርቡት ተሽከርካሪ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ባለሙያዎቹ የሚጠቀሙ በመሆኑ በባለሙያዎቹ ላይ ነፃ የሆነ ውሳኔ ለማሳለፍ የሰነ-ልቦና ችግር የተፈጠረ መሆኑና የናሙና መለወጥ ችግር አልፎ አልፎ እያጋጠመ በመሆኑ እነዚህ ችግሮች ለብልሹ አሠራር በር እየከፈቱ መሆኑን የኦዲት ቡድኑ ከሚመለከታቸው የቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች ጋር ባደረገው ውይይት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

47. ከዚህ በተጨማሪም የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ባካሄደው የዶክሜንት ክለሳ የደሴ ቅ/ጽ/ቤት አፋር /ሚሌ/ ጉምሩክ ጣቢያ ድረስ በመሄድ የተጣለበትን ኃላፊነት በተገቢውና በተቀላጠፈ ሁኔታ ለመወጣት በተሽከርካሪ አለመኖር ምክንያት ከፍተኛ የሥራ ክፍተት እየተፈጠረበት መሆኑን፣ እንዲሁም ለናሙና በመጡ ዕቃዎች ማስቀመጫ መጋዘን ባለመኖሩ ሠራተኞችንና ተገልጋዮችን ለአደጋ ያጋለጠ መሆኑን እና በሥራቸው ላይ ተፅዕኖ የፈጠረባቸው መሆኑን የአዳማ፣ ጅማ፣ ጐንደር፣ ኮሜት ተወካይ፣ ደሴ፣ ሀዋሣ እና ሁመራ ቅ/ጽ/ቤቶች፣ ከሚያዘጋጁት ወርሃዊ ሪፖርት፣ ሳምንታዊ የውይይት ሪፖርትና ቃለ-ጉባኤ ላይ ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

48. የሞጆ ተወካይ ጽ/ቤት ከፍተኛ የሆነ የስራ እንቅስቃሴ የሚካሄድበት ሆኖ ሳለ ራሱን ችሎ በሰው ሃይል የተደራጀ አለመሆኑና በስራ ላይ ያለው የሰው ሃይል የአዳማ ቅ/ጽ/ቤት ሰራተኞች በሺፍት በየ2 ሳምንቱ እየተቀያየሩ እንዲሠሩ መደረጋቸው፣ ይህም በመሆኑ የሂሳብ ሰራተኛ በተወካይ/ጽ/ቤቱ በቋሚነት ባለመኖሩ ደንበኞች ደረሰኝ ቶሎ ባለማግኘታቸው ቅሬታ የፈጠረባቸው መሆኑን ለኦዲት ቡድኑ ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ጋር ባደረገው ውይይት ለማወቅ ተችሏል፡፡

49. ከዚሁ ጋር በተያያዘ አዳማ ቅ/ጽ/ቤት ለስራ የሚያስፈልጉ መገልገያዎች ያልተሟሉ በመሆኑ፣ ለምሣሌ የሶስተኛ ወገን ሰርተፊኬት ደንበኞች ሲያመጡ ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ የኢንተርኔት አገልግሎት ባለመኖሩ ምክንያት በደንበኞች ላይ መጉላላት የተፈጠረ መሆኑ፣ እንዲሁም ለሴፍቲ የሚያሰፈልጉ ቁሳቁሶች ያልተሟላ መሆኑን የቅ/ጽ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልጸዋል፡፡

50. ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ከሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ጋር ባደረገው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቻችን ሠራተኞች ከጥበቃ ጀምሮ እስከ ኃላፊ የሥነ ምግባርና የቴክኒክ ስልጠና የተሰጠ መሆኑ፣ በሰው ኃይል አደረጃጀትም ክፍተት ያለው የአዳማ ቅርንጫፍ ከተከፈተ በኋላ በባህር ትራንዚት ሰው እንዲመደብ ተጠይቆ በሞጆ ቅርንጫፍ የሰው ኃይል ስላልተሟላ የአደማ ሥራ እየቀለለ በመሄዱ ወደ ሞጆ ቅርንጫፍ ሠራተኞችን በመላክ እንዲሰራ መደረጉንና ይህም አሰራር ጫና የፈጠረ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

51. በመሆኑም ሠራተኞችን ለመቅጠር ማስታወቂያ ወጥቶ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዲስ አደረጃጀት እንደገና እየተዋቀረ በመሆኑ ስራው ቆሟል፡፡ ኢንተርኔትን በተመለከተ የቴሌ ችግር መሆኑንና እንዲሁም ኢንተርኔት የሌላቸውም ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲያስገቡ የተፈቀደ በመሆኑ የማስገባቱ ሥራ የቅ/ጽ/ቤቶቹ መሆኑን በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ላይ ገልጸዋል፡፡ ስለሆነም እንዲያስገቡ ፋይናንስ ደብዳቤ በተጻፈው መሠረት ማስገባት ነበረባቸው ካላስገቡ ይህ የቅ/ጽቤቶቹ ችግር መሆኑን አስረድተዋል፡፡

52. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሥሩ ያሉትን ቅ/ጽ/ቤቶች በተሟላ የሰው ኃይል እንዲደራጅና ለሥራው የሚያስፈልጉ መገልገያዎችን እንዲሟሉ ባለማድረጉና አፈጻጸማቸውን ባለመከታተሉ ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት ውስንነት እንዲኖርና ተደራራቢ ሥራዎች በአንድና ሁለት ሰው ብቻ እንዲሸፈን በማድረግ ለብልሹ አሠራር በር እንዲከፍት ከማድረጉ በተጨማሪ የናሙና መለወጥና መሰባበር ሁኔታ እንዲፈጠር ማድረጉ፣ ላቦራቶሪ ለመላክም ሆነ የፍተሻ ውጤቶችን በወቅቱ ለመቀበል አስቸጋሪ ማድረጉና በደንበኞች ላይ ቅሬታ እና መጉላላት እንዲፈጠር አድርጓል፡፡

**ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ የገቢ ምርቶች ከአገር ከመውጣታቸው በፊትና ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው ገበያ ላይ ከመዋላቸው በፊት ደህንነታቸው እና ጥራታቸው የጠበቁ መሆኑን ማረጋገጡን በተመለከተ፣**

53. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ምርቶች ከአገር ከመውጣታቸው በፊት ደህንነታቸው እና ጥራታቸው እንዲሁም የሀገሪቱ ህግ በሚፈቅደው መሰረት የሚወጡ መሆናቸውን ሊያረጋግጥ፣ እንዲሁም ከውጪ የሚገቡ ምርቶች ወደ ገበያ ከመግባታቸው በፊት በጉምሩክ ጣቢያዎች ደህንነታቸውና ጥራታቸው እንዲሁም ተገቢውን መስፈርት ያሟሉ መሆናቸውን ሊረጋገጥና ምርቶች የሀገሪቱን ህግና ደንብ ተከትለው መግባታቸውን/መለካታቸውን በማረጋገጥ ይሁንታ /Permit/ ሊሰጥ ይገባል፡፡

54. ይሁን እንጂ የወጪ ምርቶች ከአገር ከመውጣታቸው በፊት ደህንነታቸው እና ጥራታቸውን ጠብቀው እንዲሁም የሀገሪቱ ህግ በሚፈቅደው መሰረት እንዲወጡ አልፎ አልፎ የማይደረግበት ሁኔታ መኖሩን በሚኒስቴር መ/ቤቱና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የማስረጃ ክለሳና ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ቃለ መጠይቅ በማድረግ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

55. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 691/2003 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የወጪ ምርቶች ከአገር ከመውጣታቸው በፊት ደህንነታቸው እና ጥራታቸው ጠብቀው የሀገሪቱ ህግ በሚፈቅደው መሰረት እንዲወጡ መደንገጉ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በተደረገው የዶኩሜንት ክለሳ በሚ/ር መ/ቤቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶች ጥራታቸውን ለማረጋገጥ የሚበጠሩበት አንዳንድ የማበጠሪያ ቤት መጋዘኖች ናሙና ለመውሰድ በሚያመች መልኩ ያልተደረደሩ መሆኑ፣ እንዲሁም ማበጠሪያ ቤቶች ወቅቱን ጠብቀው የንግድ ፈቃድ እድሳት አለመፈፀማቸው የተቀላጠፈ አገልግሎት ባለመሥጠትና በምርት ጥራት ላይ ተጽዕኖ የፈጠረ በመሆኑ፣ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት ስለመቆጣጠሩና ስለመከታተሉ የሚያረጋግጥ የክትትል ሥራ አለመሰራቱ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

56. በኦዲቱ ወቅት የታዩ ቅ/ጽ/ቤቶች የአዳማ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት በአዳማ ከ50 በላይ የማበጠሪያ ቤቶች እንዳሉና አዲሶቹ ጥራታቸውን ጠብቀው እየሠሩ ያሉ መሆኑንና የድሮዎቹ ማበጠሪያ ቤቶች ጥራታቸው የወረደ በመሆኑ አደራደራቸው ናሙና ለመውሰድ አስቸጋሪ መሆኑ፣ እንዲሁም በሃዋሳ ቅ/ጽ/ቤት ተስማሚነት ምዘና ማበጠሪያ ቤቶች ምርቶቹ ናሙና ለመውሰድ በሚያስችል መልኩ ያልተደረደሩ መሆኑን የስራ ኃላፊዋቹ ገልጸዋል፡፡

57. የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅትም ይህ ችግር ከ2007 ዓ.ም. በፊት አንደነበረና የንግድ ሚኒስቴር የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ማበጠሪያ ቤቶች ችግር እንዳለባቸው ለድርጅቱ ሲገልጽ ድርጅቱ እርምጃ ለመውሰድ እንዲያመቸው የትኞቹ ማበጠሪያ ቤቶች እንደሆኑ በስም እንዲጠቀስለት ሚ/ር መ/ቤቱን ቢጠይቁም እንዳላሳወቀው የሥራ ኃላፊዎቹ ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ ድርጅቱ ክትትል በማድረግ የነበረው ችግር ከ2007 በጀት ዓመት ወዲህ መቀረፉን ቢገልፁም ስለመቀረፉ የሚገልጽ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡

58. በተጨማሪም የሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በዋነኛነት እየተጠቀመበት ባለው መጋዘን ለሰው ልጅ ምግብነት የሚውሉ ከሀገር የሚወጡ የግብርና ምርቶች፣ የተለያዩ ዓይነት ኬሚካሎችና የሸቀጣ ሸቀጥ ምርቶች በአንድ መጋዘን እየተከማቹ በመሆናቸው የሚጠቀምበትም መጋዘን ለሰው ልጅ እጅግ ጠንቅ በሆኑ ኬሚካሎች የተበከለና ከፍተኛ የጽዳት ጉዳለት ያለው ከመሆኑም ባሻገር የምግብ ውጤቶችን ለማከማቸት ማሟላት ያለበትን

መስፈርት የማይሟላ መሆኑን የሞያሌ የንግድ ሚኒስቴር ቅርንጫፍ ቅ/ጽ/ቤት እንዳረጋገጡ ታውቋል፡፡ በዚሁ መሠረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የችግሩን አሳሳቢነት ከግምት ውስጥ በማስገባት በተጠቀሰው መጋዘን ላይ አስቸኳይ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በ23/01/2007 ዓ.ም በቁጥር 4/9/01/038/07 በተፃፈ ደብዳቤ ቢጠይቅም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ችግሩን ለመቅረፍ የሚያስችል እርምጃ እንዳልተወሰደ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

59. በሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት በህጋዊ መንገድ የሚወጡ የወጪ ምርቶች ላይ ደህንነታቸውና ጥራታቸው ተረጋግጠው እንዲወጡ ለማስቻል ጥረት መኖሩን፤ ነገር ግን በህገወጥ መንገድ የሚወጡ ምርቶች ከፍተኛ ደረጃ ላይ በመድረሱ የወጪ ምርቶችን በከፍተኛ ሁኔታ እያዳከመው መሆኑን የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡ በዚሁም መሠረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ይህንን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ችግሩን ለመለየት ጥናት ተጠንቶ የችግሩ መንስኤ በየመውጫ ኬላዎች የተጠናከረ ቁጥጥርና ክትትል ባለመኖሩ የወጪ ምርቶች በከፍተኛ ሁኔታ ከሀገር በህገወጥ መንገድ በመውጣታቸው በቅ/ጽ/ቤቱ የሚሠራውን ሥራ እንዲቀዘቅዝ ያደረገው መሆኑ በጥናቱ ቢታወቅም ችግሩን ለመቅረፍ ሚ/ር መ/ቤቱ ጥናቱን አጽድቆ ባለመላኩ እና እርምጃ ባለመወሰዱ ህገ ወጥነት እየተባባሰ መሆኑ የስራ ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

60. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከውጪ የሚገቡ ምርቶች ወደ ገበያ ከመግባታቸው በፊት በጉምሩክ ጣቢያዎች ደህንነታቸውና ጥራታቸው እንዲሁም ተገቢውን መስፈርት ያሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያለበት ሲሆን፣ ነገር ግን ምርቶችን ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገቡ የተለያዩ አስመጪዎች በኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት ናሙና ተወስዶ የደረጃ ፍተሻ ተደርጎ ውጤቱ ሳይረጋገጥ በጊዜያዊ መልቀቂያ እንዲለቀቅ የሚደረግና ለጉምሩክ በደብዳቤ በማሳወቅ ምርቶቹ ወደ ገበያ የሚሠራጩበት ሁኔታ መኖሩን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

61. የኦዲት ቡድኑ በናሙና ካያቸው ባለድርሻ አካላት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሞያሌ ቅርንጫፍ ጽቤት እና ሞጆ ቅርንጫፍ ያለው አሠራር ሚኒስቴር መ/ቤቱ የናሙና ውጤታቸው እስከሚታወቅ ድረስ ስለሚዘገይ በሚል የውዴታ ግዴታ ገብተው ዕቃዎች እንዲለቀቅላቸው በደብዳቤ እያሳወቁ የሚለቁና የጥራት ደረጃቸው ያልተረጋገጡ የገቢ ምርቶች መኖራቸውን ገልፀው ነገር ግን የባለሥልጣኑ ቅ/ጽ/ቤት ከበላይ ትዛዝ ካልደረሰው በራሱ እንደማይለቅ ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም የሶስተኛ ወገን ሰርተፊኬት ማቅረብ ያልቻሉ አስመጪዎች ምርታቸው የደረጃ መስፈርት ማሟላቱ ሳይረጋገጥ የላብራቶሪ ውጤት እስከሚገለጽ ድረስ በጉምሩክ መጠበቅ ያለባቸው ቢሆንም በውዴታ ግዴታ ይለቀቅ የሚል

ደብዳቤ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለባለሥልጣኑ ሲጽፍ የሚለቀቁ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህም በመሆኑ ሰነዶቻቸው ተጠናቀው የማይተላለፉበት ሁኔታ መኖሩ እና የሠነዶቻቸውን ቁጥር እንደሚያበዛባቸው እና ሥራዎች ተንጠልጥሎ እንደሚቆይ የሚያደርግ መሆኑን የኦዲት ቡድኑ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ካቀረቡት ቃለ መጠይቅ ምላሽ ለማወቅ ተችሏል፡፡

62. በኮሜት ተወካይ ቅ/ጽ/ቤት ቀደም ሲል በነበረው አሰራር ምርቶች በላብራቶሪ ተፈትሸው ውጤት እስከሚገለጽ ድረስ ለረጅም ጊዜ የሚቆዩ በመሆኑ (3ወርእና ከዚያ በላይ) በውዴታ ግዴታ ውል በማስገባት በጊዜያዊነት ይለቀቅ ነበር ነገር ግን አሁን ባለው አሰራር የሶስተኛ ወገን ሰርተፊኬት ካልመጣ በስተቀር ምርቶች የሚለቀቁበት አሰራር መቆሙንና አሁን የኢንቨስትመንት፣ ዕቃዎች እስከ አሁን ድረስ በውዴታ ግዴታ ደብዳቤ በጊዜያዊነት የሚለቀቁና በተጨማሪም ምርቶች መጠናቸው አነስተኛ ሲሆኑ ለደረጃው መስፈርት ናሙና ለመውሰድ የማያስችል አነስተኛ መጠን ሲሆኑ በላብላቶሪ ሳይፈተሹ የሚለቀቁ መሆኑን የሥራ ኃላፊዎቹ ለኦዲት ቡድኑ ገዋፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ የተለያዩ ምርቶችን ከውጭ ሀገር የሚያስገቡ ድርጅቶች የሶስተኛ ወገን ሰርተፊኬት ማቅረብ ሲኖርባቸው ሳያቀርቡ ዕቃቸው የሚለቀቁበት አሠራር መኖሩን የኦዲት ቡድኑ ባካሄደው ምርመራ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

63. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ቃሊቲ ቅርንጫፍ ከ2006 ዓ.ም. በፊት የሶስተኛ ወገን ሠርተፊኬት ሳይጀመር ናሙና ተወስዶ ውጤት እስኪመጣ ድረስ በጣም ስለሚዘገይ ውጤት እስኪመጣ ደንበኞች የውዴታ ግዴታ ገብተው ዕቃዎች እንዲለቀቁ እንደሚደረግ ገልጸው በአሁኑ አሠራር ግን የሶስተኛ ወገን ሠርተፊኬት ማምጣት ከተጀመረ ወዲህ እንዳይለቀቅ ቢደረግም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ዕቃዎች እንዲለቀቁ ደብዳቤ እንደሚጽፉላቸውና ዕቃዎቹን የሚለቁ መሆኑ ገልፀዋል፡፡ ይህ በመሆኑም በአሠራር ክፍተት ስለሚፈጥር እና የተገልጋዩን ጤንነት ስለሚጐዳ መቅረት እንዳለበት እንደሚያምኑ የስራ ኃላፊዎቹ ለኦዲት ቡድኑ ገልጸዋል፡፡

64. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የገቢና ወጪ ዕቃዎች የሀገሪቱን ህግና ደንብ ተከትለው መግባታቸውን/መለካታቸውን በማረጋገጥ ይሁንታ /Permit/ ሊሰጥ የሚገባ ቢሆንም በአንዳንድ ዕቃዎች ላይ ይህ አሠራር ተግባራዊ እንዳልተደረገ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

65. በመሆኑም የገቢ ምርቶች የሀገሪቱን ህግና ደንብ ተከትለው ስለመግባታቸውና መውጣታቸው በኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት የላብራቶሪ ፍተሻ ውጤት ተረጋግጦ ውጤቱ ሳይገለጽ ለዕቃዎቹ ይሁንታ የሚሰጥና ከጉምሩክ ጣቢያ በውዴታ ግዴታ የሚለቀቁና

እንዲሁም ሚ/ር መ/ቤቱ ሳያውቅ ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው ስራ ላይ ከዋሉ በኋላ ይሁንታ የሚሰጣቸው መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡

66. በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት በላብራቶሪ የሚፈተሹ ምርቶች ከኤሌክትሪክ ዕቃዎች በስተቀር በተለይ እንደ ባትሪ ያሉ ለሶስት ጊዜ በተከታታ ሳይወድቅ ደረጃውን ካለፈ በውዴታ ግዴታ እንዲገባ ተደርጎ እንዲለቀቅ የሚደረግ መሆኑን እና የ3ኛ ወገን ሰርተፊኬት ከተጀመረ ወዲህ ለሌላ ዕቃ ሰርተፊኬት እንዲያቀርቡ በማሳወቅ ለአንድ ጊዜ ብቻ በውዴታ ግዴታ እንዲለቀቅ የሚደረግበት አሠራር መኖሩን ገልፀዋል፡፡

67. የኦዲት ቡድኑ የገቢ ዕቃዎችን የጥራት ማረጋገጥ ሥራን አስመልክቶ የክሽሪና ፖኘላር ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር ሚኒስቴር መ/ቤቱ ዕቃው የሚጠይቀውን ደረጃ ስለማሟላቱ የሚሰጠውን የይለፍ ፈቃድ/permit/ ሳያገኝ ከውጪ ሀገር ያስመጣቸውን የልብስ እና የገላ ሳሙናዎችን አገልግሎት ላይ ማዋሉን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በመሆኑም ሚ/ር መ/ቤቱ ለአዲስ አበባ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን መ/ቤት ለሞጆ ደረቅ ወደብ ጉምሩክ ቅጽ/ቤት ለድርጅቱ ደብዳቤ ሰነድ እንዲበተንላቸው መፈቀዱ ከተከለሱ ሰነዶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

68. በተመሳሳይ መልኩ ትሬድ ሊንክ ኃ/የተ/የግል ማህበር በዲክላራስዮን ቁጥር C-5978; C-7836; C-12251; C-1082 ከውጪ ያስመጧቸው ጊቭ የገላ ሣሙና የጥራት ደረጃቸው በኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት ሳይረጋገጥና ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሳያሳውቁና ሙሉ የመልቀቂያ ፈቃድ ከሚ/ር መ/ቤቱ ሳያገኙ ሽያጭ ካዋሏቸው በኋላ ሚ/ር መ/ቤቱ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን መ/ቤት ለሞጆ ደረቅ ወደብ ቅጽ/ቤት በደብዳቤ ሰነድ እንዲበተንላቸው የተፈቀደ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

69. ወጪ ምርቶችን በተመለከተ ንግድ ሚኒስቴር ለኢትዮጵያ ተስማሚነት ድርጅት ናሙና ወስዶ ፈትሾ ውጤቱን እንዲያሳውቀው ውክልና የሰጠው ቢሆንም ድርጅቱ ውጤቱን ለደንበኛው በመስጠት ደንበኛው ውጤቱን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሲያደርስ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃድ የሚሰጥበት አሠራር የወጪ ምርቶችን የጥራት ደረጃ በአግባቡ ለማረጋገጥ የማያስችልና ለብልሹ አሠራር በር የሚከፍት መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

70. ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ከሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ጋር ባደረገው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ መጋዘን የመቆጣጠር ሥራ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት መሆኑ እና ናሙና የመውሰድ ሥራ የተስማሚነት ድርጅት በመሆኑ በድርጅቱ ሥራ ጣልቃ አትግቡብን የሚል አቅጣጫ ስለተሰጠ የማረጋገጥ ሥራ አይሰራም፡፡ ቢሆንም ግን በአዋሣ አከባቢ በቅርቡ መጋዘኖችን ስታንዳርዳቸውን ሳያሟሉ ፈቃድ ተሰጥቷቸውና ፈቃዳቸውን ሳያሳድሱ እየሠሩ ያሉ ማበጠሪያ ቤቶች መኖራቸውን የአዋሣ ቅርንጫፍ

ተስማሚነት ምዘና ድርጅት ሪፖርት አድርጓል፡፡ ለመታየቱም ምክንያት የሆነው አንድ ምርት ሞያሌ ሄዶ ሲታይ ሰብ ስታንዳርዱ ያልተበጠረ ምርት የሚያሳይ ነው ተብሎ ሄዶ ሲታይ ይላካል ተብሎ ቃል የተገባበት ምርትና የተላከው ቀሪ የሚያሳየው እንዳልወጣ በመሆኑ በሞያሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በተፃፈው መሠረት መስተካከያ እንዲደረግ ደብዳቤ መጻፉን ገልጸዋል፡፡ ለሞያሌ ቅርንጫፍ ገቢዎችና ጉምሩክ ምግብና የኬሚካል ውጤቶች ትክክል አለመሆኑ ተነግሯቸው የመጋዘን ጥበት እንዳለባቸውና ችግሩ የሚፈታው ሌላ ተጨማሪ መጋዘን ሲሰራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

71. ኮንትሮባንድ የመቆጣጠር ሥራ ኃላፊነት የሚ/ር መ/ቤቱ ባይሆንም በኮንትሮባንድ በሚወጡ ምርቶች ችግርን በተመለከተ ከክልል የገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች ጋር ውይይት ተደርጎ ኬኒያ ከሞያሌ ከተማ ጀርባ በመሆኑ፤ በአዋጅ አንድን ዕቃ በኮንትሮባንድ እንዳይወጣ መከላከል የሚቻለው ከ15 ኪ.ሜ ርቀት ሲኖር በመሆኑ ከኬኒያ ኢትዮጵያ ያለው ርቀት በጣም ቅርብ ስለሆነ ለመቆጣጠር አስቸጋሪ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ምክንያቱም ዕቃዎች ሲገቡና ሲወጡ ለማህበረሰቡ ፍጆታ የሚውል ነው በሚል ለመቆጣጠር አስቸጋሪ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በአብዛኛውም በኮንትሮባንድ የሚወጣው እንደ ቀይ ቦሎቄ ያለ ምርት በመሆኑ ለመቆጣጠር የማይቻልበት ደረጃ ላይ ስለሆነና ሚኒስቴር መ/ቤቱም ከባለድርሻ አካላት ጋር የተጠና ጥናት የሌለው መሆኑን ለኦዲት ቡድኑ ገልጸዋል፡፡

72. ይሁን እንጂ የስራ ኃላፊዎቹ በኮንትሮባንድ የሚወጡ ምርቶችን በተመለከተ የተጠና ጥናት የለም ቢሉም የኦዲት ቡድን ከሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት በህገወጥ መንገድ የሚወጡ ምርቶችን ተመልክቶ ከባለ ድርሻ አካላት ጋር የተጠና ጥናት ረቂቅ ለኦዲት ቡድኑ ቀርቧል፡፡

73. ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶች ወደ ገበያ ከመግባታቸው በፊት በጉምሩክ ጣቢያዎች ደህንነታቸውና ጥራታቸው እንዲሁም ተገቢውን መስፈርት ያሟሉ መሆናቸውን ወጥ በሆነ መልኩ በአግባቡ ባለመረጋገጡ የአሠራር ክፍተት መኖሩ ደረጃቸውን ያልጠበቁ ምርቶች ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ በማድረግ በተጠቃሚው ህብረተሰብ ላይ ጉዳት እንዲደርስ የማድረግ እንዲሁም ሀገሪቱ ላወጣችው የውጭ ምንዛሬ ተመጣጣኝ ያልሆነና ደረጃውን ያልጠበቀ ሸቀጥ ማራገፊያ እንድትሆን ያደርጋል፡፡ እንዲሁም ወደ ውጭ በሚላኩ ምርቶች የሚካሄደው የጥራት ደረጃ ምርመራ ባለጉዳዮች ራሳቸው ውጤቱን ከኢትዮጵያ ተስማሚነት ድርጅት በመውሰድ ሚ/ር መ/ቤቱ እንዲያፀድቅ የሚደረገው አሠራር ለብልሹ አሠራር በር የሚከፍትና ጥራትና ደረጃቸውን ያልጠበቁ የሀገር ምርቶች እንዲወጡ በማድረግ ሀገሪቱ በወጪ ንግድ በጥራት ተወዳዳሪ እንዳትሆን ሊያደርጋት ይችላል፡፡

**ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተፈላጊውን የደረጃ መስፈርት የማያሟሉ የንግድ ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም ከሀገር እንዳይወጡ ያገደ መሆኑን፣ ከተዘጋጀላቸው ደረጃ በታች ሆነው በተገኙት ላይ እርምጃ መውሰዱን በተመለከተ**

74. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪና የገቢ ንግድ ዕቃዎች ተፈላጊውን የደረጃ መስፈርት የማያሟሉ የንግድ ዕቃዎች መኖራቸውን ሲያረጋግጥ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም ከሀገር እንዳይወጡ ሊያግድና አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ያላቸው የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ደረጃውን መስፈርት ማሟላታቸውን ሊቆጣጠር ከተዘጋጀላቸው ደረጃ በታች ሆነው በተገኙት ላይ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

75. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 691/2003 መሰረት የወጪና የገቢ ንግድ ዕቃዎች ተፈላጊውን የደረጃ መስፈርት የማያሟሉ የንግድ ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም ከሀገር እንዳይወጡ ማገድ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ ይሁን እንጂ የገቢ ዕቃዎችን በተመለከተ የደረጃ መስፈርት የማያሟሉ በኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት የላብራቶሪ ውጤት ወይም በዓለም አቀፍ ሶስተኛ ወገን ሠርተፊኬት አምጥተው ትክክለኛነቱ ተረጋግጦ ደረጃቸውን የማያሟሉ መሆናቸው ተረጋግጦ እንዲታገዱ ከተደረገ በኋላ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጁ ከተደነገገው በተቃራኒ ደብዳቤ በመጻፍ እንዲለቀቁ የሚያደርግ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ጉዳዩን አስመልክቶ ከተካሄደው የዶኩሜንት ክለሳዎችና ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት ውጤቱን ሲልክ ዕቃዎቹ የኢትዮጵያ ደረጃ የማያሟሉና ቀድመው የሚለቀቁ በመሆኑ በህጉ መሠረት ጥራታቸው ሳይረጋገጥ ወደ ገበያ ገብተው ለተጠቃሚው የሚደርሱ መሆናቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡ (አባሪ 2 )ተያይዟል፡፡

76. አምፖሎች ከታገዱ በኋላ ለአንድ ጊዜ ብቻ እንዲገቡ በሚል ሚኒስቴር መ/ቤት በደብዳቤ በፃፈላቸው መሠረት የተለቀቁ እና ለተጠቃሚው ህብረተሰብ የቀረቡ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

77. ለአብነት ያህል ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለአፈዲሆም ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በዲ/ዮን ቁጥር C1996/2013 በተመዘገበ ሰነድ ከቻይና ሀገር ያስመጧቸው በቁጥር 600 ካርቶን ኃይል ቆጣቢ አምፑሎች ሬድ ሉመን በማሽኒያ ላይ ባለመጠቀሱ እንዳይገባ በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት የታገደውን ኃይል ቆጣቢ አምፑል የሚፈለገውን የደረጃ መስፈርት ሳያሟላ በጳጉሜ 5/2005 ዓ.ም. በቁጥር 01-1-34/4881 በተፃፈ ደብዳቤ ሚኒስቴር መ/ቤቱ እንዲለቀቅ መፍቀዱን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

78. በተመሳሳይ መልኩ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለተመስገን ላቢሶ ላኪ አማካኝነት በኢንቮይስ ቁጥር P.I. No.TL/007/15 የተመዘገበና ክብደቱ 45 ቶን የሆነ ቀይ በሎቄ እና በኢብራሂም መኒር

ላኪ አማካኝነት በኢነቮይስ ቁጥር 0002/2015 የተመዘገበና ክብደቱ 45 ቶን የሆነ የእርግብ አተር አስገዳጅ የኢትዮጵያን ደረጃ የማያሟላ ምርት መሆኑን ጠቅሶ የሞያሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በቀን 21/06/2007 ዓ.ም. በቁጥር 4//9/1/479/07 እና በቀን 21/06/2007 ዓ.ም. በቁጥር 4/9/1/480/07 ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ለሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት በጻፈው ደብዳቤ ምርቱ ከሀገር እንዳይወጣ ከታገደ በኋላ በቀን 24/06/2007 ዓ.ም. በቁጥር 4/9/1/495/07 እና በ24/06/2007 ዓ.ም. በቁጥር 4/9/1/496/07 እገዳው ተነስቶ ምርቱ ከሀገር እንዲወጣ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተፈቀደ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

79. በሌላ መልኩ ደንበኞች የሶስተኛ ወገን ሠርተፊኬት ካመጡ ያስመጧቸውን የገቢ ምርቶች እንዲለቀቅላቸው ሚኒስቴር መ/ቤቱ ህዳር/2006 ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ያሳወቀ ሲሆን፣ ነገር ግን ለአዳማ ቅርንጫፍ ሚያዝያ/2006 በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተላለፈው መመሪያ ዘግይቶ መድረሱ ታውቋል፡፡ በመሆኑም ደንበኞች ያስመጧቸውን ዕቃዎች በውዴታ ግዴታ መሠረት ውጤቱን ባያሟላም እንዲታገዱ ያልተደረጉ እና የሚለቀቁ መሆኑ ታውቋል፡፡ እንዲሁም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ደረጃቸውን የማያሟሉ ገቢ ዕቃዎች አግደው ለሚ/ር መ/ቤቱ ቢያሳውቁም አስመጪዎች የታገደባቸው ዕቃ እንዲለቀቅላቸው ሚ/ር መ/ቤቱን ሲጠይቁ በበላይ አመራር እንዲፈቀድላቸው የሚደረግ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

80. በአዋጅ ቁጥር 691/2003 አስፈላጊውን የደረጃ መስፈርት የማያሟሉ የንግድ ዕቃዎች ወደ ሃገር እንዳይገቡ የተደነገገ መሆኑ ይታወቃል፡፡ አንዳንድ ጊዜ አዋጁ በዝርዝር ያላካተተታቸው እና በደረጃው መሰረት በዝርዝር ያልተካተቱ ምርቶች ቁጥጥር አፈጻጸም ላይ መ/ቤቱ በስራ ማኑዋል መሰረት እንደ ዕቃው መጠንና የሚውልበት አገልግሎት በበላይ አመራሩ ውሳኔ የሚሰጥበት አሰራር መኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በመሆኑም ገቢ ዕቃዎች አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ባለማሟላታቸው እንደ ገላ ሳሙና፣ የዱቄት ሣሙና /ኦሞ/ የኤሌክትሪክ ዕቃዎችና ኃይል አባካኝ አምፖሎች በኮሜት ተወካይ ጽ/ቤት ከታገዱ በኋላ ሚኒስቴር እንዲገቡ መፍቀዱን በኦዲቱ ወቅት ከተሰበሰበ ማስረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

81. በመሆኑም ለምሣሌ ኙራይም እንጉዳይ ኃ/የተ/የግ/ድርጅት ከማሊዥያ ወደ ሀገር ውስጥ ያስመጣቸው የገላ ሳሙናዎች በተደረገው የላብራቶሪ ፍተሻ (Free fatty acid/ የደረጃውን መስፈርት አለማሟላቱ ቢገለጽም ወደ ሀገር እንዲገባ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን መ/ቤት ደብዳቤ በመጻፍ ሳሙናው ወደ ሀገር እንዲገባ መፍቀዱን በኦዲቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፣

82. እንዲሁም ፑንት ጠቅላላ የንግድ ድርጅት እና የኮሚሽን ወኪል ኃ/የተ/የግል ማህበር በደክላራስዮን ቁጥር C7478 እና C4519 ያሰመጣቸው የገላ ሳሙናወች ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት በተደረገው የላብራቶሪ ፍተሻ (Free Fatty Acid) የደረጃውን መስፈርት እንደማያሟሉ ቢገለጽም ወደ ሀገር እንዲገቡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለአዳማ ቅ/ጽ/ቤት ደብዳቤ የጻፈ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱት ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

83. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 691/2003 አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ያላቸው የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የደረጃውን መስፈርት ማሟላታቸውን በመቆጣጠር ከተዘጋጀላቸው ደረጃ በታች ሆነው በተገኙት ላይ እርምጃ እንደሚወስድ ሥልጣን የተሰጠው ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ እንደተቻለው ከደረጃ በታች ሆነው በተገኙት እርምጃ አልተወሰደም፡፡

84. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ያላቸው የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች በኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት ወይም በዓለም አቀፍ ሶስተኛ ወገን የላብራቶሪ ፍተሻ ታይተው ተፈላጊውን የደረጃ መስፈርት ማሟላታቸውን ተረጋግጦ ዕቃዎቹ የሚፈለገውን ደረጃ ሳያሟሉ ከተገኙ ፈቃድ እስከ መሰረዝ የሚያደርስ እርምጃ እንደሚወሰድባቸው በማሳወቅ በማስጠንቀቂያ እንዲለቀቁ እየፈቀደ መሆኑና በፍተሻ ውጤቱ ደረጃቸውን ያላሟሉትን ገበያ ላይ ለተጠቃሚ መድረሳቸው ቢታውቅም እርምጃ እየወሰደ አለመሆኑ በኦዲቱ ከተሰበሰቡ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡ (አባሪ 3) ተያይዟል፡፡

85. በናሙና በታዩ ቅ/ጽ ቤቶች አዳማ፣ አዋሣ፣ ሞጆ ተወካይ፣ ሞያሌ ፣ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት/ እንዲሁም ባለድርሻ አካላት /የኢትዮጵያ ተስማሚነት ድርጅት፣ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣ አስመጪዎች ያስመጧቸው የተለያዩ የገቢ ዕቃዎች በሚ/ር መ/ቤቱ ናሙና ተወስዶ በኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት በላብራቶሪ ተፈትሾ ውጤታቸው ሳይታወቅ ያስገቧቸው ዕቃዎች አገልግሎት ላይ ማዋላቸውን ሚ/ር መ/ቤቱ እያወቀ ምንም እርምጃ ያልወሰደና ዕቃዎቹ እንዲለቀቁ ሰነድ እንዲበተንላቸው ያደረገ መሆኑን በኦዲተ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡ በመሆኑም ማኒስቴር መ/ቤቱም የካቲት 12/2006 በደብዳቤ ቁጥር 01-1-34/0880 ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣ ሚያዝያ 17/2006 ዓ.ም. በደብዳቤ ቁጥር 011-34/1356፣ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ለሞጆ ደረቅ ወደብ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት፣ እና መጋቢት 24/2006 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 01-1-34/1133 ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት እና ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እንደቅደም ተከተላቸው ሰነዱ እንዲበተንላቸው የፈቀደላቸው መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

86. ትሬድ ሊንክ ኃ/የተ/የግል ማህበር በዲክላራስዮን ቁጥር C-5978; C-7836; C-12251; C-1082 ከውጪ ያስመጧቸው ጊቨ የገላ ሣሙና የጥራት ደረጃቸው በኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት ሳይረጋገጥና ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሳያሳውቁና ሙሉ የመልቀቂያ ፈቃድ ከሚ/ር መ/ቤቱ ሳያገኙ ሽያጭ ካዋሏቸው በኋላ ሚ/ር መ/ቤቱ እርምጃ ያልተወሰደና ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን መ/ቤት ለሞጆ ደረቅ ወደብ ጉምሩክ ቅጽ/ቤት በደብዳቤ ሰነድ እንዲበተንላቸው የተፈቀደ መሆኑ ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

87. በመሆኑም በ01/11/2005 በቁጥር ንሚ/አአከ/0305/05 30፣ በ16/011/05 በቁጥር ንሚ/አአኮ/0324/05 32፣ በ22/05/05 በቁጥር ንሚ/አአኮ/0241/05 27፣ በ15/01/06 በቁጥር ንሚ/አአኮ/0351/06 43፣ በ23/01/06 በቁጥር ንሚ/አአኮ/0387/06 28፣ በጠቅላላው 160 ሚትሪክ ቶን የአርማታ ብረት አስመጪዎች ደረጃውን ያልጠበቀ የአርማታ ብረት እንዳስገቡ፣ እንዲሁም በ11/04/2006 በቁጥር ንሚ/አአኮ/ 0393/06 10፣ በ09/11/05 በቁጥር ንሚ/አአኮ/0319/05 6፣ በ26/06/06 በቁጥር ንሚ/አአኮ/233/06 19፣ በ11/07/2005 በቁጥር ንሚ/አአኮ/0268/05 7 በጠቅላላው 42 የኬሚካል ውጤቶች /የልብስ ሣሙና፣ የገላ ሳሙናና የዱቄት ሳሙና በላብራቶሪ የፍተሻ ውጤት ደረጃቸውን ያልጠበቁ መሆኑን መረጋገጡን ከላይ በተገለፀው ቀንና ቁጥር በኮሜት ተወካይ ጽ/ቤት ለንግድ ሚኒስቴር የገቢና ወጪ ዕቃዎች ጥራት ቁጥጥር ለገሐር ቅ/ጽ/ቤት ቢገለጽም የንግድ ሚኒስቴር በአስመጪዎች ላይ ምንም እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑን በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

88. ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ከሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ጋር ባደረገው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ተፈላጊውን የደረጃ መስፈርት የማያሟሉ የንግድ ዕቃዎች እንዲለቀቁ የሚደረጉ መሆኑ፣ ይህም የሚሆንበት በበላይ ኃላፊዎች ውሳኔ እና የመፈተሻ የላብራቶሪ አቅም ማነስ ምክንያት ሳይፈተሹ የሚለቀቁ ሲሆን እንዲለቀቁም በአመራሩ ደብዳቤ እንዲፃፍ የሚታዘዝ በመሆኑ ለሚመለከታቸው ክፍሎች ይለቀቅላቸው የሚል ደብዳቤ የሚጻፍ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

89. እንዲሁም ምርቶች የጥራት ደረጃቸው ሳይታወቅ በውዴታ ግዴታ ጥራት ደረጃ ሳይገለጽ በጊዜያዊ መልቀቂያ ተለቆ ሙሉ መልቀቂያ ተሰጥቶቸው ውጭ ምንዛሪ ማወራረድ ሳይችሉ ሲቀር ቀጣይ የንግድ ስራቸውን ማከናወን ስለማይችሉ፤ ይህ ደግሞ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የቁጥጥር ስርዓት አሉታዊ ተጽዕኖ ከማሳደሩም በላይ የንግድ ሂደቱን በማስተጓጎል የገበያ ክፍተት ስለሚፈጥር ችግሩን ለመፍታት በደብዳቤ ሰነድ እንዲበተን ይደረጋል፡፡ ምርቶች ከጉምሩክ ግቢ ከወጡ በኋላ ከደረጃ በታች ሆነው በተገኙ ላይ እርምጃ የሚያስወስድ የህግ ማዕቀፍ የሌለ መሆኑ፣ በአዋጁ ላይ ማገድ እንዳለበት እንጂ መክሰስ፣ መቅጣትና ማስወገድ

እንዳለበት የሌለ በመሆኑ ከጉምሩክ ጣቢያ እንዲወጣ ብቻ የሚደረግ ነው፡፡ ይህንንም ለማስራት የማስፈጸሚያ ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ያልጸደቀ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

90. በመሆኑም ተፈላጊውን የደረጃ መስፈርት የማያሟሉ የገቢና ወጪ ንግድ ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም ከሀገር እንዳይወጡ እንዲታገዱና እርምጃ እንዲወሰድ በአዋጅ ቁጥር 691/2003 የተደነገገ ሲሆን በዚሁ መሠረት በላብራቶሪ ፍተሻ የጥራት ደረጃቸው ተጣርቶ ደረጃቸውን የማያሟሉ የገቢና ወጪ ዕቃዎች መኖራቸው ቢረጋገጥም ሚ/ር መ/ቤቱ በህጉ መሠረት ተገብውን እርምጃ በሚያዘውና በተሟላ መልኩ ባለመውሰዱ ደረጃቸውን ያልጠበቁ ምርቶች ለህብረተሰቡ እንዲደርሱና የህብረተሰቡን ጤናና ደህንነት ከመጉዳት ባለፈ የገበያ ውድድርን በማዛባትና ሸማቾች ለሚከፍሏቸው ዋጋዎች ተመጣጣኝ የሆኑ ምርቶችና አገልግሎቶችን እንዳያገኙ ያደርጋል፡፡

**የደንበኞችን የላብራቶሪ የፍተሻ ውጤት መገለጽ ባለበት ጊዜና ሰዓት ማሳወቁንና ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን፣ ናሙናዎች ከተወሰዱበት ሰዓት ጀምሮ በ48 ሰዓት ላብራቶሪ እንዲቀርቡ ማድረጉን በተመለከተ፣**

91. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት የደንበኞችን የላብራቶሪ የፍተሻ ውጤት መገለጽ ባለበት ጊዜና ሰዓት ማሳወቁን ሊከታተልና ሊቆጣጠር እንዲሁም አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ በሚያዘው መሰረት የተወሰዱ ናሙናዎች ከውጫዊ ተፅዕኖ ነጻ ሆነው የጥራት ባህሪያቸው ሳይለወጥ ከተወሰዱበት ሰዓት ጀምሮ በ48 ሰዓት ለፍተሻ ላብራቶሪ እንዲቀርቡ ሊያደርግ ይገባል፡፡

92. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት የደንበኞችን የላብራቶሪ የፍተሻ ውጤት መገለጽ ባለበት ጊዜና ሰዓት ማሳወቁን ሊከታተልና ሊቆጣጠር የሚገባ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ እንደተቻለው ይህንን ጉዳይ ተግባራዊ አላደረገም፡፡

93. የኦዲት ቡድኑ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት የደንበኞችን የላብራቶሪ የፍተሻ ውጤት መገለጽ ባለበት ጊዜና ሰዓት ለምን እንደማያሳውቅ ለመረዳት እንደተቻለው የላብራቶሪ ውጤት መዘግየት ድርጅቱ ዋና ዋና ችግሮች የሚላቸው የላብራቶሪ ምርመራ ፈላጊዎች ቁጥር መብዛትና የላብራቶሪ ዕቃ መፈተሻ እጥረት መኖር፣ በሙያው የሰለጠነ የሰው ኃይል አለመኖር፣ በሥራ ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ እያሳደረ መሆኑን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ለበላይ አመራር በተደጋጋሚ መፍትሄ እንዲያገኝ ጥያቄ ቢቀርብም ችግሩ ሊቀረፍ ያልተቻለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

94. በመሆኑም የሞያሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ለተስማሚነትና ምዘና ድርጅት ለናሙናዎች አስቸኳይ የፍተሻ አገልግሎት ክፍያ ተከፍሎ መገለጽ ባለበት ጊዜና ሰዓት ውጤት የማያሳውቃቸው

መሆኑን እና እንዲሁም በደሴ ቅ/ጽ/ቤት በላብራቶሪ ውጤት መዘግየት ምክንያት በጊዜያዊ መልቀቂያ መጠናቸው 252969 MT የሚጠጋ የመዋቢያ ሳሙና የኢትዮጵያን አስገዳጅ ደረጃ ሳያሟሉ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በመፍቀዱ የተለቀቁ መሆኑ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ሰነዶችና ቃለመጠይቆች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

95. ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ለኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት የሥራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ሲመልሱ ውጤት የሚዘገይበት ምክንያት በመፈተሻ ማቴሪያል እጥረት፣ በፈታሽ ባለሙያና የክህሎት አቅም ችግር መሆኑ፣ በአሁኑም አሠራር ከ4-5 የሚሆኑ ዕቃዎች እንደሚዘገዩ ለምሣሌ ውሃ የውጭ ምንዛሬ ስለሚፈልግ ምንዛሬውን ለማግኘት እስከ 8 ወር ስለሚፈጅ ተፈትሾ እስከሚመጣ ድረስ የሚቆይ መሆኑ፣ ከመቀሌ የሚመጡ ናሙናዎች በዲኤች ኤል የሚላኩ ስለሆነ ድርጅቱ ፈትሾ እስከሚልክ የመዘግየት ሁኔታ መኖሩን እንዲሁም በአሁኑ ወቅት ኃይል ቆጣቢ አምፖሎችን ለፍተሻ ሲቀርቡ አብሮ መላክ ያለባቸው ሠነዶች/ማስረጃዎች ተሟልተው ባለመቅረባቸው መጓተት መኖሩን የሥራ ኃላፊው ገልጸዋል፡፡

96. በሌላ መልኩ አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ በሚያዘው መሰረት የተወሰዱ ናሙናዎች ከውጫዊ ተፅኖ ነጻ ሆነው የጥራት ባህሪያቸው ሳይለወጥ ከተወሰዱበት ሰዓት ጀምሮ በ48 ሰዓት ለፍተሻ ላብራቶሪ መድረስ ያለባቸው ቢሆንም የኦዲት ቡድኑ በናሙና ባያቸው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ናሙናዎች ከተወሰዱበት ሰዓት ጀምሮ በ48 ሰዓት ለፍተሻ ሳይቀርቡ እስከ አንድ ሳምንት ድረስ የሚቆዩ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

97. ናሙያዎች ከተወሰዱ በኋላ ለምን በተቀመጠው ጊዜ ወደ ላብራቶሪ እንደማይደርሱ አስመልክቶ የኦዲቱ ቡድኑ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ሲመልሱ በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት እንደ ብረት ዓይነቶች በአፈርና በዝናብ የዝገት ችግር የሚፈጠር እና የቦታ ጥበት ችግር የሚያጋጥም በመሆኑ ለዚህ ችግር እንደ ምክንያት የሆነው የላብራቶሪ ፍተሻ የሚያስፈልጋቸውን ናሙና በወቅቱ በማውጣት አዲስ አበባ ወደሚገኘው የኢትዮያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት ላብራቶሪ ለመላክ ዝግጁ ለማድረግ በተደጋጋሚ በሚያጋጥም የሥራ ማስኬጃ ቶሎ አለመለቀቅ ችግር፣ የነዳጅ ፍጆታ ከፍተኛ መሆን የተሽከርካሪ አለመኖር መሆኑን በቃለ መጠይቅ የስራ ኃላፊዎቹ ገልጸዋል፡፡

98. የሞያሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች እንደገለጹት እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለሥራ ማከናወኛ ተሽከርካሪ ባለመኖሩና የተስማሚነት ምዘና ድርጅት በአካባቢው ባለመኖሩ የህዝብ ማመላለሻ ትራንስፖርት የሚጠቀሙ በመሆኑ ናሙናዎቹ ሳይላኩ ለሳምንታትና ለወራት በእጃቸው እንደሚቆዩ ገልፀው ይህም ደንበኞች ለእንግልትና ለተለያዩ ከፍተኛ አላስፈላጊ

ወጪዎች መዳረጋቸውና ቅሬታ እያስነሣ የሚገኝ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በአዳማ፣ በድሬዳዋ፣ በደሴ፣ በትግራይና የሞያሌ ቅ/ጽ/ቤቶች በትራንስፖርት ችግር ናሙናዎች በተገቢው ቀንና ሰዓት /በ48/ ሰዓት ለላቦራቶሪ ፍተሻ እንደማይደርሱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

99. ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ከሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ጋር ባደረገው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ይህ የሆነበት ምክንያት የላብራቶሪ የአቅም ውስንነት መኖሩ፣ የሰው ኃይል ማነስ እና ድርጅቱ ቃል በገባው መሠረት የማይፈጽምና ስራውን ሲጨርስ ባለማሳወቁ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

100. እንዲሁም ናሙናዎች ከውጫዊ ተፅዕኖ ነጻ ሆነው የጥራት ባህሪያቸው ሳይለወጥ ከተወሰዱበት ሰዓት ጀምሮ በ48 ሰዓት ለፍተሻ ላብራቷር የማይቀርቡ መሆኑ፣ ለዚህም ምክንያቱ የተሽከርካሪ ችግር፣ የፒቲ ካሽ በወቅቱ አለመላክና ማነስ ችግር መሆኑን የስራ ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

101. በመሆኑም የተስማሚነት ምዘና ድርጅት የደንበኞችን የላብራቶሪ የፍተሻ ውጤት መገለጽ ባለበት ጊዜና ሰዓት ማሳወቁን ክትትልና ቁጥጥር ባለመደረጉ የናሙና ውጤት መዘግየት ችግር በደንበኞች ላይ ቅሬታ እንዲያሳድር ማድረጉ፣ ደንበኞች ለተጨማሪ የመጋዘን ኪራይ ወጪ እንዲከፍሉና ምርቱ ለተጠቃሚው ወቅቱን ጠብቆ እንዳይደርስ አድርጓል፡፡ እንዲሁም ናሙናዎች ከውጫዊ ተፅኖ ነጻ ሆነው የጥራት ባህሪያቸው ሳይለወጥ ከተወሰዱበት ሰዓት ጀምሮ በ48 ሰዓት ለፍተሻ ላብራቶሪ እንዲቀርቡ ባለመደረጉ እንደ ብረት ዓይነቶች በአፈርና በዝናብ የዝገት ችግር መፍጠሩ፣ የቦታ ጥበት ችግር እንዲኖርና ደንበኞች ለተለያዩ አለአስፈላጊ ወጪዎች እንዲዳረጉና ቅሬታ እንዲያስነሳ ያደርጋል፡፡

**ምርትን ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገቡ አስመጪዎች አለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው የላብራቶሪ ሰርተፊኬት እንዲያቀርቡ ማድረጉንና፣ የሦስተኛ ወገን ሰርተፊኬት ያላቀረቡ አስመጪዎች የላብረቶሪ ውጤት እስከሚገለጽ ድረስ በጉምሩክ እንዲጠብቁ ማድረጉን በተመለከተ፣**

102. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ምርትን ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገቡ አስመጪዎች አሰገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ያላቸው ምርቶች አለም አቀፍ ተቀባይነት ባላቸው ኢንስፔክሽን አካላት የተረጋገጠ የላብራቶሪ ሰርተፊኬት ከአገልግሎት መጠየቂያ ጋር እንዲያቀርቡ ሊያደርግ፣ የሰርተፊኬቱ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ (Rondomly) አንድ ሶስተኛ ወካይ ናሙና ወስዶ ሰርተፊኬቱን ሊያረጋግጥና የሦስተኛ ወገን ሰርተፊኬት ማቅረብ ግዴታ መሆኑ ከሁለት ጊዜ በላይ ተነግሯቸው ሰርተፊኬት ማቅረብ ያልቻሉ አስመጪዎች ምርታቸው የደረጃ መስፈርት ማሟላቱ የላብረቶሪ ውጤት እስከሚገለጽ ድረስ በጉምሩክ እንዲጠብቁ ሊደረግ ይገባል፡፡

103. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ህዳር 2/2006 ዓ.ም. ለቅ/ጽ/ቤቶች በፃፈው ደብዳቤ አሰገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ያላቸው ምርቶች ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገቡ አስመጪዎች አለም አቀፍ ተቀባይነት ባላቸው ኢንስፔክሽ አካላት የተረጋገጠ የላብራቶሪ ሰርተፊኬት ከአገልግሎት መጠየቂያ ጋር እንዲቀርቡ በማድረግና የሦስተኛ ወገን ሰርተፊኬት ማቅረብ ግዴታ መሆኑ ከሁለት ጊዜ በላይ ተነግሯቸው ሰርተፊኬት ማቅረብ ያልቻሉ አስመጪዎች ምርታቸው የደረጃ መስፈርት ማሟላቱ የላብረቶሪ ውጤት እስከሚገለጽ ድረስ በጉምሩክ እንዲጠብቅ መደረግ ያለበት ቢሆንም ነገር ግን አንዳንድ ተገልጋዮች ከውጭ ለሚያስመጡት ዕቃ የሶስተኛ ወገን ሠርተፊኬት ሳያቀርቡ በነበረው አሰራር /በውዴታ ግዴታ/ እና የላብራቶሪ ውጤት ሳይገለጽ ምርቶች እየተለቀቁ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

104. ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ከሞያሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊዎች ጋር ባካሄደው ቃለ መጠይቅ ሲመልሱ የሞያሌ የውሀ ፓምፖች የሶስተኛ ወገን ሰርተፊኬት ከአገልግሎት መጠየቂያ ጋር እንዲያቀርቡና የሰርተፊኬቱ ትክክለኛነት በኢሜል በማረጋገጥ የሚስተናገዱበት ሁኔታ መኖሩን ቢገልጹም፣ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተገኝቶ በተከለሰ ማስረጃ ብዙ አስመጪዎች መጠናቸው ብዙ የሆኑ የውሃ ፓምፖች የሶስተኛ ወገን ማምጣት ሲኖርባቸው ሳያመጡና በተስማሚነት ምዘና ድርጅት ተፈትሸው ሳይረጋገጡ የሚለቀቁ መሆኑ ታውቋል፡፡

105. እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት ሷሊሃ አሊ መሀመድ የህንፃ መሣሪያ አስመጪ135 የውሃ ፖምፖች የSGS ሠርተፊኬት ማቅረብ አለመቻላቸውን በጥር 15 ቀን 2007 አመልክተው18 ጥር/2007 በቁጥር 1.1.34/4044 በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በተጻፈ ደብዳቤ በውዴታ ግዴታ እንዲለቀቁ መደረጉን ለማወቅ ተችሏል፡፡

106. በተመሳሳይ መልኩ ሚፍታህ አብዶ አስመጪ160 የውሃ ፓምፖች የSGS ሠርተፊኬት ማቅረብ አለመቻላቸውን በጥር 8 ቀን 2007 አመልክተው ጥር 15/2007 በቁጥር 01-1-34/4026 ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ደብዳቤ በመጻፍ እንዲለቀቁ የተደረገ መሆኑ ለመረዳት ተችሏል፡፡

107. ፋሲል ክፍለ እየሱስ ኃይሌ /አይዞን ትሬዲንግ ካምፓኒ/ ቆርቆሮ በ27/10/2006 እንዲለቀቅላቸው አመልክተው በሐምሌ 22 ቀን 2006 በቁጥር 01.1.34/2364 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለኮሜት ተወካይ ጽ/ቤት በመጻፍ በውዴታ ግዴታ እቃዎቹ የተለቀቁ መሆኑ፣

108. የኢትዮጵያ የሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት13400 ካርቶን የገላ ሳሙና ጥር 26/2006 ዓ.ም እንዲለቀቅላቸው አመልክተው የሶስተኛ ሠርተፊኬት ሳያቀርቡና የላብራቶሪ

ምርመራ ሳይካሄድ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በ27/05/2006 እንዲለቀቅላቸው ለኮሚት ተወካይ ጽ/ቤት የጻፈላቸውና የተለቀቁ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

109. ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ከሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ጋር ባደረገው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የሶስተኛ ወገን ሰርተፊኬት አሰራር ከተጀመረ በኋላ የተለቀቁ ዕቃዎች መኖራቸውን ገልጸው፣ ይህም የሚሆንበት ምክንያት ዕቃዎች የሶስተኛ ወገን ከተጀመረ በኋላ እንዲለቀቁ በበላይ አመራር ውሳኔ የሚለቀቅበት ሁኔታ መኖሩ እና የውሃ ፓምኘን በተመለከተ በአዳማ፣ ሞጆ ደረቅ ወደብ እና በኮሜት ተወካይ ጽ/ቤት ከውሃ ፓምፕ ውጭ የሚለቀቅ ውጪ የሚለቀቅ አለመኖሩን ገልጸዋል፡፡

110. ይሁን እንጂ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በረቂቅ ሪፖርት ላይ በሰጡት መልስ የላብራቶሪ ፍተሻ አገልግሎት ተጠቅመው በአጭር ጊዜ ምርቶቻቸውን የጥራት ደረጃዎችን አሟልተው የሚለቀቁበት ሁኔታ በሌለበት፣ ቀጣይና ጠንካራ እርምጃዎች ሊወሰድ በማይቻልበት ሁኔታ አስመጪዎች የሶስተኛ ወገን ሰርተፊኬት ማቅረብ ግዴታ መሆኑን በማስገንዘብ በማስጠንቀቂያ ምርቶቹ በጊዜያዊ መልቀቂያ የሚለቀቁበት ሁኔታ ከቀድሞ ጥራትና ደረጃዎች ባለስልጣን ጀምሮ ይሰራበት የነበረ መሆኑን በመግለጽ ሆኖም ግን ይህ አሰራር ክፍተት በመፍጠሩ ከህዳር 2006 ዓ.ም ጀምሮ እንዲቆም መደረጉን ቢገለጽም ይህ አሰራር ስራ ላይ ከዋለም በኋላ ምርቶቹ እንደሚለቀቁ ከላይ በፓራግራፍ ከ106 እስከ 109 የተጠቀሱ ገቢ ምርቶች የተለቀቁ መሆኑ እንዲሁም በአባሪ 2 ላይ በዝርዝር በተመለከተው መሠረት ተግባራዊ አለመሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

111. በመሆኑም ምርትን ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገቡ አስመጪዎች አሰገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ያላቸው ምርቶች አለም አቀፍ ተቀባይነት ባላቸው ኢንስፔክሽን አካላት የተረጋገጠ የላብራቶሪ ሰርተፊኬት እንዲያቀርቡና ሰርተፊኬቱን ማቅረብ ያልቻሉ አስመጪዎች የላብራቶሪ ውጤት እስከሚገለጽ ድረስ በጉምሩክ እንዲጠብቁ በአለመደረጉ ደረጃቸውን ያልጠበቁ ምርቶች ተለቀው በህብረተሰቡ ጤና ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡

**ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሀገሪቱን የስነ ልክ ሥርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን ቁጥጥር ማድረጉን፣ የመለኪያ መሣሪያዎች በክልል ንግድ ቢሮዎችና በፌዴራል ተጠናክረው መሥራታቸውን የሚያረጋግጥ መሆኑን በተመለከተ፣**

112. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሀገሪቱን የስነ ልክ ሥርዓት ሊዘረጋ፣ መተግበሩን ሊቆጣጠር እና የመለኪያ መሣሪያዎች የትክክለኛነት ሥራዎች በክልል ንግድ ቢሮዎችና በፌዴራል

ተጠናክረው መሥራታቸውን የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

113. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሀገሪቱን የስነ ልክ ስርዓት እንዲዘረጋና ተግባረዊ መደረጉን እንዲቆጣጠር በአዋጅ ቁጥር 691/2003 ስልጣን የተሰጠው ቢሆንም መ/ቤቱ የዘረጋው የሀገሪቱን የስነ ልክ ስርዓት በክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች ቢከናወንም ሸማቹ ኅብረተሰብ በተሻለ ሁኔታ ጥቅሙ እንዲጠበቅና አፈጻጸሙ ውጤታማ እንደሚሆን በማሰብ ለክልሎች ውክልና የሰጠ ቢሆንም ተግባራዊ መደረጉን ተገቢውን ቁጥጥር እያደረገ አይደለም፡፡

114. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት ንግድ ቢሮዎች ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሀዋሳ ከተማ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ በ2007 በጀት አመት አንድ ጊዜ ብቻ ውይይት ከማድረግ ውጪ የስነ ልክ ሥራ አፈጻጸሙን ውጤታማ ሊያደርግ የሚያስችል ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር እንዲሁም የድጋፍ ስራዎች ያልተከናወኑ መሆኑ ታውቋል፡፡

115. የአዲስ አበባ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ሚ/ር መቤቱ በዘረጋው የሀገሪቱ የስነ ልክ ስርዓት መሰረት በንግድ ቢሮው ተግባራዊ መደረጉን ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር የማያደርግና የስራ ግኑኙነት በሚ/ር መ/ቤቱና በንግድ ቢሮው ኬዝ ቲም ጋር ቀጥተኛ ግኑኙነት ስለሌለ በስራ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በግብረ መልስ በቼክ ሊስት ተደግፈው ያልተሰሩ በመሆኑ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ወጥነት ባለው መልኩ ለመፍታት አለመቻሉ እና የሚፈጠሩ የአሰራር ችግሮችን አስቸኳይ መፍትሄ ሊያገኙ ባለመቻላቸው ስራዎቹ በተያዘላቸው ዕቅድና ፕሮግራም መሰረት እንዳይከናወኑ ማድረጉንና በተጨማሪም የሚ/ር መ/ቤቱና ንግድ ቢሮው ተግባርና ኃላፊነት በአግባቡ ተለይቶ እንዳይታወቅ ማድረጉን የስራ ኃላፊ ለአዲት ቡድኑ ገልጸዋል፡፡

116. በኦሮሚያ ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ ሚ/ር መ/ቤቱ ክትትልና ድጋፍ የሚያደርግባቸው በየጊዜው የሚላኩ የዕቅድ ክንውን ሪፖርቶች የተለያዩ ዓውደ ጥናቶች ስልጠናዎች በሚሰጥበት ወቅት እንደዚሁም የሚዛን መስፈሪያ መሳሪያዎች ርክክብ በመሆኑ በስራው ዙሪያ የሚያጋጥሙ ችግሮችና መፈትሂዎች ላይ በመወያየት የመፍትሔ አቅጣጫ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ማስቀመጥ ባለመቻሉ መሠራት ያለበት የስነ ልክ ሥራ በተፈለገው መጠን አለመሠራቱን ጉዳዩ የሚመለከታቸ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ አስረድተዋል፡፡

117. የኦዲት ቡድኑ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለክልል ቢሮዎች ተገቢውን ድጋፍ መስጠቱን አስመልክቶ ለሀዋሳ ከተማ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ኃላፊ ላደረገው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአካል በመገኘት ሥራው ስለመሠራቱ የማያረጋግጥ

በመሆኑ በክልል የሚገኙ አመራሮች ለተግባሩ ተገቢውን ትኩረት እንዳይሰጡ ማድረጉና ከውጭ ሀገር የሚገቡና ከፍተኛ ችግር ያለባቸው ሚዛኖች ትኩረት እንዳይሰጣቸው ማድረጉ፣ የህግ ማዕቀፎች እንዲጸድቁ አለመደረጉ እና ምርመራ የሚያኪሄዱ ባለሙያዎች የሚደገፉበት ሁኔታ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሌለው በመሆኑ በየክልሎች የሚገኙ የመለኪያ መሣሪያዎች ወቅቱን ጠብቀው ትክክለኛነታቸ እንዳይረጋገጥ ማድረጉን የስራ ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

118. በተመሳሳይ መልኩ የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ የመለኪያ መሳሪያዎች የትክክለኛነት የማረጋገጥ በተመለከተ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በተጨባጭ የሚደረግ የክትትል ስራ አለመኖሩን ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን ንግድ ቢሮው ከወረዳ ጀምሮ እስከ ማዕከል ባሉ የስነ ልክ መዋቅሮች አመታዊ የመለኪያ መሳሪያዎች ትክክለኛነት የማረጋገጥ እንደሚሰራ ገልጸዋል፡፡ ይሁን እንጂ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ስራዎች መሰራታቸውን የሚከታተልበትና ክፍተቶችንና ጥንካሬዎች የሚያሳውቅበት አሰራር ባለመኖሩ ክፍተቶችን ለማየት እንዳይቻል ማድረጉን ለኦዲት ቡድኑ በቃለ መጠይቅ አስረድተዋል፡፡

119. በኦሮሚያ ክልል የንግድና ገበያ ልማት ቢሮ የመለኪያ መሳሪያዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ እስከ ወረዳ ድረስ መዋቅር ተዘርግቶ እየተሰራ የሚገኝ ሲሆን፣ በዚህ ዙሪያ ያጋጠሙ ችግሮች መሳሪያዎች በሁሉም ወረዳዎች በበቂ ሁኔታ ድጋፍ ባለመደረጉ ስራው በሚፈለገው መጠን እንዳይሄድ ማድረጉን ስራ ኃላፊዎች በቃለ መጠይቅ አስረድተዋል፡፡

120. ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ከሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ጋር ባደረገው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ሚ/ር መ/ቤቱ ድጋፍ የሚያደርግ ሲሆን ነገር ግን ድጋፍ አልተደረገም ለሚለው ከሚገባው በላይ መደረጉንና የአሰልጣኞችን ስልጠና አቅም በፈቀደ ሁሉ መሰጠቱን ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም የመቆጣጠሪያ ስታንዳርዶች ተገዝተው ለዘጠኙ ክልሎችና ለሁለት ከተማ አስተዳደሮች የተሰራጨ መሆኑ፣ ክልሎች ፍላጐታቸውን ካልጠየቁ ማወቅ የማይቻል መሆኑን ገልፀዋል፡፡

121. እንዲሁም ሀዋሳ ላይ ብሄራዊ ስነ ልክ ኢንስቲትዩት ካሊብሬሽን አገልግሎት የሚሰጥ መሆኑ፣ ክልሎችም የመቆጣጠሪያ ስታንዳርዶች ካሊቢሬት እንዲያስደርጉ ድጋፍ ያደርጋል፡፡ ነገር ግን ክልሎች ሳይጠይቁ የት እንደሚሰራ ማወቅ ስለማይቻል ድጋፍ ማድረግ አይቻልም፡፡ በደብዳቤ ሲገልጹ ድጋፍ ይደረጋል፡፡ ሆኖም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስራ ከጀመረ ጀምሮ የካሊብሬሽን ድጋፍ የጠየቀ ክልል የሌለ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

122. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሀገሪቱን የስነ ልክ ሥርዓት ዘርግቶ በዚያ መሰረት ተግባራዊ መደረጉን ተገቢውን ክትትል ባለማድረጉና እንዲሁም የመለኪያ መሣሪያዎች የትክክለኛነት ሥራዎች በክልል ንግድ ቢሮዎችና በፌዴራል ተጠናክረው መሥራታቸውን የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ባለመኖሩ የስነ ልክ ስራዎች በተያዘላቸው ዕቅድና ፕሮግራም መሰረት ደረጃቸውን በጠበቀ መልኩ ስለመከናወናቸው ለማረጋገጥ ካለማስቻሉም በላይ በአሰራር ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችንት ወጥነት ባለው መልኩ ለመፍታት እንዳይቻል አድርጓል፡፡

**የመለኪያ መሣሪያዎች ወደ ገበያ ከመግባታቸው በፊት ደረጃቸውን የጠበቁ መሆኑን ማረጋገጡን በተመለከተ፣**

123. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከውጭ ሀገር የሚገቡ የመለኪያ መሣሪያዎች ወደ ገበያ ከመግባታቸው በፊት ደረጃቸውን የጠበቁ መሆኑን ሊያረጋገጥ ይገባል፡፡

124. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከውጭ የሚገቡ የመለኪያ መሳሪያዎች ወደ ገበያ ከመግባታቸው በፊት ደረጃቸውን የጠበቁ መሆኑ የመለኪያ መሣሪያዎች የትክክለኛነት ማረጋገጫ ቬሪፋይ ሳይደረጉ በጊዜያዊ መልቀቂያ የሚለቀቁና በክልሎችም የመለኪያ መሳሪያዎቹ ወደ ገበያ ከመግባታቸው በፊት ደረጃቸውን የጠበቁ መሆኑን የማይረጋገጥ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ጉዳዩን አስመልክቶ ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ጋር ከተካሄዱ ቃለ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

125. በመሆኑም ሁሉም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የመለኪያ መሳሪያዎች አስመጪዎች የትክክለኛነት ማረጋገጫ እንዲሰጣቸው ለሚ/ር መ/ቤቱ የአገልግሎት ጥያቄ በደብዳቤ ቢያቀርቡም ሚ/ር መ/ቤቱ ከ 39 አመት በፊት ይሰራበት በነበረው አሰራር የመለኪያ መሳሪያዎቹን ትክክለኛነት ሳያረጋግጥ በህግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 431/1968 ዓ.ም የሚዛንና መስፈሪያ ደንብ ቁጥር 5 መሰረት የትክክለኛነት ማረጋገጫ ሳይሰጣቸው በውዴታ ግዴታ እንዲለቀቁ እንደሚደረግ ታውቋል፡፡

126. በኦዲቱ በናሙና በታዩ ንግድ ቢሮዎች የሀዋሳ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ እና የኦሮሚያ የንግድና ገበያ ልማት የመለኪያ መሳሪያዎች ወደ ገበያ ከመግባታቸው በፊት ደረጃቸው የጠበቁ መሆኑን የማያረጋግጡ መሆኑና ነገር ግን ገበያ ላይ የገቡትን የሚከታተሉ መሆናቸው የስራ ኃላፊዎቹ ለኦዲት ቡድኑ ገልጸዋል፡፡

127. በተመሳሳይ መልኩ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩ አስመልክቶ ቃለ መጠይቅ ካቀረበላቸው የአዲስ አበባ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮም የመለኪያ መሳሪያዎች ወደ ገበያ ከመግባታቸው በፊት

ደረጃ የጠበቁ መሆኑን ማረጋገጥ ስራው የንግድ ቢሮው መሆኑ ንግድ ሚኒስቴር ባለማሳወቁ እየተሰራ አለመሆኑ፣ የስራ ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

128. ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ከሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ጋር ባደረገው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የመለኪያ መሳሪያዎቹ ወደ ሀገር ሲገቡ በውጤታ ግዴታ እንዲለቀቁ የሚደረግ መሆኑ፣ ዕቃዎቹ ወደ ገበያ ከመግባታቸው በፊት በገቡት ውል መሠረት መጋዘኖቻቸው ድረስ በመሄድ ቬሪፋይ የሚደረግ መሆኑ፣ ይህም በጉምሩክ ግቢ ውስጥ ቬሪፋይ ለማድረግ ከቦታው ጥበትና ከተለያዩ የአከባቢ ሁኔዎች አንጻር ምቹ ባለመሆኑ ነው፡፡ ደንቡን ለማሻሻል አዋጅ ተረቆ ተዘጋጅቷል የቀድሞው ደንብ ከሚሸፍናቸው የመለኪያ መሳሪያዎች ውስንነት በስተቀር መሰረታዊ የህጋዊ ስነ ልክ መርሆች የተከተለ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

129. እንዲሁም የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በረቂቅ ሪፖርት ላይ በሰጡት መልስ አሰገዳጅ ደረጃ ያላቸው ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የመለኪያ መሳሪያዎች ትክክለኛነት ሳይረጋገጥ ወደ ገበያ የሚገቡበት አሰራር የሌለ መሆና በመለኪያ መሳሪያዎቹ ባህሪ እና ማሟላት የሚገባቸው ቅድመ ቬሪፊኬሽን የአከባቢ ሁኔታ አስቸጋሪነት በልኬት ላይ የሚመጣውን መዛባት ለመቅረፍ ለልኬት ምቹ ሁኔታ ባለበት በደንብ ቁጥር 431/1965 የሚዛንና መስፈርያ ደንብ አንቀጽ መሰረት በአስመጪው መጋዘን ወይም በሚኒስቴር መ/ቤቱ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በጊዚያዊነት ከጉምሩክ ግቢ እንዲወጡ ተደርጐ ወዲያው ቃል በገቡት መሠረት ቬሪፋይ እንደሚደረግ ቢገልጹም የመለኪያ መሣሪያዎቹ ቬሪፋይ ሳይደረጉ ከ4 ወራት እስከ 22 ወራት እንደሚዘገይ የኦዲት ቡድኑ ባደረገው ዶክሜንት ክለሳ ለማወቅ ተችሏል፡፡

130. በመሆኑም የመለኪያ መሳሪያዎች ወደገበያ ከመግባታቸው በፊት ትክክለኛነታቸው የማይረጋገጥ በመሆኑ ደረጃቸውን ያልጠበቁ የመለኪያ መሳሪያዎች በስፋት ወደ ገበያ እንዲገቡ ያደርጋል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተገልጋዮች ቬሪፊኬሽን ለማስደረግ የክብደት ማነፃፀሪያዎች ወስደው እንዳያዘገዩ ውል በማስገባት መሣሪያዎቹ በወቅቱ እንዲመልሱ ማድረጉን በተመለከተ፣

131. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተገልጋዮች ቬሪፊኬሽን ለማስደረግ የክብደት ማነፃፀሪያዎች ወስደው እንዳያዘገዩ ውል አስገብቶ መሣሪያዎቹ በወቅቱ እንዲመልሱ ሊያደርግ ይገባል፡፡

132. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተገልጋዮች የተሸጋጋሪ ሚዛን (Standard Weight) ክብደት ማነፃፀሪያ ቬሪቪኬሽን ለማስደረግ ወስደው እንዳይዘገዩና በወቅቱ እንዲመልሱ ግዴታቸውን

የሚያሳውቅበት አሰራር ስለሌለው አንዳንድ ተገልጋዮች መሳሪያዎቹን ከወሰዱ በኋላ ለቀጣዩ ተገልጋይ ያለማስረከብና የስራ መጓተት የሚፈጠርበት ሁኔታ መኖርና ችግሩን ለማስተካከልም የተወሰደ እርምጃ እንደሌለ ታውቋል፡፡ እንዲሁም በክልሎች የሚገኙ ዞንና ወረዳዎች የማነጻጸሪያ መሳሪያዎችን ስለማይወስዱ ቢሮ ድረስ በመምጣት ካሊቢሬት የሚያስደረጉ በመሆኑ በወቅቱ ካሊቤሬት አያደርጉም፡፡

133. ይሁን እንጂ በኦዲቱ በናሙና በታዩ የንግድ ቢሮዎች የሀዋሳ ከተማ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ በወቅቱ ቬሪፋይ (ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የመለኪያ መሳሪያዎችን ትክክለኛነት ማረጋገጥ) በማድረግ የሚመለስ እና ችግር ያለባቸውና የማይሰተካከሉትን የሚወርስ ሲሆን ነገር ግን ተገልጋዮች እንዳያዘገዩ ውል የማስገባት ስራ የማያስገቡ መሆኑ፣

134. የኦሮሚያ ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ በክልሉ የሚገኙ ሁሉም ዞኖችና ከተሞች በተመሳሳይ ጊዜ ላይ ቬርፋይ ማስደረግ ላይ የመዘግየት ሁኔታ (1 ዓመትና ከዚያ በላይ የሚቆይ) በመሆኑ በየክልሉ የሚገኙ ሚዛኖች ደረጃቸውን ሳይጠብቁ አገልግሎት የመስጠት ሁኔታዎቸው ከፍተኛ መሆኑንና፣ ተገልጋዮቹ መሳሪያዎች የማይዋሱ በመሆኑ ውል የማስገባት ስራ የማይሰራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

135. ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ከሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ጋር ባደረገው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ክብደት ማነጻጸሪ ቬሪፋይ ለማስደረግ ወስደው በጣሉት ላይ በተለያየ መንገድ እርምጃ ለመውሰድ ሙከራ መደረጉን ገልጸው ይህንንም ለህግ ክፍሉ መተላለፉንና የህግ ክፍሉም መጀመሪያ ርክክብ የተደረገበት ደብዳቤ ተጠይቋል፡፡ ነገር ግን የፊንጫ ስኳር ፋብሪካ ማነፃፀሪያውን የወሰደው ከኢትዮጵያ ቡና ልማት በመሆኑና የኢትዮጵያ ቡና ተክል ልማት በመፍረሱ የድርጅቱ ማስረጃዎች ለባለአደራ ቦርድ በመተላለፉ ማስረጃው ለማቅረብ ያልተቻለና በዚህም ምክንያት ማስከፈል ያልቻሉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

136. ቢሆንም የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ በኃላፊዎች በረቂቅ ሪፖርት በሰጡት መልስ የተሽጋጋሪ ሚዛን ከአንዱ ድርጅት ወደ ሌላ ድርጅት የሚተላለፉበት አሠራር በውል የተደገፈ መሆኑን እንዲሁም የተሽጋጋሪ ሚዛን የክብደት ማነፃፀሪያዎች ቅብብሎሽ በክብደታቸው ምክንያት የአንዱ ተገልጋይ ሥራ ሲያልቅ ወደ ሌላ ድርጅት በደብዳቤ ርክክብ እንደሚደረግ ቢገልፁም በተረካቢውና በሚኒስቴር መ/ቤት መካከል ውል አለመኖሩን በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

137. በመሆኑም ተገልጋዮች ቬሪፊኬሽን ለማስደረግ የክብደት ማነፃፀሪያዎች ወስደው እንዳያዘገዩ ውል አስገብቶ ባለመሰጠቱ የመለኪያ መሳሪያዎቹ በወቅቱ ተመልሰው ለሌላው ተገልጋይ እንዳይጠቀምበትና የመዘግየትና የመጥፋት ሁኔታ እንዲኖር አድርጓል፡፡

**የአውቶ ቦቴ የቬሪፊኬሽን የአገልግሎት ክፍያ ተመን ከሚሰጠው አገልግሎት አንጻር መሆኑን፣ የፈሳሽ ማጓጓዣ ታንከር( ቦቴ) የቬርፊኬሽን ሰርተፊኬት የሚሰጥና ተግባራዊ መደረጉን ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ፣**

138. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአውቶ ቦቴ የቬሪፊኬሽን የአገልግሎት ክፍያ ተመን ከሚሰጠው አገልግሎት አንጻር መሆኑንና የፈሳሽ ማጓጓዣ ታንከር( ቦቴ) ይዘት የመለኪያ መሳሪያ ከተገጠመለት በኋላ የመሳሪያውን ትክክለኛነት በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ውስጥ መሆኑን በማረጋገጥ ለሶስት ዓመት የሚያገለግል የቬርፊኬሽን ሰርተፊኬት ሊሰጥና በተሰጠው መሰረት ተግባራዊ መደረጉን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

139. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአውቶ ቦቴ ቬርፊኬሽን የአገልግሎት ክፍያ ዋጋው በ1966 ዓ.ም የሚዛንና መስፈሪያ ማስከፈያ ደንብ ቁጥር 431 መሰረት የወጣ በመሆኑ አሁን ከሚሰጠው አገልግሎት አንጻር እጅግ ዝቅተኛ በመሆኑ ተመጣጣኝ እንዲሆን አልተደረገም፡፡

140. በኦዲት ወቅት በታየው የአውቶ ቦቴ ማዕከሉ ግልጋሎቱን ተደራሽ በማድረግ ጥራት ያለው ቬሪፊኬሽን ከማከናውን አንጻር አውቶሜት በማድረግ የሱፐርቪዥን እና የቁጥጥር ስራ በከፊል ተዘርግቶ ከተንቀሳቀሰበት ከህዳር 6/2006 ዓ.ም ጀምሮ ለእያንዳንዱ ተንቀሳቃሽ የፍሳሽ ማጓጓዣ ብር 100/ አንድ መቶ/ ብቻ የነበረ ሲሆን ይህ ክፍያ አሁን ካለው የውሃና የመብራት ክፍያ ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛ በመሆኑ የክፍያ ተመኑ እንዲስተካከል በቀን 11/03/2004 እና 04/10/2004 በተፃፉ ደብዳቤዎች ያሳወቀ ቢሆንም ሚኒስቴር መ/ቤቱ መልስ ያልሰጠ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት በተካሄደው የዶክሜንት ከለሳ ለማወቅ ተችሏል፡፡

141. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከብሔራዊ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት የተረከበው መሣሪያዎች ላይ (Working Standard) የተገጠሙት Outlet እና Inlet ቫልቮች፣ ሆዞች ከማርጀታቸው የተነሳ የተሠፈረ /የተለካው/ ውሀ ወደ ውጭ የሚፈስ በመሆኑ በልኬቱ ላይ ተፅዕኖ በማሳደሩ ችግሩን ለመቅረፍ የአውቶ ቦቴ ማዕከሉ ሆዞቹ እንዲገዙ እና ፍሳሹ እንዲስተካከል በደብዳቤ የተጠየቀ ቢሆንም ሚ/ር መ/ቤቱ መልስ ባለመሰጠቱ ችግሩ እስከ 2008 በጀት ዓመት እየስተተዋለ የሚገኝ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

142. ለቁጥጥር ያመቻል በሚል ማዕከሉ በሚሰጠው ሰርተፊኬት ላይ የተለያዩ ማሳሰቢያዎችን፣ ቀድሞ ከነበረው ተጨማሪ የልኬት ውጤቶች በመጨመር እና በሀገሪቱ ካሉ ማንኛውም የነዳጅ ማከፋፈያ ማደያዎች፣ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ነዳጅ በሚረከቡበት ጊዜ ሰዓት ደቂቃ ቴክስት ወደ ማዕከሉ በመላክ ሰርተፊኬቱን የማረጋገጥ ስራ መስራት የሚያስችል ሶፍትዌር ተዘርግቶ በስራ ላይ መዋሉ ቢገለጽም ይሁን እንጂ በማዕከሉ የሚሰጠው የቬሪፊኬሽን ሥራ አስመልክቶ ፈጣንና ቀልጣፋ ባለመሆኑ በነዳጅ ማጓጓዝ ሥራ ላይ የተሠማራው ደንበኛ

አገልግሎቱን ለማግኘት እስከ አምስት ወራት ወረፋ የሚጠብቅ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

143. በሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት የነዳጅ ማጓጓዣ ተሽከርካሪ መጫን ከሚገባው መጠን በላይ በሕገወጥ መንገድ የአካል ለውጥ በማድረግ ከ700 ሊትር በላይ ከተሰጠው ትክክለኛ ሰርተፊኬት ውጪ ነዳጅ በማመላለስ ሲጠቀም የነበረ ድርጅት ጽ/ቤቱ በደረሰው ጥቆማ በሕግ እርምጃ እንዲወሰድበት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሲያሳውቅ ለ3 ወራት ድርጅቱን ከሥራ ከማገድ ውጭ ሚ/ር መ/ቤቱ እርምጃ ስለመውሰዱ የሚያሳይ ማሰረጃ በቅ/ጽ/ቤትም ሆነ በሚኒስቴር መ/ቤቱ አልተገኘም፡፡

144. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፈሳሽ ማጓጓዣ ታንከር (ቦቴ) ትክክለኛነት በማረጋገጥ የቬርፊኬሽን ሰርተፊኬት የሚሰጥ ሲሆን የቬርፊኬሽን ሰርተፊኬት አስመስለው በመስራት ሀሰተኛ በሆነ ሠርተፊኬት የሚጠቀሙት ደንበኞች ላይ ለሶስት ወር ከማገድ ውጭ በህግ አግባብ እንዲጠየቁ ያልተደረገ መሆኑን በኦዲቱ ከተሰበሰቡ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለምሳሌ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት የተሸከርካሪ ባለንብረቶች ውሰጥ የሶስት ወር እግዳቸው ተነስቶላቸው ተለዋጭ ሠርተፊኬት የተሰጣቸውና እርምጃ ያልተወሰደባቸው መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ ይህንኑ የሚያሳይ ሰንጠረዥ (በአባሪ 4) ተይዟል፡፡

145. ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ከሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ጋር ባደረገው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የነበረው የዋጋ ተመን አነስተኛ መሆኑ ቢታወቅም ለዚህ ምክንያት አዲስ የተረቀቀ የሥነ ልክ አዋጅ አለመጽደቁ መሆኑና ለዚህ ጥያቄ ተነስቶ አዋጁ ሳይሻር የማይቻል መሆኑ፣ አዋጁ የሥነ ልክ ሥረዓት ተዘርግቶ መቆጣጠር አለበት ቢልም ይህንን ማድረግ ያልተቻለ መሆኑ፣ ምክንያቱም በፊት የነበረው አዋጅ ክፍተት ያለበት በመሆኑ እንዴት መቆጣጠር፣ መቅጣት እንደሚቻል የሚያሳየን አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡ ረቂቅ አዋጁ ለማጸደቅ በሂደት ላይ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

146. እንዲሁም የቦቴ ማዕከሉ (Working Standard) የተገጠሙት Outlet እና Inlet ቫልቮች፣ ሆዞች ያረጁ በመሆኑ የተሠፈረው /የተለካው/ ውሀ ወደ ውጭ የሚፈሰው ትክክል መሆኑንና መሳሪያዎቹ እንዲገዙ በተደጋጋሚ ጥያቄ ቢቀርብም ግዥ ሥርዓቱ በጣም አዝጋሚ በመሆኑ በ2007 ዓ.ም በጀት ሊገዛ አለመቻሉ፣ ዕቃዎቹ እንዲገዙ ትዕዛዝ ተላልፎ ፕርፎርማ ከተሰበሰበ በኋላ በማዘገየት ዕቃዎቹ ሳይገዙ የበጀት ዓመቱ አልቋል በማለት ገልፀዋል፡፡ ሆኖም ግን በመውጫ ስብሰባ ወቅት የስራ ኃላፊዎቹ ዕቃዎቹ እንደተገዙ ቢገልፁም ሥራ ላይ አለማዋሉን አስረድተዋል፡፡ የሠርተፊኬትን አስመስሎ መሥራትና የአካል ለውጥ በማድረግ ማጭበርበርን በተመለከተ ለሶስት ወር ከማገድ ውጭ በህግ አግባብ እርምጃ ያልተወሰደ

መሆኑ ምክንያቱም ይህ የሚሠራው የህግ ክፍሉ በመሆኑ ወደ ህግ ክፍሉ ተላልፎ በሂደት ላይ ነው፡፡

147. በመሆኑም በኦዲቱ ከ2005-2007 ዓም ሀሰተኛ ሰርተፊኬት አስመስለው በመጠቀም ከታገዱት ውስጥ ለህግ ክፍል ክስ እንዲቀርብባቸው በ5/06/2007 ዓም ለ6 ድርጅቶች ብቻ የተጻፈ መረጃ ለኦዲት ቡድኑ ቀርቧል፡፡

148. ይሁን እንጂ የአውቶ ቦቱ የአገልግሎት ክፍያ አነስተኛ በመሆኑ አሁን ከሚሰጠው አገልግሎት አንጻር እንዲሻሻል ባለመደረጉ ወጪው ከጥቅሙ ከፍ እንዲልና መንግስት ከስራው የሚያገኘው ገቢ አነስተኛ እንዲሆን ያደርጋል፣ እንዲሁም የፈሻሽ መለኪያ መሳሪያዎች ሲያጁ ወይንም ሲበላሹ በወቅቱ እንዲቀየሩ ባለመደረጉ ትክክለኛ የሆነ የልኬት ስራ እንዳይሰራ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡ ሰርተፊኬት በማጭበርበር ወይም አስመስሎ በመስራት በሚጠቀሙ ተገልጋዮች ላይ አስፈላጊው እርምጃ በህግ አግባብ በወቅቱ እንዲወሰድ ባለመደረጉ ህገወጥ ስራዎች እንዲበራከቱ ያደርጋል፡፡

**ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላትስ ጋር ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር እና ቀልጣፋ የሆነ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፣**

**ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልሎች፣ ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና ከተገልጋዮች ጋር ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር ያለው መሆኑን በተመለከተ፣**

149. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሌሎች አስፈጻሚ መ/ቤቶች የሚሰራባቸው አስገዳጅ ደረጃዎች በተቀናጀ መልኩ እንዲተገበሩ ሊያደርግና በአፈጻጸም ላይ የሚያወያይ መደበኛ ጉባኤ ሊጠራና የወጪና የገቢ ንግድ ዕቃዎች ተፈላጊውን የደረጃ መሥፈርት ሳያሟሉ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም ከሀገር እንዳይወጡ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር በትብብር ሊሠራ ይገባል፡፡

150. በኦዲቱ ወቅት ጉዳዩን አስመልክቶ ከተሰበሰቡ ማስረጃዎች ለማወቅ እንደተቻለው ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 691/2003 በተሰጠው ስልጣን መሰረት በሌሎች አስፈጻሚ መ/ቤቶች የሚሰራባቸው አስገዳጅ ደረጃዎች በተቀናጀ መልኩ እንዲተገበሩ መደበኛ የሆነ ጉባኤ አዘጋጅቶ በመጥራት እያወያየ አይደለም፣

151. ይሁን እንጂ በኦዲቱ በናሙና በታዩት ቅ/ጽ/ ቤቶች የአዲስ አበባ ፣ አዳማ፣ በኮሜት ተ/ጽ/ቤት፣ የአዋሣ፣ የሞያሌ፣ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በሌሎች አስፈጽሚ መ/ቤቶች የሚሠራባቸው አስገዳጅ ደረጃዎች በተቀናጀ መልኩ እንዲተገበሩ ከባለድርሻ አካላት ጋር በሚፈለገው መልኩ

በቅንጅት የማይሰሩና እንዲሁም  በሚሰሩ ስራዎች በአሰራር ላይ ባሉ ችግሮችና መፍትሄዎች አፈጻጸም ላይ ለማወያየት መደበኛ የሆና ተከታታይ  ጉባኤ እዳልተደረገ ታውቋል፡፡

152. በአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የናሙና አወሳሰድን በተመለከተ ሁሉም እንስፔክተር በተመቸው ናሙና የሚወስድ መሆኑ እና በደብዳቤ ሥራው እንዲሠራ ከማሳወቅ ውጪ ቴክኒካል የሆነ ሥልጠና የማይሰጥ በመሆኑ እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአሠራር ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች በተጠናከረ መልኩ ባለመሥራቱ በናሙና አወሳሰድ ላይ ችግር መኖሩ፣ ለምሳሌ ከአንድ መኪና ናሙና ሲወሰድ ከየት እንደሚጀመርና ምን ያህል መወሰድ እንዳለበት አለመታወቁ በሥራ ላይ የሚፈጠሩ ችግሮችን በጋራ ተወያይቶ ለመፍታት ያለመቻል ችግር እየተጠፈረ መሆኑ የስራ ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

153. የኦዲት ቡድኑ በናሙና ካያቸው የክልል ንግድ ቢሮዎች  የሀዋሳ ፣ የአዲስ አበባ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎችና የኦሮሚያ ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ ሚ/ር መ/ቤቱ በህጋዊ ስነልክ አተገባበር ዙሪያ  ወጥነት ያለው ቋሚ የሆነ የመወያያ  መድረክ  በማዘጋጀት ተግባራዊ ባለማድረጉ እስከ ወረዳ ድረስ በመውረድ ሥራው የተፈለገውን ያህል አለመሠራቱ የስራ ኃላፊዎቹ በቃለመጠይቅ ገልጸዋል፡፡

154. የአዳማ ቅ/ጽ/ቤት ገቢዎችና ጉምሩክ ከሚ/ር መ/ቤቱ ጋር በተሟላ መልኩ በቅንጅት የመሥራት ችግር በመኖሩ ችግሩን ለመፍታት የባለሥልጣን ቅ/ጽ/ቤቱ ከሚ/ር መ/ቤቱ አስፈጻሚ  አካላት ጋር ችግሮችን የሚፈቱበት የመወያያ መድረክ ለማድረግ ቢጀመርም ሊቀጥል ባለመቻሉ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤት ሰራተኞች በአንድ ቦታ  ሆነው ለደንበኞች ቀልጣፋ  አገልግሎት መስጠት እንዳይቻልና ደንበኞች  እንዲጉላሉ ያደረገ መሆኑ የቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ ገልጸዋል፡፡

155. የአዲስ አበባ ቃሊቲ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ቅርንጫፍ ቅንጅታዊ አሠራርን በተመለከተ ቅ/ጽ/ቤቱ ከንግድ ሚኒስቴር መ/ቤትም ሆነ ከተወካይ ጽ/ቤቱ ጋር በሚፈለገው መልኩ በቅንጅት እየሠራ አለመሆኑ፣ ለዚህም በየጊዜው ዕቃዎችን ግልጽ እና ወቅታዊ የማይደረግ መሆኑ፣ ባለስልጣን መ/ቤቱ ቅዳሜ ስለሚሠራ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ቅዳሜ የማይሠራ በመሆኑ ደንበኞች አገልግሎት ባለማግኘታቸው ከፍተኛ ቅሬታ እየተፈጠረ በመሆኑ በዚህ ላይ በመወያየት በቅርንጅት መሥራት አለመቻሉ፣ የንግድ ሚኒስቴር የብረት ናሙና የሚወስደው በመጋዝ በመቁረጥ በመሆኑና ጊዜ በመውሰዱ ተሽከርካሪዎች በስምንት ሰዓት ውስጥ ግቢውን ለቀው የሚወጡበት አሠራር ቢኖርም ከሁለት እስከ ሶስት ቀናት በግቢው በመቆየት የቦታ ጥበትና የሥራ መጓተት ያጋጠመ መሆኑ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም ቋሚ የሆነ የመወያያ መድረክ የሌለ መሆኑ፣

156. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 691/2003 የገቢና ወጪ የንግድ ዕቃዎች ተፈላጊውን የደረጃውን መስፈርት ሳያሟሉ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም ከሀገር እንዳይወጡ ከሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት ጋር በትብብር እንዲሠራ ስልጣን ቢሰጠውም ከሁሉም አስፈጻሚ አካላት ጋር በተሟላ መልኩ በትብብር እየሠራ አለመሆኑ ታወቋል፡፡

157. በኦዲቱ በናሙና በታዩት የአዲስ አበባ፣ የኮሜት ተ/ጽቤት፣ የአዳማ፣ የሃዋሳ እና የሞያሌ ቅ/ጽ/ቤቶች፣ ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣንጋር በተፈለገው ደረጃ በቅንጅትና በትብብር ስለማይሠራ ዕቃዎች የኢትዮጵያ አስገዳጅ ደረጃ ያላቸውንና የሌላቸውን ባለማወቅ እና ናሙና የተወሰዱ ዕቃዎች ውጤት ሳይገለጽ የሚለቅበት ሁኔታ መኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

158. የኦዲት ቡድኑ በናሙና ካያቸው ባለድርሻ አካት የሞጆ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ቅ/ጽ/ቤት ከሞጆ ተወካይ ጽ/ቤት ጋር በበቂ ሁኔታ በቅንጅትና በትብብር እንደማይሠራ ለማወቅ ተችሏል፡፡

159. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪና የገቢ ንግድ ዕቃዎች ተፈላጊውን የደረጃ መሥፈርት ሳያሟሉ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም ከሀገር እንዳይወጡ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር የሚፈለገውን ያህል በትብብር ለመስራት አንድ ማዕከል ወይም ተቀራራቢ ቢሮ ባለመሆኑ ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት ለደንበኞች ለመስጠት ክፍተት የተፈጠረ መሆኑ የሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት ተስማሚነት ምዘና ድርጅ ኃላፊ ተገልጿል፡፡

160. ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ከሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ጋር ባደረገው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በሌሎች አስፈጻሚ መ/ቤቶች የሚሰራባቸው አስገዳጅ ደረጃዎች በተቀናጀ መልኩ እንዲተገበሩ በአፈጻጸም ላይ የሚያወያይ መደበኛ ጉባኤ አዘጋጅቶ የማያወያይ መሆኑ ይህ ሊሆን የቻለው በአዋጁ ላይ የቴክኒክ ደንብ ስራ ለማለት ተፈልጎ መሆኑን ገልጸው ነገር ግን በአዋጁ የተገለጸው በስህተት መሆኑ፣ ይህ ስራ የሚሰራው የቴክኒክ ደንብ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ሲሆን የሚመለከተውም ንግድ ነክ አዋጆችን መሆኑና ክፍሉ በፊት በዳይሬክቶሬት ደረጃ የነበረና አሁን ግን በቡድን ደረጃ እየሰራ የሚገኝ መሆኑ፣ የናሙና አወሳሰድ ዘዴ በእያንዳንዱ የምርት ደረጃ ላይ የተገለጸ ሲሆን ከደረጃ ውጭ መመሪያ ሊዘጋጅለት የማይቻል መሆኑን ገልጸዋል፡፡

161. እንዲሁም ሚ/ኒስቴር መ/ቤቱ በገቢና ወጪ ዕቃዎች ክትትልና ቁጥጥር ዙሪያ ከሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት ላይ ክፍተቶች ያሉበት መሆኑ ይህም ከደረጃዎች ኤጀንሲ ጋር አስገዳጅ ደረጃዎች ሲከለሱ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሳያሳውቅ ለተስማሚነት ድርጅት ብቻ የሚያሳውቅና ሚ/ር መ/ቤቱ በነበረው ደረጃ የሚሰራና

ደረጃዎቹ ወቅታዊ ሲደረጉ የማያሳውቅ በመሆኑ በመካከል የአሰራር ልዩነት እየተፈጠረ መሆኑ፣ የኢትዮጵያ ገቢዎችን ጉምሩክ ባለስልጣን የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ ካሳወቀው ደረጃዎች ውጪ አስገዳጅ ደረጃዎች ውስጥ ያልተካተቱን ደንበኞች እንዲያመጡ ወደ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚልክና ምልልስ የፈጠረ መሆኑ፣ እንዲሁም ባንክ መመሪያዎችን እንዲያስፈጽም ደብዳቤ የሚላክ ቢሆንም ባንክ መመሪያዎቹን አንዳንዴ በትክክል የማያስፈጽም በመሆኑ ክፍተቶች መፈጠራቸው ገቢዎችና ጉምሩክ መረጃዎች ባለማስተላለፍ በአስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ምርቶች ሳይፈተሽ እንደሚለቀቁ ከቅንጅት አኳያ የሚስተዋሉ ችግሮች መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

162. ይሁን እንጂ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በረቂቅ ሪፖርት ላይ በሰጡት መልስ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች ባሉበት በገቢዎችና ጉምሩክ ሰብሳቢነት ሞጆ ደረቅ ወደብ፣ አዳማ፣ ሞያሌ ኮሜትና መቀሌ ከባለድርሻ አካላት ጋር ቋሚ የውይይት መድረክ እንዳለው መረጃዎችንም እንደሚለዋወጥ እንዲሁም ከባንክ እና ከደረጃዎች ኤጀንሲ መረጃዎች የሚለዋወጥ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ሆኖም በኦዲቱ በናሙና በታዩ ቅ/ጽ/ቤቶች ከገቢዎችና ጉምሩክ እና ከክልል ንግድ ቢሮዎች ጋር ቋሚ የሆነ መወያያ መድረክና ጠንካራ የሆነ ቅንጅታዊ አሰራር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

163. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር ለመስራት ጠንካራ የሆነ ቅንጅታዊ አሠራርና መደበኛ የሆነ ጉባኤ አዘጋጅቶ ውይይት የማያደር በመሆኑ በአሰራር ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮች በወቅቱ አሰፈላጊውን መፍትሄ እንዳያገኙ ያደርጋል፡፡

**ከተገልጋዮች የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት በየ6 ወሩ ቋሚ የምክክር መድረኮች ያዘጋጀ መሆኑን፣ ከክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች ባለሙያዎች ጋር በየሩብ ዓመቱ ውይይት ማድረጉንና በየስድስት ወሩ ግምገማ ማካሄዱን በተመለከተ፣**

164. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ ከሚያስገቡና ከሚያሰወጡ ተገልጋዮች የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በየ6 ወሩ ቋሚ የምክክር መድረኮች ሊያዘጋጅና ተግባራዊ ሊያደረግ፣ ከክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች ባለሙያዎች ጋር በሕጋዊ ሥነ-ልክ ሥራ አፈጻጸም ዙሪያ በየሩብ ዓመቱ ውይይት ሊያደርግና በየስድስት ወሩ አንድ ጊዜ ግምገማ ሊያካሄድ ይገባል፡፡

165. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ዕቃዎችን ከሀገር ውስጥ የሚያስገቡና ከሀገር ውጭ የሚልኩ ተገልጋዮች የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በየ6 ወሩ ቋሚ የግንኙነት መድረኮች ሊያዘጋጅና ተግባራዊ እንደሚያደርግ ቢገልጽም ከ2005-2007 በጀት ዓመት መደበኛ የሆነ የግንኙነት መድረክ እንደሌላቸው ነገር ግን በተለያዩ ጊዜያት

በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር ማለትም ከኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ፣ ከብሔራዊ ስነልክ ኢንስቲትዩት፣ ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት፣ ከኢትዮጵያ የኢነርጅ ባለሥልጣን፣ ከመድኃኒትና ምግብና ቁጥጥር ባለሥልጣን እና ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ጋር የጋራ መድረክ ተዘጋጅቶ ውይይት እንደሚያደርጉ ቢገልጹም በቃለ ጉባኤ ያልተደገፈና ማስረጃው የሌለው መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

166. በኦደቱ በናሙና በታዩት የንግድ ሚኒስቴር ቅ/ጽ/ቤቶች የአዳማ እና የሞያሌ ቅ/ጽ/ቤቶች ከተገልጋዮች የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ቋሚ የሆነ የመወያያ መድረክ የሌለውና ይህም በመሆኑ የናሙና መዝግየት ችግር አለመፈታትና ከጉምሩክ ጋር ያለመናበብ ችግር የተፈጠረ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

167. በናሙና በታዩ የአዋሣ፣ የአዳማ ቅርንጫፍ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት ንግድ ሚኒስቴር ከተገልጋዮች የሚነሱ ችግሮችን በጋራ ለመፍታት ቋሚ የሆነ የመወያያ ፕሮግራም የሌለው በመሆኑ በአሠራር ላይ የሚከሰቱ ችግሮችን ምክንያት ለይቶ ለማወቅ አለመቻሉና ለሚስተዋሉ ችግሮች ጋራ መፍትሄ እርምጃ ለመውሰድ አለመቻሉ የስራ ኃላፊዎቹ ገልጸዋል፡፡

168. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች ባለሙያዎች ጋር በሕጋዊ ሥነ-ልክ ሥራ አፈጻጸም ዙሪያ በየሩብ ዓመቱ ውይይትና በየስድስት ወሩ አንድ ጊዜ ግምገማ ሊያካሄድ እንደሚባ በአምስት ዓመት /2003-2007/ ስትራቴጂክ ዕቅዱ እና በዓመታዊ ዕቅዱ ላይ ያስቀመጠ ቢሆንም ከክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች ጋር የሪፖርት አቀራረብ ስርዓት የሌለው መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

169. በኦዲቱ በናሙና በታዩ የንግድ ቢሮች የሀዋሳ፣ የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ፣ የኦሮሚያ ገበያ ልማት ቢሮ ከሚ/ር መ/ቤቱ ጋር መረጃዎችን በመለዋወጥ ውይይት የማያደርግና በመሆኑ ሪፖርቶችን በጋራ በመገምገም በሥራ ላይ የሚስተዋሉ ክፍተቶችን መቅረፍ አለመቻሉ ለማወቅ ተችሏል፡፡

170. ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ከሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ጋር ባደረገው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ከተገልጋዮች የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር ቋሚ የመወያያ መድረክ የሌለው መሆኑ፣ ነገር ግን የህዝብ ክንፍ ከሚባሉት ጋር በአመት ሁለት ጊዜ የውይትት መደረኮች ይደረጋሉ ነገር ግን በቃለ ጉባኤ የተደገፈ አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡

171. ከክልል ንግድና ኢንዱትሪ ባለሙያዎች ጋር በህጋዊ ስነ ልክ ስራ አፈጻጸም ዙሪያ በዕቅዱ መሰረት በየሩብ ዓመቱ ውይይት የማይደረግና ክልሎችን ሁለት ጊዜ ከመጥራት አንድ

ጊዜ ሁሉንም ክልሎች በመጥራት በየ6 ወሩ ግምገማ የሚደረግ ሲሆን መ/ቤቱም ከክልሎች ጋር የሪፖርት አቀራረብ ስርዓት የሌለው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

172. በመሆኑም ከተገልጋዮች የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት ከሚመለከታቸው ተቋሚት ቋሚ የሆነ የመወያያ መድረክ እንዲኖር ባለመደረጉ ችግሮች በወቅቱ እንዳይፈቱና መፍትሄ እንዳያገኙ አድርጓል፡፡

**ከላብራቶሪ ፍተሻ ውጤት ጋር በተያያዘ ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር ውይይት ያደረገና መፍትሄ ያስቀመጠ መሆኑን በተመለከተ፣**

173. ሚ/ር መ/ቤቱ ከላብራቶሪ ፍተሻ ውጤት ጋር በተያያዘ በሚነሱ ጉዳዮች ላይ ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር ውይትት በማድረግ መፍትሄ ሊያሰቀምጥ ይገባል፡፡

174. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በላቦራቶሪ ፍተሻ ውጤት ጋር በተያያዘ በሚነሱ ጉዳዮች ላይ ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር ውይይት በማድረግ መፍትሄ ማስቀመጥ እንዳለበት በሁለቱ መ/ቤቶች የመግባቢያ ሰነድ ላይ የተቀመጠ ቢሆንም የሚከሰቱ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ውይትት በማድረግ የመፍትሄ እርምጃ አላሰቀመጠም፡፡

175. በኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት የሚከናወኑው የላብራቶሪ ናሙናዎች የፍተሻ ውጤት የመዘግየት ሁኔታዎች በድርጅቱ የሚታይ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

176. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት ለኢትዮጵያ ተስማሚነትና ምዘና ድርጅት የሰሜን ምዕራብ ቅ/ጽ/ቤት ናሙናዎች በሚልክበት ጊዜ በተደጋጋሚ ናሙና የሚረከበው አካል ባለመኖሩ በወጪ ምርት ሥራ ላይ መዘግየት መፈጠሩ እና የምርት ጥራት ፍተሻ ሙያው ከሚመለከታቸው ውጪ በድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ተሰርቶ የሚላከው ውጤት ትክክል አለመሆኑን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ በኢትዮጵያ ተስማሚነትና ምዘና ድርጅት ለሰሜን ምዕራብ ቅ/ጽ/ቤት ሲያሳውቅ በግልባጭ ሚኒስቴር መ/ቤቱ እንዲያውቀው ቢያደርግም ለችግሩ የመፍትሔ እርምጃም ያልወሰደ መሆኑን ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

177. በኦዲቱ በናሙና በታዩ ቅ/ጽ/ቤቶች የአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ከላብራቶሪ ፍተሻ ውጤት መዘግየት ጋር በተያያዘ በሚነሱ ጉዳዮች ላይ ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር የውጤት መዘግየት በተመለከተ በተደጋጋሚ ውይይት ቢያደርግም ችግሩ በገቢ ዕቃዎች ላይ የሚስተዋል መሆኑ የስራ ኃላፊ ለኦዲት ቡድኑ ገልጸዋል፡፡

178. የአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የናሙና ፍተሻ ውጤት መዘግየትን ለንግድ ሚኒስቴር መ/ቤት ቢያሳውቅም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር ውይይት በማድረግ ችግሩ እንዲቀረፍ ያልተደረገ መሆኑ ገልጸዋል፡፡

179. የሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት ከተስማሚነት ድርጅት ጋር ስለ ናሙና ፍተሻ መዘግየት በተደጋጋሚ ቢነጋገሩም ናሙናዎች አስቸኳይ የፍተሻ አገልግሎት ክፍያ ተከፍሎባቸው በተጠቀሰው ቀንና ሰዓት አለመድረሳቸው በደንበኞች ላይም ቅሬታ መፍጠሩን ለሚ/ር መ/ቤቱ በ2006 ዕቅድ አፈፃፀማቸው ላይ ቢገልጹም መ/ቤቱ የማስተካከያ እርምጃ አለመውሰዱና እንዲሁም የሀዋሣ ቅርንጫፍ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጽ/ቤት ሚኒስቴር መ/ቤቱ በናሙና መዘግየት የተነሳ የሚፈጠሩ ችግሩን ለመቅረፍ የናሙና ፍተሻ ሥራውና የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሥራ በአንድ መ/ቤት ባለመሠራቱ የናሙና ውጤት የመዘግየት ሁኔታ መቀረፍ ያልቻለ ችግር መሆኑ ታውቋል፡፡

180. በኦዲቱ በታዩ ባለድርሻ አካላት የኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት ከላብራቶሪ ውጤት መዘግየት ጋር በሚነሱ ጉዳዮች ላይ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የደረጃዎች ኤጀንሲ አስገዳጅ ደረጃዎች በትክክል መሬት ወርደው እንዲተገበሩ ባለማድረጉ፣ ቴክኒካል የሬጉላቶሪ ጽ/ቤት ባለማቋቋሙና በተከሰቱት ችግሮች ላይ ውይይት በማኬሄድ ተገቢውን መፍትሄ መስጠት አለመቻሉን የስራ ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

181. ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ከሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ጋር ባደረገው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ከላብራቶሪ ውጤት መዘግየት ጋር በሚነሱ ጉዳዮች ላይ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከድርጅቱ ጋር ውይይት የሚያደርግና ከሩቅ ቦታ የሚመጡ ናሙናዎች በአስቸካይ እንዲፈተሰሹ የተደረገበት አሰራር እንዲኖር ውይይት መደረጉን ገልጸዋል፡፡ ይሁን እንጂ ውይይቱ ስለመደረጉ የሚያሳይ ማስረጃው ማስረጃ የሌለና በቃለ ጉባኤ ያልተደገፈ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

182. እንዲሁም የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በረቂቅ ሪፖርት ላይ በሰጡት መልስ የላብራቶሪ የፍተሻ ውጤት በሚዘገይበት ምክንያት በየቀኑ ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር በመገናኘት ችግሮቸ ለመፍታት ጥረት እየተደረገ መሆኑንና ናሙናዎች ተራ በመጠባበቅ በላብራቶሪ እንዳይቆዩ ፈጣን የላብላቶሪ ፍተሻ አገልግሎት የሚሰጥበት አሰራር እንዲዘረጋ ተደርጓል በማለት ቢገልጹም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሥራ ኃላፊዎች እና በክልል በሚገኙ የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት ኃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ሚኒስቴር መ/ቤቱና ድርጅቱ ውይይት በማድረግ በተፈጠረ የናሙና ውጤት መዘግየት የመፍትሔ አቅጣጫ ባለመቀመጡ ችግሩ አለመቀረፉን ታውቋል፡፡

183. በመሆኑም መኒስቴር መ/ቤቱ ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር ከላብራቶሪ ውጤት መዘግየት ጋር በሚነሱ ጉዳዮች ላይ በየጊዜው ውይይት በማድረግ ችግሮች እንዲፈቱ በአለመደረጉ የናሙና መዘግየት ችግር እንዳይቀረፍ ያስችላል፡፡

**ናሙናዎች መረጃ በመረጃ ቋት ተመዝግቦ እንዲያዝ መደረጉን፣ ወቅቱን የጠበቀ መረጃ ለቅ/ጽ/ቤቶችና ለተገልጋዮች እንዲሰራጭ ማድረጉንና ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር መረጃ የሚለዋወጥና መሆኑን በተመለከተ፣**

184. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የናሙናዎች መረጃ በጥንቃቄ በባህር መዝገብና/ loog book/ በመረጃ ቋት ተመዝግቦ ሊያዝ፣ ወቅቱን የጠበቀ መረጃ በማሰባሰብ በማደራጀትና በመተንተን ለቅ/ጽ/ቤቶችና ለተገልጋዮች ሊያሰራጭና ሚ/ር መ/ቤቱ ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር መረጃ ሊለዋወጥና ወርሀዊ ወይም የሩብ አመት ሪፖርቶችን በጋራ ሊገመግም ይገባል፡፡

185. ይሁን እንጂ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በሥሩ የሚገኙ በናሙና በታዩት በአዲስ አበባ፣ በኮሜት፣ በሞጆ፣ በአዳማ፣ በሀዋሳ እና በሞያሌ ቅ/ጽ/ቤቶች የናሙና ተረካቢ ሠራተኛ ባለመኖሩ የናሙናዎች መረጃ በመረጃ ቋት ተመዝግቦ እንዲያዝ እንዳልተደረገ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

186. የኮሜት ተወካይ ጽ/ ቤት የናሙና ተረካቢ ባለሙያ ባለመኖሩ ስራው የሚሰራው በኢንስፔክተሩ መሆኑንና ባለሙያ እንዲመደብ በተደጋጋሚ ቢጠየቅም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ምላሽ ያልተሰጠበት በመሆኑ የናሙና መሰባበርና መጥፋት የሚገጥም ሲሆን፣ እንዲሁም በጽ/ቤቱ የላብራቶሪና የመጠባበቂያ ናሙናዎች ማስቀመጫ ቦታ ችግር እና የተለያዩ ሰነዶችን በአግባቡ ለመያዝና ፋይል ለማድረግ የካስቶዲንና የመደርደሪያ ችግር መኖር እና የሞጆ ተወካይ ጽ/ቤት የሥራ ቦታ ለሥራ ምቹ ባለመሆኑ ሰነዶች ለሥራ በቀላሉ ለማግኘት የሚያስችል ቦታ እና መደርደሪያ ባለመኖሩ በሥራ ላይ ጫና እየፈጠረ መሆኑን የቅ/ጽ/ ቤቶቹ የስራ ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

187. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለስራ አጋዥ የሆኑ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃዎችን በሚፈለገው ደረጃ በማሰብሰብና በማደራጀት ወጥ በሆነ መልኩ ወቅቱን ጠብቆ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና ለክልሎች እንዲሰራጩ አላደረገም፡፡

188. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለቅ/ጽ/ቤቶች ለሥራቸው አጋዥ የሆኑ መረጃዎችን ወጥ በሆነ መልኩ ወቅቱን በመጠበቅ ማድረስ ባለመቻሉ በቅርንጫፎች ጽ/ቤቶች መካከል የአሠራር ልዩነት እየተፈጠረ መሆኑ በቃለ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

189. በኦዲቱ በናሙና በታዩ ቅ/ጽ/ቤቶች የአዳማ ቅንጫፍ ጽ/ቤት በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተዘጋጅቶ ወደ ቅርንጫፎች የወረደው የአሠራር ማንዋል ዝርዝር መመሪያ ባለመሆኑ ሁሉን ያቀፈና ያልተሟላ ሲሆን፣ እንዲሁም በቅርንጨፍ የሚሠጡ አገልግሎቶች በማንዋሉ ያልተካተቱ በመሆኑ ሥራው የሚሠራው በልምድና ከሌሎች ቅርንጫፎ ጽ/ቤቶች አሠራር በመጠየቅ ለመሥራት በመገደዳቸው በአንድ ወጥ አሠራር ላይ ክፍተት ያለ መሆኑ ገልጸው እንዲሁም ሞጆ ተወካይ ጽ/ቤት ሚ/ር መ/ቤቱ መረጃዎችን ወጥነት ባለው መልኩ ወቅቱን ጠብቆ ባለመላኩ የሶስተኛ ወገን ሠርተፊኬት አሠራር በቅ/ጽ ቤቱ ዕቃዎች በውዴታ ግዴታ እንዲለቀቁ የተደረጉ ሲሆን፣ አንዳንድ ዕቃዎች እንደ ሶላር ያሉ ዕቃዎች አስገዳጅ መሆናቸውን የሚገልጽ መስረጃ ለጽ/ቤቱ ባለመላኩ ዕቃዎቹ የተለቀቁ መሆኑ፣ የሞያሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወቅቱን የጠበቀ መረጃ በማሠራጨት ላይ ክፍተት ያለበት በመሆኑ ወጥ የሆነ ነገር እንደሌለና ማስረጃዎቹ ከአለፉ በኋላ የሚደርሱበት ሁኔታ መኖሩ የስራ ኃላፊዎቹ ገልጸዋል፡፡

190. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተስማሚነት ምዘና ድረጅት ጋር መረጃ በመለዋወጥ ወርሃዊ ወይም የሩብ አመት ሪፖርት በጋራ እየገመገመ አለመሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

191. ድርጅቱ ከሚ/ር መ/ቤቱ የጋራ ስራዎች ምን እንደሆኑና እንዴት እየሰሩ እንደሆነ የሚያሳይ ሪፖርቶች የማይለዋወጡና እና በጋራ የመገምገምንና አብሮ የመሥራትን ሁኔታ በሁለቱ መካከል የሌለ መሆኑን የደርጅቱ የስራ ኃላፊዎች ከኦዲት ቡድኑ ጋር በካሄደው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ገልጸዋል፡፡

192. ጉዳዩን አስመልክቶ ኦዲት ቡድኑ ለሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የናሙና ተረካቢ ሰራተኛ /ካስቶዲያን/ በ2004 ዓ.ም በተደረገው የአደረጃጀት ለውጥ አስፈላጊ አይደለም ተብሎ እንዲቀር የተደረገ መሆኑ በዚያ ምክንያት በቅ/ጽ/ቤቶች የናሙና ተረካቢ ሰራተኛ የሌለ በመሆኑ የናሙናዎች መረጃ በመረጃ ቋት ያልተያዘ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

193. መመሪያ በተመለከተ አዲስ መመሪያ ሲመጣ ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች በኢሜል የሚላክ መሆኑ፣ ነገር ግን ቅ/ጽ/ቤቶቹ መረጃ በእጃቸው ኖሮ በአፈጻጸም ላይ ክፍተት መኖርና አዋጁን በደንብ አንብቦ ያለመረዳት ችግር መኖሩን አስረድተዋል፡፡

194. ዳይሬክቶሬቱ ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር የሚለዋወጠው መረጃ የላብራቶሪ ፍተሻ ውጤት ብቻ ሲሆን፣ ወርሃዊና የሩብ አመት ሪፖርቶችን በጋራ የማይገመገም መሆኑ፣

የመግባቢያ ሰነዱ ላይ የተቀመጠው ድርጅቱ ከኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት ጋር መረጃዎችን በመለዋወጥ የሚገመግሙት በማለት ገልጸዋል፡፡

195. እንዲሁም የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በረቂቅ ሪፖርት ላይ በሰጡት መልስ ወቅታዊ መረጃዎች በመረጃ መረብ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እንደሚተላለፍና ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት የላብራቶሪ ፍተሻ አገልግሎት በሚሰጠው አሠራር ላይ ችግሮች ቢከሰቱ በወቅቱ ምላሽ የሚጠይቁ በመሆናቸው ቋሚ መድረክ ሳይጠበቅ በጋራ ውይይት መድረክ ላይ በየቀኑ ግንኙነት በማድረግ አፈጻጸሙ እንደሚገመገም ቢገልጹም ስለመገምገሙ የሚያሳይ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡

196. በመሆኑም የናሙናዎች መረጃ በጥንቃቄ በመረጃ ቋት ተመዝግቦ አለመያዙ የናሙናዎችን መረጃ በቀላሉ እንዳይገኝ ያስችላል፣ ወቅቱን የጠበቀ መረጃ ለቅ/ጽ/ቤቶችና ለተገልጋዮች እንዲሰራጭ አለመደረጉ በቅ/ጽ/ቤቶች መካከል የአሰራር ልዩነት እንዲፈጠርና ያደርጋል፡፡

**ሁሉንም የሥራ አመራር ያካተተ መደበኛ እና ተከታታይ የማናጅመንት የውይይት መድረክ ያለው መሆኑን በተመለከተ፣**

197. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሁሉንም የሥራ አመራር ያካተተ— መደበኛ እና ተከታታይ የማናጅመንት /የስራ አመራር/ የውይይት መድረክ ሊኖረው እና በውይይቱ ላይ የሚነሱ ጉዳዮችን በቃለ ጉበኤ በአግባቡ ሊይዝ ይገባል፡፡

198. ይሁን እንጂ ሚኒስቴርመ/ቤቱ ሁሉንም የሥራ አመራር ያሳተፈ መደበኛ እና ተከታታይ የሆነ የማኔጅመነት /የስራአመራር/ የውይይት መድረክ ፈጥሮ በውይይቱ ላይ የሚነሱ ነጥቦችን በቃለ ጉባኤ እንዲያዙ እንዳላደረገ ለማወቅ ተችሏል፡፡

199. የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ባካሄደው የመረጃ ክለሳ መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የማኔጀመንት ቃለ ጉባኤ አራት ከፍተኛ የሥራ አመራሮችና አንድ የመ/ቤቱ ህዝብ ግንኙነትና የኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ኃላፊ በአጠቃላይ አምስት አባላትን የያዘ በመሆኑ ካሉት አስራ ስምንት የማናጅመንት አባላት አንጻር ሁሉንም የከፍተኛ አመራር /የስራ ኃላፊዎች/ ያላካተተ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በመሆኑም በገቢና ወጪ ዕቃዎች ዳይረክቶሬት ስር ባሉ በሁለቱም ቡድኖችየሥራ ክንውን ወቅት ከ2005-2008 ህዳር መጨረሻ ድረስ የሰው ኃይል አደረጃጀት ችግር፣ ለሥራ በሚያስፈልጉ ግብዓቶች የሟሟላት ችግር፣ ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚላኩ ጥያቄዎች ተገቢው መልስ በወቅቱ አለማግኘት ችግር ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚተላለፉ ማስረጃዎች በወቅቱ እና በሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እኩል ያለመድረስ ችግር እንደተፈጠረ ለማወቅ ተችሏል፡፡

200. ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ለሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ጋር ባደረገው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሁሉን የስራ አመራር ያሳተፈ መደበኛ እና ተከታታይ የሆነ የማኔጅመንት የውይይት መድረክ የሌለው መሆኑ፣ ምክንያቱም መ/ቤቱ የማኔጀመንት የሚላቸው 5 አባላትን የያዘ ከፍተኛ የሥራ አመራሮችን ብቻ እንጂ በመ/ቤቱ የሚገኙ ዳይሬክቶሬቶችን የማያካትት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

201. በመሆኑም ሁሉንም የሥራ አመራር ያሳተፈ መደበኛ እና ተከታታይ የሆነ የማኔጅመነት /የስራ አመራር/ ያካተተ የውይይት መድረክ ባለመኖሩ ከቅ/ጽ/ቤቶች የሚነሱ ችግሮች ለበላይ አመራሩ ቀርበው መፍትሄ እንዳያገኙ አድርጓል፡፡

**በክልል የሚካሄደውን የሕጋዊ ሥነ ልክ አተገባበር ገምግሞ ድጋፍ የሚያደርግ መሆኑን፣ በቅ/ጽ/ቤቶችና በክልሎች በአካል በመገኘት የጋጠሙ ችግሮችን ገምግሞ መፍትሄ የሰጠ መሆኑ በተመለከተ፣**

202. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በክልል የሚካሄደውን የሕጋዊ ሥነ ልክ አተገባበርና አሠራር ሊገመግምና ድጋፍ ሊያደርግ፣ በቅ/ጽ/ቤቶችና በክልሎች በገቢና ወጪ ዕቃዎችና በህጋዊ ስነ ልክ ቁጥጥርና ክትትል ዙሪያ በአካል በመገኘት የተከናወኑትንና በክንውን ወቅት የጋጠሙ ችግሮችን በማየትና ሊገመግምና መፍትሔ ሊሰጥ ይገባል፡፡

203. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ክልሎች በማስተባበር በጋራ በቅንጅት መስራት፣ በክልል የሚገኙ ሥነ-ልክ ባለሙያዎች ያለባቸውን የክህሎት ክፍተት ችግር የመሙላት፣ የሚጠቀሙበት ስታንዳርድ የመለኪያ መሳሪያዎች በቂ አለመሆንና አንድ ወጥ አተገባበር እንዲኖር በመገምገም ተገቢውን ድጋፍ እያደረገ አለመሆኑ ታውቋል፡፡

204. በኦዲቱ በናሙና በታዩ ክልሎች የአዲስ አበባ እና የሀዋሳ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ሚ/ር መ/ቤቱ ለንግድ ቢሮው የህጋዊ ስነ ልክ አተገባበርን በመገምገም አስፈላጊውን ድጋፍ አያደርግም፡፡ ይህ ባለማድረጉ በየደረጃው የህጋዊ ስነ ልክ የሚቀጠሩ ፈጻሚዎች ያላቸውን የክህሎት ክፍተት መሙላት ያልተቻለ እና የኦሮሚያ ክልል የንግድና ገበያ ልማት ቢሮ ሚ/ር መ/ቤቱ ድጋፍ፣ ክትትል፣ ስልጠና እና የመለኪያ መሳሪያዎች እገዛና ድጋፍ የማድረግ ስራ የተጠናከረ አለመሆኑ ታውቋል፡፡

205. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቅ/ጽ/ቤቶች እና በክልል ንግድ ቢሮዎች በአካል በመገኘት በገቢና ወጪ ዕቃዎች እና በህጋዊ ስነልክ ቁጥጥርና ክትትል ዙሪያ የተከናወኑትንና በክንውን ወቅት የገጠሙ ችግሮ በማየት ለችግሮቹ የመፍትሔ እርምጃ ለመውሰድ በተሟላ መልኩ እንዳልገመገመ ለመረዳት ተችሏል፡፡

206. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ ቅ/ጽቤቶች እና በክልል ንግድ ቢሮዎች /በአዲስ አበበ፣ በአዳማ፣ በሞጆ፣ በሀዋሣ እና በሞያሌ ቅ/ጽቤቶች እና በአዲስ አበባ፣ በኦሮሚያ፣ በሀዋሣ ንግድ ቢሮዎች/ ውስጥ በአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፣ በኮሜት ተ/ጽ/ቤት፣ በሞጆ ተወካይ ጽ/ቤት፣ በሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት እንዲሁም በአዋሣ ንግድ ቢሮ በ2007 ዓ.ም በጀት ዓመት ብቻ አንድ ጊዜ በአካል በመገኘት በክንውን ወቅት የጋጠሙ ችግሮች ላይ ውይይት የተደረገ ቢሆንም የመፍትሔ እርምጃ ያልተሰጠ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

207. በሞያሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በአካል በተገኙበት ወቅት በጽ/ቤቱ ያሉ ችግሮችን አንስተው፤ የጽ/ቤቱን የመገልገያ ችግሮች አንደ ተሽከርካሪ፣ ፎቶ ኮፒ ማሽን፣ ስካነር የመሳሰሉት እና የኮንትሮ ባንድ ችግር ከፍተኛ መሆኑን በሰፊው ውይይት ቢደረግበትም ከጽ/ቤቱ ምንም አይነት የመፍትሔ ምላሽ ባለመሰጠቱ የጽ/ቤቱ ሥራ መጓተትና የደንበኛ ቅሬታ የፈጠረ መሆኑ፣ እንዲሁም በከተማ ውስጥ የሚገኙ ማደያዎች ለሞተር ሳይክሎችና የኬንያ ታርጋ ላላቸው መኪናዎች ነዳጅ ከታሪፈ በላይ እንደሚሸጥና በብዙ ሺህ ሊተር የሚቆጠር ነዳጅ በአህያ እየተጫነ በኮንትሮባንድ መልክ ከሀገር እየወጣ በመገኘቱ ለሚ/ር መ/ቤቱ በዕቅድ አፈፃፀሙ ቢያሳውቅም ምንም መፍትሄ እርምጃ ያልተሰጠ መሆኑን ከተከለሱ መስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

208. ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ከሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ጋር ባደረገው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በክልል ለሚገኙ ባለሙያዎች ያለባቸው የክህሎት ክፍተት ለመሙላት ለሁሉም ክልሎች ስልጠናዎችን የተሰጠ መሆኑ ነገር ግን ስልጠናውን የሚወስዱ ሰዎች በተለያዩ ምክንያቶች ስራውን የሚለቁበት ሁኔታ መኖሩን፣ እንዲሁም የመቆጣጠሪያ ስታንዳርዶችን ከGIZ ጋር በመሆን ድጋፍ የማድረግ ስራ መሰራቱ ነገር ግን በቂ አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡

209. እንዲሁም በህጋዊ ስነ ልክ እና በገቢና ወጪ ዕቃዎች ስራዎች ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን ለማየትና የመፍትሄ እርምጃ ለማስቀመጥ በክልሎች በኣካል በመገኘት በዕቅድ ቢቀመጥም በዕቅዱ መሰረት ተፈጻሚ አለመሆኑን አስረድተዋል፡፡

210. በመሆኑም በክልል የሚካሄደውን የሕጋዊ ሥነ ልክ አተገባበርና አሠራር ገምግሞ በቂ ድጋፍ ባለማድረጉ ባለሙያዎች ያለባቸውን የክህሎት ክፍተት ችግርና አንድ ወጥ አተገባበር አለመኖር እና የመለኪያ መሳሪያዎች በቂ አለመሆኑ የሚፈለገው ያህል ስራው እንዳይሰራ ማድረጉ እንዲሁም በቅ/ጽ/ቤቶችና በክልሎች በገቢና ወጪ ዕቃዎችና በህጋዊ ስነ ልክ ቁጥጥርና ክትትል ዙሪያ በአካል በመገኘት በክንውን ወቅት የጋጠሙ ችግሮችን በማየትና ገምግሞ መፍትሄ ባለመሰጠቱ ችግሮቹ ተለይተው መፍትሄ እንዳያገኙ አድርጓል፡፡

**የቅርንጫፍ ጽ//ቤቶች የሚያቀርቡትን ወርሀዊ፣ ሩብ ዓመት፣ ግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርታቸውን ከገመገመ በኋላ ግብረ መልስ የሰጠ መሆኑን በተመለከተ፣**

211. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቅርንጫፍ ጽ//ቤቶች የሚያቀርቡትን ወርሀዊ፣ ሩብ ዓመት፣ ግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርታቸውን ከገመገመ በኋላ ግብረ መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡

212. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚቀርቡትን ወርሃዊ፤ የሩብ ዓመት፣ የግማሽ ዓመትና አመታዊ ሪፖርቶችን ከገመገመ በኋላ በአፈጻጸም ላይ በሚያጋጥሙና መፍትሄ ሊቀመጥላቸው በሚገቡ ችግሮች ላይ ወቅታዊ የሆነ ግብረ መልስ አለመስጠቱ ታውቋል፡፡

213. በኦዲቱ በናሙና በታዩ የአዲስ አበባ፣ ኮሜት ተ/ጽ/ቤት ሞጆ፣ አዳማ እና ሃዋሳ ቅ/ጽቤቶች ወርሃዊ፣ የሩብ ዓመት፣ የግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ እንዲሁም 1ለ5 ሪፖርት የሚያቀርቡ ሲሆን ነገር ግን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ በሚያቀርቧቸው የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች ላይ በወርሃዊ ስብሰባዎች በጋራ ስብሰባ ውይይት በማካሄድ በግምገማ ወቅት ከመነጋገር ውጪ ለሚቀርቡት ሪፖርት ግብረ መልስ ተሰጥቶ የማያውቅ መሆኑ፣ ይህም በመሆኑ ችግሮቹን ማንሳት ያቆሙ መሆኑ እና ጽ/ቤቶቹ ምን ላይ ማተኮር እና ምን ላይ መሥራት እንዳለባቸው ለማወቅ መቸገራቸውን ገልጸዋል፡፡

214. ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ከሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ጋር ባደረገው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ቅ/ጽ/ቤቶች እና ክልሎች በሚሰበሰቡበት ጊዜ በሚቀርቡ ሪፖርት ላይ ውይይት ውይይት ከተደረገ በኋላ ግብረ መልስ የሚሰጥ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

215. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ውይይት በሚደረግበት ጊዜ ግብረመልስ ይሰጣል ቢሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ከሚልኳቸው ሪፖርቶች ግብረ መልስ የማይሰጣቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

216. በመሆኑም የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች በሰጡት የረቂቅ ኦዲት መልስ የቅ/ጽ/ቤቶችን ወርሃዊ፣ ሩብ ዓመት ግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርቶች በመገምገም አጠቃላይ በሚደረገው የ6 ወር የሥራ አፈጻጸም ግምገማ ላይ ግብረ መልስ እንደሚሰጥ እና በቅ/ጽ/ቤቶቹ በአካል በመገኘት ከተገልጋይና ከባለድርሻ አካላት ጋር በ6 ወር በምርቶች ጥራት ቁጥጥር ዙሪያ ውይይት አድርጐ ለችግሮች ከባለድርሻ አካላትና ተገልጋዮች ጋር በመወያየት ሥራ ሂደቱን አስመልክቶ በሚነሱ ጉዳዮች የመፍትሔ አቅጣጫ እንደሚቀመጥ ቢገልጹም፡፡ ይህን የሚያሳይ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡ እንዲሁም የኦዲት ቡድኑ በናሙና መርጦ ባያቸው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በሚያቀርቡት የዕቅድ አፈፃፀምና 1 ለ 5

ሪፖርታቸው  እና በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ላይ በሰጡት መልስ በየወሩ መጨረሻ ለሚያቀርቡት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርትና 1 ለ5 ሪፖርታቸው በተያዘው ዕቅድ መሠረት በጽሑፍ ግብረ መልስ እንደማይሰጣቸውና በአካል በመገኘትም ስለ ምርቶች ጥራት ውይይት በማድረግ የመፍትሔ አቅጣጫ የማይቀመጥ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

217. በመሆኑም የቅርንጫፍ ጽ//ቤቶች የሚያቀርቡትን ወርሀዊ፣ ሩብ ዓመት፣ ግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርታቸውን ገምግሞ ግብረመልስ በወቅቱ እንዲሰጥ ባለመደረጉ ቅ/ጽ/ቤቶቹ ለሚቀርቡዋቸው ችግሮች መፍትሂ እንዳያገኙና እንዲሁም  ምን ላይ ማተኮር እና ምን ላይ መሥራት እንዳለባቸው  ለማወቅ አስቸጋሪ ያድርጐታል፡፡

## ክፍልሦስት

### 1. የመደምደሚያ ሃሳቦች

218. የገቢና ወጪ ዕቃዎችና የህጋዊ ስነልክ ስራዎች ደረጃ ፍተሻ አፈጻጸም ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆን በሚኒስቴር መ/ቤቱ ፣ በቅ/ጽ/ቤቶች እና በባለድርሻ አካላት የተደረጉ ጥረቶች መኖራቸውን እንረዳለን፤ ከክዋኔ ኦዲት ዋና ዋና ዓላማዎች አንዱ በመንግስት የሚወጡ አዋጆች እና ደንቦች እንዲሁምበመ/ቤቶች የተዘረጉ የአሰራር ስርአቶች እና የወጡ መመሪያዎችበአግባቡ ተፈፃሚና ውጤታማ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡ከዚህ ዓላማ አንፃር የሚኒስቴር መ/ቤቱ የገቢና ወጪ ዕቃዎች እና የህጋዊ ስነ ልክ ስራዎች ደረጃ ፍተሻ አፈጻጸም ውጤታማነት በኦዲቱ በሚገመገምበት ወቅት ከዚህ በታች የተመለከቱ ዋና ዋና የአሠራር ክፍተቶች ታይተዋል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ህጋዊ ሥነ ልክን ስራዎችን በተሸለና ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲከናወኑ ለክልሎች በሰጠው ውክልና መሰረት በእስትራቴጂክ ዕቅዱ አካቶ ለክልሎች በማውረድ ክልሎችም ዕቅድና አፈጻጸማቸውን በመከታተል እንዲልኩ ያላደረገ፣ የህጋዊ ስነልክ ቡድንም አመታዊና ድንገተኛ ምርመራ በዕቅድ በማካተትና በመፈጸም የአፈጻጸም ሪፖርት የማያቀርብ እና እንዲሁም በዕቅድ አፈጻጸም ላይ የሚታዩ ክፍተቶች በመለየት የመፍትሂ እርምጃ ያለመውሰዱ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የደረጃዎች ፍተሻን በተመለከተ የአፈፃፃም መመሪያ ያወጣ ቢሆንም በናሙና በታዩ ቅ/ጽ/ቤቶች መመሪያው ያልደረሰ እና በመመርያው መሰረት ተግባራዊ የማይደረግ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያከናውናቸው የደረጃዎች ፍተሻ ቀልጣፋ እና ውጤታማ እንዲሆን በሥሩ የሚገኙ ቅ/ጽ/ቤቶች በተሟላ ሰው ኃይል በማደራጀትና ለሥራው የሚያስፈልጉ አስፈላጊ ግብዓቶችን በማሟላት አፈጻጸማቸውን እየተከታተለና እየተቆጣጠረ ያለመሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ምርቶች ከአገር ከመውጣታቸው በፊት ደህንነታቸው እና ጥራታቸው እንዲሁም የሀገሪቱ ህግ በሚፈቅደው መሰረት እንዲወጡ የማያደርግበት ሁኔታ መኖሩን፣ አንዳንድ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶች ወደ ገበያ ከመግባታቸው በፊት በኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት ናሙና ተወስዶ የደረጃ ፍተሻ ተፈትሾ አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ በሚያዘው መሠረት ደረጃቸው ሳይረጋገጥ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በጊዜያዊ መልቀቂያ እንዲለቀቁ የሚያደርግ መሆኑን እና በአንዳንድ የገቢና ወጪ ምርቶች

የሀገሪቱን ህግና ደንብ ተከትለው መግባታቸውን/መለካታቸውን ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት የሚላክለትን ውጤት ወይም የሶስተኛ ወገን ሰርተፊኬት ትክክለኛነት በማረጋገጥ ይሁንታ /Permit/ እየሰጠ ያለመሆኑ፣

- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪና የገቢ ንግድ ዕቃዎች ተፈላጊውን የደረጃ መስፈርት የማያሟሉ የንግድ ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም ከሀገር እንዳይወጡ እንዲያግድ በተሰጠው ስልጣን ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶች በተስማሚነት ምዘና በላብራቶሪ ፍተሸ ተደርጎላቸው ከደረጃ በታች የሆኑት እንዲታገዱ ያላደረገና በጊዜያዊ መልቀቂያ እንዲለቀቁ የሚያደርግና መስፈርት የማያሟሉትን በመቆጣጠር ከተዘጋጀላቸው ደረጃ በታች ሆነው በተገኙት ላይ በተሰጠው ስልጣን መሰረት አስፈላጊውን እርምጃ አለመውሰዱ፣
- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት የደንበኞች የላብራቶሪ ፍተሸ ውጤት በደንበኞች ላይ ቅሬታ እንዳያሳድር በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲያሳውቅ አስፈላጊውን ክትተልና ቁጥጥር ያላደረገና በአንዳንድ ቅ/ጽ/ቤቶች አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ በሚያዘው መሰረት የሚወሰዱ ናሙናዎች ከውጫዊ ተጽኖ ነጻ ሆነው የጥራት ባህሪያቸው ሳይለወጥ ከተወሰዱበት ሰዓት ጀምሮ በ48 ሰዓት ውስጥ ለላብራቶሪ ምርመራ ቶሎ እንዲቀርቡ ያለመደረጉ፣
- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ምርትን ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገቡ አስመጪዎች አሰገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ያላቸው ምርቶች አለም አቀፍ ተቀባይነት ባላቸው ኢንስፔክሽን አካላት የተረጋገጠ የላብራቶሪ ሰርተፊኬት ከአገልግሎት መጠየቂያ ጋር እንዲያቀርቡ የማድረግና የሰርተፊኬቱ ትክክለኛነት ወካይ ናሙና ወስዶ የማረጋገጥ አሰራር ስርዓት የዘረጋ ቢሆንም ወጥ በሆነ በተሟላ መልኩ እያደረገ ያለመሆኑ፣ እንዲሁም አንዳንድ አስመጪዎች የሦስተኛ ወገን ሰርተፊኬት ማቅረብ ግዴታ መሆኑ ከሁለት ጊዜ በላይ ተነግሯቸው ሰርተፊኬት ማቅረብ ያልቻሉ ምርታቸው የደረጃ መስፈርት ማሟላቱ የላብረቶሪ ውጤት እስከሚገለጽ ድረስ በጉምሩክ እንዲጠብቁ አለማድረጉ፣
- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሀገሪቱን የስነ ልክ ስርዓት የዘረጋ ቢሆንም የክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች በተሰጣቸው ውክልና መሰረት በተዘረጋው ስርዓት ተግባራዊ ማድረጋቸው ተገቢውን ቁጥጥር ያላደረገና የመለኪያ መሣሪያዎች የትክክለኛነት ሥራዎች በክልል ንግድ ቢሮዎችና በፌዴራል ተጠናክረው መስራታቸውን ለማረጋገጥ በቂ የሆነ ስታንዳርድ የመለኪያ መሣሪያዎች የሌሉት፣ ክልሎች ላይ የሚገኙ የሕጋዊ ሥነ-ልክ ባለሙያዎች የክህሎት ክፍተት ያለባቸውና የሚጠቀሙበት ስታንዳርድ ለመለኪያ

መሳሪያዎቹ ለጉዳዩ ትኩረት ካለመስጠትና ከየአቅም ውስንነት አኳያ በየጊዜው ካሊቤሬት የማይደረግና ስራዎቹ መሰራታቸውን የሚከታተልበትና ክፍተቶችና ጥንካሬዎችን የሚከታተልበት አሰራር የሌለው መሆኑ፣

- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከውጭ የሚገቡ የመለኪያ መሳሪያዎች ወደ ገበያ ከመግባታቸው በፊት ደረጃቸውን የጠበቁ መሆኑን ሳያረጋግጥ በጊዜያዊ መልቀቂያ እንዲለቀቁ የሚያደርግ መሆኑ፣

- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ አንዳንድ ተገልጋዮች የተሸጋጋሪ ሚዛን (Standard Weight) የክብደት ማነፃፀሪያዎች ቬሪፋይ ለማስደረግ ወስደው ቬሪፋይ ካስደረጉ በኋላ የማነጻጸሪያ መሳሪያዎቹን ከተጠቀሙበት በኋላ በወቅቱ እንዲመልሱና እንዳያዘገዩ ለሌሎች ተገልጋዮች እንዲያስረክቡ ውል በማስገባት የማይሰጥ መሆኑ፣

- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአውቶ ቦቴ ቬርፊኬሽን ክፍያ በ1966 ዓ.ም የወጣ ሲሆን አሁን ከሚሠጠው አገልግሎትና ወጪ አንጻር ክፍያው ወቅታዊና ተመጣጣኝ ከጊዜው አንጻር እንዲሆን ማሻሻያ ወይም ማስተካከያ ያለመደረጉ፣ በተመሳሳይ የፈሳሽ ማጓጓዣ ታንከር (ቦቴ) ትክክለኛነት በማረጋገጥ የሚሰጠው የቬርፊኬሽን ሰርተፊኬት በትክክል ተግባራዊ መደረጉ የሚከታተልበት አሰራር ስራ ላይ ቢያውልም የቬርፊኬሽን ሰርተፊኬት አስመስለው በመስራት በሚጠቀሙት ላይ ለሶስት ወር ከማገድ ውጭ በህግ አግባብ እርምጃ እንዲወሰድ ያለማድረጉ፣

- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአስፈጻሚ መ/ቤቶች ፣ቅ/ጽ/ቤቶች፣ በክልሎችና ባለድርሻ አካላት የሚሰራባቸው አስገዳጅ ደረጃዎች በተጠናከረ መልኩ በቅንጅት እንዲሰሩ ከተገልጋዮች የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት በአፈጻጸም ላይ በሚያጋጥሙ ችግሮችና ሊወሰዱ በሚገባቸው የመፍትሄ እርምጃዎች ላይ የሚወያይ መደበኛ የሆነ ጉባኤ በመጥራት ውይይት የማያደርግና ተፈላጊውን የኢትዮጵያ ደረጃ መስፈርት የማያሟሉ ምርቶችና ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም ከሀገር እንዳይወጡ ከሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት ጋር በትብብር የሚሰራ ቢሆንም በአንዳንድ ቦታዎች ቅንጅታዊ አሰራሩ ላይ ክፍተቶች የሚስተዋሉ መሆኑ፣

- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች የሚካሄዱ የህጋዊ ስነ ልክን የስራ አፈጻጸምን በየሩብ ዓመቱ ውይይት ለማድረግና በየስድስት ወሩ ግምገማ ለማድረግ ዕቅድ ቢያዘጋጅም ከ2005-20007 ዓ.ም ባሉት ጊዘያት ውስጥ በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ ያለማድረጉ፣ እንዲሁም ከላብራቶሪ ፍተሻ ውጤት መዘግየት ጋር በተያያዘ በተደጋጋሚ

በሚነሱ ጉዳዮች ላይ ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር በመሆን ችግሮችን እንዲቀረፉ ተከታታይነት ያለው ውይይት በማድረግ ለችግሮቹ መፍትሄ እንዲቀመጥ ያለማድረጉ፣

- ❖ በአንዳንድ ቅ/ጽ/ቤቶች የናሙና ተረካቢ ሠራተኛ ባለመኖሩ ናሙናዎች በናሙና መረካከቢያ ሰነድና በመረጃ ቋት እንዲያዙ ያልተደረጉ፣ ለቅ/ጽ/ቤቶች ለስራ አጋዥ የሆኑ መረጃዎችን በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች መካከል የአሰራር ልዩነት እንዳይፈጠር ወጥ በሆነ መልኩ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃዎችን በሚፈለገው ደረጃ በማሰብሰብና በማደራጀት እንዲሰራጩ አላደረገም፡፡ እንዲሁም ከተስማሚነት ምዘና ድረጅት ጋር መረጃ በመለዋወጥ ወርሃዊ ወይም የሩብ አመት ሪፖርት በጋራ ገምግሞ የማያውቅ መሆኑ፣

- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሁሉንም የሥራ አመራር ያሳተፈ መደበኛ እና ተከታታይ የማኔጅመነት/የስራአመራር/ መድረክ ፈጥሮ በውይይቱ ላይ የሚነሱ ነጥቦችን ጉዳዮች በቃለ ጉባኤ እንዲያዙ ያላደረገ መሆኑ፣

- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በክልል የሚካሄደውን የሕጋዊ ሥነ ልክ አተገባበርና አሠራርን ላይ ያሉትን ችግሮችን በሰው ኃይል ስልጠና፣ በመሳሪያዎችና ሌሎች አስፈላጊ በሆኑ ድጋፎች በመለየት እየገመገመ በበቂ ሁኔታ ድጋፍ እያደረገ አለመሆኑ፣ በቅ/ጽ/ቤቶችና በክልሎች በገቢና ወጪ ዕቃዎችና በህጋዊ ስነ ልክ ቁጥጥርና ክትትል ዙሪያ በአካል በመገኘት የተከናወኑትንና በክንውን ወቅት የጋጠሙ ችግሮችን በማየት ገምግሞ መፍትሔ ያልሰጠ ካለመሆኑም በላይ ከቅርንጫፍ ጽ//ቤቶች ለሚያቀርቡ ወርሀዊ፣ ሩብ ዓመት፣ ግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርታቸውን እየገመገመ ግብረ መልስ የማይሰጥ መሆኑ፣

219. የገቢና ወጪ ዕቃዎችና የህጋዊ ስነ ልክ ስራዎች ደረጃ ፍተሸ አፈጻጸም ውጤታማና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ እየተከናወነ እንዳልሆነ ያሳያል፡፡ ይህን መሰረት በማድረግ በሚቀጥለው የሪፖርት ክፍል በኦዲቱ ወቅት የታዩትን የአሰራር ክፍተቶች ለማሻሻል አስተዋፅኦ ያደርጋሉ ተብሎ የታመንባቸው የማሻሻያ ሃሳቦችቀርበዋል፡፡

## ክፍልአራት

### 2. የማሻሻያ ሀሳቦች

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ህጋዊ ሥነ ልክን ቡድን የሚያከናውናቸውን የስነ ልክ ስራዎች ዓመታዊ ምርመራና ድንገተኛ ፍተሸ በእስትራቴጂክ ዕቅዱ አካቶ አመታዊ ዕቅድ እንዲያቅዱ ሊያደርግና እንዲሁም የክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች በተሰጣቸው ውክልና መሰረት የሚያከናዉኑዋቸውን የህጋዊ ስነ ልክ ስራዎች መ/ቤቱ በእስትራቴጂክ ዕቅዱ በማካተት ለክልሎች ሊያወርድና ክልሎችም ዕቅድና የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በተቀመጠው ጊዜ (በየ3 ወሩ) እንዲያቀርቡ ሊያደርግና አፈጻጸማቸውን ሊገመግም በገቢና ወጪ እቃዎች እና በመለኪያ መሳሪያዎች ደረጃ ፍተሻ አፈጻጸም ክንውን ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን በመለየት የመፍትሄ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያወጣውን የደረጃዎች ፍተሻ መመሪያ በማሻሻል ውጤታማና ቀልጣፋ ለማድረግ የሚያስችል ግልጽ በሆነና በማያሻማ መልኩ አዘጋጅቶ በሥሩ ለሚገኙ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ሊያሰራጭና በትክክል ተግባራዊ መደረጉን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሥሩ ያሉትን ቅ/ጽ/ቤቶችን የማስፈጸም አቅምን ወደ ተሻለ ደረጃ ለማድረስና ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲከናወን በተሟላ የሰው ኃይል በማደራጀትና ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ መገልገያዎችን በማሟላት አፈጻጸማቸውን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ምርቶች ከሃገር ከመውጣታቸው በፊት ደህንነታቸውና ጥራታቸውን የጠበቁ መሆኑን የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት በሁሉም ክልሎች የሚገኙ የማበጠሪያ ቤቶችን የሥራ እንቅስቃሴና በየጊዜው ፈቃድ ማሳደሳቸውን የሚከታተል መሆኑን የሚቆጣጠርበት ስርዓት ሊኖረውና እንዲሁም ገቢ ምርቶች ወደ ገበያ ከመግባታቸው በፊት የሕብረተሰቡን ጤንነትና የአካባቢ ደህንነት ከማስጠበቅ አንጻር በጉምሩክ ጣቢያዎች ደህንነታቸውና ጥራታቸው የጠበቁና ተገቢውን መስፈርት ያሟሉ መሆናቸውን በማረጋገጥ ምርቶችየሀገሪቱን ህግና ደንብ ተከትለው መግባታቸውን/መለካታቸውን በማረጋገጥ ይሁንታ /Permit/ ሊሰጥ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ያላቸው ምርቶች አስፈላጊውን የደረጃ መስፈርት የማያሟሉ ገቢ ምርቶች ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ በተስማሚነት ምዘና ድርጅት ተፈትሸው ማለፋቸውን በማረጋገጥ ደረጃ የማያሟሉ ምርቶች እንዳይገቡ ሊያደርግና ፣ እንዲሁም ወጪ ምርቶችም ማበጠሪያ ቤቶቹ ደረጃቸውን የጠበቁና ናሙና

ለመውሰድ በሚመች መልኩ የተቀመጡ መሆኑን ድርጅቱ ክትትል የሚያደርግ መሆኑን በማረጋገጥ ምርቶቹ ከሀገር እንዳይወጡ ሊያደርግና ከደረጃ በታች በሆኑት ላይ በህብረተሰቡ ጤናና የአካባቢ ደህንነትን ከማስጠበቅ አንጻር በመቆጣጠር ከተዘጋጀላቸው ደረጃ በታች ሆነው በተገኙት ላይ አስፈላጊውን እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኢትዮጵያ ተስማሚነት ድርጅት ወደ ሀገር የሚገቡ ዕቃዎችን የላብራቶሪ የፍተሻ ውጤት እንደ የዕቃዎቹ አይነትና ባህሪ በተቀመጠላቸው ጊዜ ውስጥ በመፈተሽ ውጤታቸውን መገለጽ ባለበት ጊዜና ሰዓት ማሳውቁን ሊከታተልና ሊቆጣጠርና እንዲሁም አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ በሚያዘው መሰረት የተወሰዱ ናሙናዎች ከውጫዊ ተፅኖ ነጻ ሆነው የጥራት ባህሪያቸው ሳይለወጥ ከተወሰዱበት ሰዓት ጀምሮ በ48 ሰዓት ለፍተሻ እንዲቀርቡ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ምርትን ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገቡ አስመጪዎች አሰገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ያላቸው ምርቶች አለም አቀፍ ተቀባይነት ባላቸው ኢንስፔክሽን አካላት የተረጋገጠ የላብራቶሪ ሰርተፊኬት ከአገልግሎት መጠየቂያ ጋር እንዲያቀርቡ በማድረግ የሰርተፊኬቱ ትክክለኛነት አንድ ሶስተኛ ወካይ ናሙና ወስዶ በላብራቶሪ ሊያረጋግጥና በሥሩ ለሚገኙ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አስመጪዎች ለሚያመጧቸው ዕቃዎች የሦስተኛ ወገን ሰርተፊኬት ማቅረብ ግዴታ መሆኑ ከሁለት ጊዜ በላይ ተነግሯቸው ሰርተፊኬት ማቅረብ ላልቻሉ አስመጪዎች ምርቶቹ ተለቀው በማህበረሰቡና በአከባቢ ላይ ጉዳት እንዳያስከትሉ በውዴታ ግዴታ እንዳይለቀቁ የደረጃ መስፈር ማሟላታቸውን የላብራቶሪ ውጤት እስከሚገለጽ ድረስ በጉምሩክ ጣቢያዎች እንዲጠብቁ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን የሀገሪቱን የስነ ልክ ስርዓት ሊዘረጋና በሁሉም ውክልና በተሰጣቸው የክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች ተግባራዊ መደረጉን ቁጥጥር ሊያደርግና የመለኪያ መሣሪያዎች የትክክለኛነት ሥራዎች በክልል ንግድ ቢሮዎችና በፌዴራል ተጠናክረው እንዲሠሩ በቂ የሆነ ስታንዳርድ የመለኪያ መሣሪያዎች ለክልሎችም ድጋፍ ሊያደርግ እና በክልሎችም የሕጋዊ ሥነ-ልክ ባለሙያዎች ያለባቸውን የክህሎት ክፍተታቸውን እንዲያሻሽሉ ትኩረት በመስጠት የስልጠ ድጋፍ ሊያደርግ እና የቬሪፊኬሽን ሥራ መሠራቱንም የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሸማቹን ጥቅም ከማስጠበቅ አንጻር የመለኪያ መሳሪያዎች ወደ ከገበያ ከመግባታቸው በፊት በፌደራልና በክልል ንግድ ቢሮዎች ደረጃቸውን የጠበቁ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተገልጋዮች ቬሪፋይ ለማስደረግ የክብደት ማነጻጸሪያ መሳሪያዎችን ወስደው ከተጠቀሙበት በኋላ እንዳያዘገዩና በወቅቱ እንዲመልሱ ውል አስገብቶ በውሉ መሰረት ተከታትሎ መሳሪያዎቹ እንዲመልሱ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአውቶ ቦቴ የቬርፊኬሽን የአገልግሎት ክፍያን አሁን ከሚሰጠው አገልግሎት አንጻር ወቅታዊ በማድረግ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ ሊያስከፍል፣ የፈሳሽ ማጓጓዣ ታንከር (ቦቴ) የመለኪያ መሳሪያ ከተገጠመለት በኋላ በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ውስጥ መሆኑን በማረጋገጥ ቬሪፋይ አድርጎ የሚሰጠው ሰርተፊኬት የተቀመጠለትን ጊዜ ጠብቆ የሚሰጠው መሆኑን ሊያረጋግጥ እና በሀሰተኛ ሰርተፊኬት አስመስለው በሚሰሩት ላይ እገዳ ሊያደርግና በህግ አግባብ አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሌሎች አስፈጻሚ መ/ቤቶች የሚሰራባቸው አስገዳጅ ደረጃዎች በተቀናጀ መልኩ እንዲተገበሩ ሊያደርግና በአፈጻጸም ላይ መደበኛ የሆነ ጉባኤ ሊያዘጋጅና ሊያወያይ፣ የወጪና ገቢ ንግድ ዕቃዎች አስፈላጊውን የደረጃ መስፈርት ሳያሟሉ ወደ ሀገር እንዳይገቡ ወይም እንዳይወጡ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካለት ጋር ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማከናወን ተከታታይነት ያለውን የውይይት መድረክ በማዘጋጀት ግንዛቤ በማስጨበትና አስፈላጊ የሆኑ ወቅታዊ መረጃዎችን በመስጠትና በመለዋወጥ እና የአንድ አከባቢ አገልግሎት ለተገልጋዩ በመስጠት በትብብር ሊሰራና እንዲሁም ዕቃ ወደ ሀገር ውስጥ ከሚያስገቡና ከሚያስወጡ ተገልጋዮች የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የሚነሱ ችግሮች በተደጋጋሚ እንዳይከሰቱና ችግሮች መፍትሄ እንዲያገኙ በጋራ ለመፍታት በየስድስት ወሩ መደበኛ የውይይት መድረክ ሊያዘጋጅና ወቅቱን ጠብቆ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልሎች ንግድና ኢንዱስተሪ ቢሮ የህጋዊ ስነ ልክ ባለሙያዎች ጋር ስራው በትክክል እየተካናወነ ስለመሆኑና ክልሎች በተሰጣቸው ውክልና መሰረት ሃላፊነታቸውን እየተወጡና ተግባራዊ እያደረጉ ስለመሆኑ በአፈጻጸሙ ዙሪያ በየሩብ ዓመቱ ውይይት ሊያደርግና በአጠቃላይ በስራዎቹ ላይ በሚታዩ ጉዳዮች በየስድስት ወሩ አንድ ጊዜ ግምገማ ሊያደርግና ከላብረቶሪ ፍተሻ ውጤት ጋር በተያያዙ ከተገልጋዮች

ለሚነሱ ጉዳዮች ቅሬታ እንዳያሳድር ትኩረት በመስጠት ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር ውይይት ሊያደርግና የሚነሱ ችግሮችን በመለየት መፍትሄ ሊያስቀምጥ ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች መደበኛ የሆነ የናሙና ተረካቢ ሠራተኛ በመመደብ የናሙናዎች መረጃ በጥንቃቄ በመረጃ ቋት ተመዝግቦ እንዲያዙ ሊያደርግ፣ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና ለተገልጋዮች ለስራ አጋዥ የሆኑ መረጃዎችን በመተንተንና በማደራጀት ወጥ የሆነ አሰራር እንዲኖር ወቅቱን ጠብቆ በሁለም ቅ/ጽ/ቤቶች ሊያሰራጭና ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር አስፈላጊ የሆኑ መረጃ ሊለዋወጥና ወርሀዊ ወይም የሩብ አመት ሪፖርቶችን በጋራ ሊገመግም ይገባል፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሁሉንም የሥራ አመራር ያሳተፈ መደበኛ እና ተከታታይ ያለው የማኔጅመነት የውይይት መድረክ ሊኖረው እና በውይይቱ ላይ የሚነሱ ነጥቦችን በቃለ ጉባኤ በመያዝ ተከታታይ ቁጥር ሰጥቶ በአግባቡ ሊይዝ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በክልል የሚካሄደውን የሕጋዊ ሥነ ልክ አተገባበርና አሠራር በተሻለና ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲከና በበቂ ሁኔታ አፈላጊውን የሆነ ድጋፍ ሊያደርግና አፈጻጸሙን ሊገመግምይገባል፡፡
- በቅ/ጽ/ቤቶች የሚሠሩ የገቢና ወጪ ዕቃዎች ከሀገር ሲወጡና ወደ ሀገር ሲገቡ ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ እና የሥነ ልክ የቁጥጥርና የክትትል ሥራ እንዲሠሩ በውክልና ለክልል ንግድ ቢሮዎች በሠጠው መሠረት ሥራው በተፈለገው ሁኔታ እንዲሠራ በሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና በክልል ንግድ ቢሮዎች በአካል በመገኘት በገቢና ወጪ ዕቃዎች እና በህጋዊ ስነልክ ቁጥጥርና ክትትል ዙሪያ የተከናወኑትንና በክንውን ወቅት የገጠሙ ችግሮችን በማየት ለችግሮቹ የመፍትሔ እርምጃ በመስጠት በተሟላ መልኩ ሊገመግምና ቅ/ጽ//ቤቶች ለሚያቀርቧቸው ወርሀዊ፣ ሩብ ዓመት፣ ግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ የአፈፃፀም እና 1ለ5 ሪፖርት ከገመገመ በኋላ ግብረ መልስ በመስጠት በሪፖርታቸው የተመለከቱትን የሥራ ክፍተቶች የሚደፍኑበት የሚያስችል የመፍትሔ እርምጃ ሊሰጥ ይገባል፡፡

በመውጫ ስብሰባ ወቅት የንግድ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴታ ክቡር አቶ ሀሳድ ዚያድ ሪፖርቱ የአሰራር ክፍተቶችን ያሳየ እንደሆነና የተጠቀሱትም ግኝቶች ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ጠቃሚ መሆናቸውን እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ አሁን እያጋጠሙት ያሉትን ችግሮች ለማሻሻል አጋዥ እንደሚሆናቸው ገልፀዋል ፡፡

## አባሪ 1

| የኦዲትጭብጥ<br><br>Audit issue) | የመመዘኛመስፈርት<br><br>(Evaluative criteria) |
|---|---|
| 1ሚኒስቴር መ/ቤቱ የገቢና ወጪ ዕቃዎች እና የመለኪያ መሳሪያዎች የደረጃ ፍተሻ አፈጻጸም እኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ የሚከናወን መሆኑን መገምገም፣ | . |
| ሚኒስቴር መ/ቤቱ የገቢና ወጪ ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ ሲገቡና ሲወጡ ቀልጣፋና ውጤታማ የደረጃ ፍተሻ ማድረግ የሚያስችል የክትትል እና ቁጥጥር ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፣ | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የገቢና ወጪ ዕቃዎች እና በህጋዊ የመለኪያ መሳሪያዎች ደረጃ ፍተሻ እስትራቴጂክ ዕቅድ ሊያዘጋጅና ስትራቴጂክ ዕቅዱን መሰረት አድረጎ አመታዊ ዕቅድ ሊያዘጋጅና ዕቅዱን ተግባራዊ በማድረግ የእቅድ ክንውን ሪፖርት ሊያቀርብ ይገባል፡፡ |
| | ሚኒስቴር መ/ቤቱ በገቢና ወጪ ዕቃዎች እና በህጋዊ መለኪያ መሳሪያዎች ደረጃ ፍተሻ አፈጻጸም ዕቅድ ክንውን ላይ ለሚታዩ ክፍተቶች በመለየት የመፍትሄ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ |
| | ሚኒስቴር መ/ቤቱ ክልሎች ህጋዊ ስነ-ልክ በተመለከተ ዕቅድ እንዲያዘጋጁና የዕቅድ ክንውን ሪፖርት እንዲያቀርቡ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የደረጃዎች ፍተሻ አፈፃፀምን ውጤታማና ቀልጣፋ ለማድረግ የአሠራር መመሪያ አውጥቶ በሥሩ ለሚገኙ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ሊያሳውቅና ተግባራዊነቱን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሥሩ ያሉትን ቅ/ጽ/ቤቶች በሰው ኃይል በማደራጀትና ለሥራው የሚሆኑ መገልገያዎችን በማሟላት አፈጻጸማቸውን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ |
| | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ምርቶች ከአገር ከመውጣታቸው በፊት ደህንነታቸው እና ጥራታቸው እንዲሁም የሀገሪቱ ህግ በሚፈቅደው መሰረት የሚወጡ መሆናቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |

| | |
|---|---|
| | ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከውጪ የሚገቡ ምርቶች ወደ ገበያ ከመግባታቸው በፊት በጉምሩክ ጣቢያዎች ደህንነታቸውና ጥራታቸው እንዲሁም ተገቢውን መስፈርት ያሚሉ መሆናቸውን ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ |
| | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪና የገቢ ንግድ ዕቃዎች ተፈላጊውን የደረጃ መስፈርት የማያሟሉ የንግድ ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም ከሀገር እንዳይወጡ ሊያግድ ይገባል። |
| | ሚኒስቴር መ/ቤቱ አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ያላቸው የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የደረጃውን መስፈርት ማሟላታቸውን ሊቆጣጠር ከተዘጋጀላቸው ደረጃ በታች ሆነው በተገኙት ላይ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ |
| | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት የደንበኞችን የላብራቶሪ የፍተሻ ውጤት መገለጽ ባለበት ጊዜና ሰዓት ማሳወቁን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፣ |
| | ሚኑስቴር መ/ቤቱ አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ በሚያዘው መሰረት የተወሰዱ ናሙናዎች ከውጫዊ ተፅኖ ነጻ ሆነው የጥራት ባህሪያቸው ሳይለወጥ ከተወሰዱበት ሰዓት ጀምሮ በ48 ሰዓት ለፍተሻ ላብራቶሪ ሊቀርቡ ይገባል፡፡ |
| | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የገቢና ወጪ ምርቶች የሀገሪቱን ህግና ደንብ ተከትለው መግባታቸውን/መለካታቸውን በማረጋገጥ ይሁንታ /Permit/ ሊሰጥ ይገባል። |
| | ሚኒስቴር መ/ቤቱ ምርትን ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገቡ አስመጪዎች አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ያላቸው ምርቶች አለም አቀፍ ተቀባይነት ባላቸው ኢንስፔክሽን አካላት የተረጋገጠ የላብራቶሪ ሰርተፊኬት ከአገልግሎት መጠየቂያ ጋር እንዲያቀርቡ ሊያደርግና የሰርተፊኬቱ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ (Rondomly) አንድ ሶስተኛ ወካይ ናሙና ወስዶ ሰርተፊኬቱን ሊያረጋግጥ ይገባል። |
| | ሚ/ር መ/ቤቱ የሦስተኛ ወገን ሰርተፊኬት ማቅረብ ግዴታ መሆኑ ከሁለት ጊዜ በላይ ተነግሯቸው ሰርተፊኬት ማቅረብ ያልቻሉ አስመጪዎች ምርታቸው የደረጃ መስፈርት ማሟላቱ የላብረቶሪ ውጤት እስከሚገለጽ ድረስ በጉምሩክ እንዲጠብቁ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | ሚኒስቴር መ/ቤቱ አስገዳጅ ደረጃ ያላቸውንና የሌላቸውን ምርቶች በመለየት ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሊያሳውቅ ይገባል፡፡ |
| ሚኒስቴር መ/ቤቱ ህጋዊ የመለኪያ መሣሪያዎች ወደ ሀገር ሲገቡ የደረጃ ፍተሻ የሚደገረግላቸው እና ስራ ላይ ሲውሉ ደረጃቸውን ጠብቀው እየሠሩ ስለመሆኑ ማረጋገጥ የሚያስችል የክትትልና የቁጥጥር ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፣ | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሀገሪቱን የስነ ልክ ሥርዓት ሊዘረጋ፣ መተግበሩን ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ |
| | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመለኪያ መሣሪያዎች የትክክለኛነት ሥራዎች በክልል ንግድ ቢሮዎችና በፌዴራል ተጠናክረው መሥራታቸውን የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | ሚኒስቴር መ/ቤቱ በክልሎች የሚካሄዱ የመለኪያ መሳሪያዎች ካሊብሬሽን በማስተባበር የማነጻጸሪያ መሣሪያዎቻቸውን ካሊብሬት እንዲያስደርጉ ሊያደርግና አፈጻጸማቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡ |
| | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመለኪያ መሣሪያዎች ወደ ገበያ ከመግባታቸው በፊት ደረጃቸውን የጠበቁ መሆኑን ሊያረጋገጥ ይገባል፡፡ |
| | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአውቶ ቦቴ የቬሪፊኬሽን የአገልግሎት ክፍያ ተመን ከሚሰጠው አገልግሎት አንጻር ሊሆን ይገባል፡፡ |

| | |
|---|---|
| | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፈሳሽ ማጓጓዣ ታንከር( ቦቴ) ይዘት የመለኪያ መሳሪያ ከተገጠመለት በኋላ የመሳሪያውን ትክክለኛነት በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ውስጥ መሆኑን በማረጋገጥ ለሶስት ዓመት የሚያገለግል የቬርፊኬሽን ሰርተፊኬት ሊሰጥና በተሰጠው መሰረት ተግባራዊ መደረጉን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ |
| | ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተገልጋዮች ቬሪፊኬሽን ለማስደረግ የክብደት ማነፃፀሪያዎች ወስደው እንዳያዘገዩ ውል አስገብቶ መሣሪያዎቹ በወቅቱ እንዲመልሱ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር እና ቀልጣፋ የሆነ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም፣ | |
| ኒስቴር መ/ቤቱ ከክልሎች፣ ከቅ/ጽ/ቤቶች፣ እና ከተገልጋዮች ጋር ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ በትብብር ለመስራት የሚያስችል የቅንጅታዊ አሰራር ስርአት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፣ | ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሌሎች አስፈጻሚ መ/ቤቶች የሚሰራባቸው አስገዳጅ ደረጃዎች በተቀናጀ መልኩ እንዲተገብሩ ሊያደርግና በአፈጻጸም ላይ የሚያወያይ መደበኛ ጉባኤ ሊጠራ ይገባል፡ |
| | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪና የገቢ ንግድ ዕቃዎች ተፈላጊውን የደረጃ መሥፈርት ሳያሟሉ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም ከሀገር እንዳይወጡ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር በትብብር ሊሠራ ይገባል፡፡ |
| | ሚኒስቴር መ/ቤቱ ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ ከሚያስገቡና ከሚያሰወጡ ተገልጋዮች የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በየ6 ወሩ ቋሚ የምክክር መድረኮች ሊያዘጋጅና ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡ |
| | ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች ባለሙያዎች ጋር በሕጋዊ ሥነ-ልክ ሥራ አፈጻጸም ዙሪያ በየሩብ ዓመቱ ውይይት ሊያደርግና በየስድስት ወሩ አንድ ጊዜ ግምገማ ሊያካሄድ ይገባል፡፡ |
| | ሚ/ር መ/ቤቱ ከላብራቶሪ ፍተሻ ውጤት ጋር በተያያዘ በሚነሱ ጉዳዮች ላይ ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር ውይትት በማድረግ መፍትሄ ሊያሰቀምጥ ይገባል፡፡ |
| ሚ/ር መ/ቤቱ ቀልጣፋ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ፣ ሪፖርት አቀራረብ እና የግብረ መልስ አሰጣጥ ሥርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ | የናሙናዎች መረጃ በጥንቃቄ በባህር መዝገብና/ loog book/ በመረጃ ቋት ተመዝግቦ ሊያዝ ይገባል። |
| | ሚ/ር መ/ቤቱ ወቅቱን የጠበቀ መረጃ በማሰባሰብ በማደራጀትና በመተንተን ለቅ/ጽ/ቤቶችና ለተገልጋዮች ሊያሰራጭ ይገባል፡፡ |

| | |
|---|---|
| | ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሁሉንም የሥራ አመራር ያካተተ— መደበኛ እና ተከታታይ የማናጅመንት /የስራ አመራር/ የውይይት መድረክ ሊኖረው እና በውይይቱ ላይ የሚነሱ ጉዳዮችን በቃለ ጉበኤ በአግባቡ ሊይዝ ይገባል፡፡ |
| | ሚ/ር መ/ቤቱ ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት ጋር መረጃ ሊለዋወጥና ወርሀዊ ወይም የሩብ አመት ሪፖርቶችን በጋራ ሊገመግም ይገባል፡፡ |
| | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቬርፊኬሽ ባለሙያ አስፈላጊውን የትክክለኛነት ማረጋገጫ ስራ አከናውኖ ሲያበቃ ለስራ ኃላፊው ሪፖርት ሊያቀርብ እና ባለሙያው የተመደበለትን ስራ በአግባቡ አከናውኖ መመለሱን የሚያረጋግጥ ክትትልና ግምገማ ሊደረግ ይገባል፡ |
| | ሚኒስቴር መ/ቤቱ በክልል የሚካሄደውን የሕጋዊ ሥነ ልክ አተገባበርና አሠራር ሊገመግምና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቅ/ጽ/ቤቶችና በክልሎች በገቢና ወጪ ዕቃዎችና በህጋዊ ስነ ልክ ቁጥጥርና ክትትል ዙሪያ በአካል በመገኘት የተከናወኑትንና በክንውን ወቅት የጋጠሙ ችግሮችን በማየትና ሊገመግምና መፍትሔ ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቅርንጫፍ ጽ//ቤቶች የሚያቀርቡትን ወርሀዊ፣ ሩብ ዓመት፣ ግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርታቸውን ከገመገመ በኋላ ግብረ መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | ሚኒስቴር መ/ቤቱ እና በሥሩ የሚገኙ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተገልጋዩች ቅሬታ ሲያቀርብ ቅሬታውን ተቀብሎ ተገቢውን ውሣኔ በ3 የሥራ ቀናት ውስጥ በመስጠት ለቅሬታ አቅራቢው ሊያሳውቅ ይገባል፡፡ |

**አባሪ 2**

**አስመጪዎች የሚያስገቧቸው ዕቃዎች አስገዳጅ የኢትዮጵያን ደረጃ ሳያሟሉ ቀርተው በሥሩ የሚገኙ በናሙና ተመርጠው በተኬደባቸው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ያገዳቸውን የወደቁ ዕቃዎች ሚኒስቴር መ/ቤቱ እና በሥሩ ያሉ ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲለቁላቸው የፈቀደበትን የሚያሳይ ሠንጠረዥ**

| ተራ ቁ. | የአስመጪው ድርጅት ስም | የገባው ዕቃ ወይም የወጣው ዕቃ | እገዳው እንዲነሳላቸው የጠየቁበት ቀን | የተፈቀደበት ቀንና የደብዳቤ ቁጥር | እንዲለቅ የተፃፈለት አካል |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ፑንት ጠቅላላ የንግድ ድርጅት እና የኮሽን ወኪል ኃ.የተ.የግል ማህበር | የገላ ሳሙና | 12/05/2006 | ግንቦት 27/2006 በቁጥር 01.1-34/1530 | ለአዳማ ቅ/ ጽ/ቤት |
| 2 | ሷሊሃ አሊ መሀመድ የህንፃ መሣሪያዎ አስመጪ | የውሃ ፓምፖች | ጥር 15/2007 | ጥር 18/2007 በቁጥር 1.1-34/4044 | በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት |
| 3 | አቶ አህመድ ከማል | ሚስማሮች | ሰኔ 30/2006 | ሰኔ 30/2006 በቁጥር 01.1/34/2195 | ለአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት |
| 4 | አቶ ፊድሉ ባለኬር | ሚስማሮች | ሰኔ 6/2006 | ሰኔ 6/2006 በቁጥር 01.1.34/2018 | ለኮሜት ተወካይ ጽ/ቤት |
| 5 | ዘካሪያስ ለቹ | ሚስማሮች | ሚያዝያ 1/2006 | ሚያዝያ 7/2006 በቁጥር 1.1.34/1269 | ለኮሜት ተወካይ ጽ/ቤት |
| 6 | ሌጋ ፍሬሰንበት አስመጪና ላኪ | ሚስማሮች | ሚያዝያ 13/2006 | ሚያዘያ 14/2006 በቁጥር 1.134/1313 | ለኮሜት ተወካይ ጽ/ቤት |
| 7 | አህመድ አብደላ | የሽንት ቤት ሳሙና | -- | መጋቢት 3/2006 በቁጥር 01.1.34/1013 | ለአስመጪው |
| 8 | የአቃቂ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ /ያተ/የግል ማህበር | ቆርቆሮ | -- | መስከረም 28/2007 በቁጥር 01.1.34/3147 | ለኮሜት ተወካይ ጽ/ቤት |
| 9 | ፋሲል ክፍለ እየሱስ ኃይሌ /አይዞን ትሬዲንግ ካምፓኒ/ | ቆርቆሮዎች | በ27/10/2006 | ሐምሌ 22/2006 በቁጥር 01.1.34/2364 | ለኮሜት ተወካይ ጽ/ቤት |
| 10 | የኢትዮጵያ የሸጠጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት | የገላ ሳሙና | ጥር 26/2006 | በ27/05/2006 | ለኮሜት ተወካይ ጽ/ቤት |
| 11 | ቃሲም ኑሪባዬ አስመጪ | Tea Buiscuts | በ7/04/2006 | በ06/04/2007 ከአንድ ዓመት በኋላ | ለኮሜት ተወካይ ጽ/ቤት |
| 12 | አፈደሆም ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር | ኃይል ቆጣቢ አምፖሎች | -- | በ05/13/2005 በቁጥር 01.1.34/4881 | ለአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት |
| 13 | ኢብራሂም መኑር /ላኪ/ | የእርግብ አተር | በ21/06/2007 በቁጥር 4/9/1/480/07 /የታገደበት ቀን/ | በ24/06/2007 በቁጥር 4/9/1/496/07 | በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ለሞያሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት |

## አባሪ 3

ቀድሞ ይሠራበት የነበረው አሠራር የላብራቶሪ ውጤት መዘግየት በሚኒስቴር መ/ቤቱ ላይ የሚያቀርቡትን ቅሬታ ለማስወገድና ምርቶቹ በጉምሩክ መጋዘን ቆይታቸውን ለማሳጠር ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው የምትር ጥራት ሰርተፊኬት የመቀበል አሠራር በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲተገበር ህዳር 02/2006 በቁጥር 011-34/0143 ቢገለጽም በናሙና ተመርጠው ለማሳያ ያህል ቀጥሎ በሠንጠረዥ ላይ አለመተግበሩ ታውቋል፡፡

| ተራ ቁ. | የአስመጪው ድርጅት ስም | የገባው ዕቃ | እንዲለቀቅ ያመለከቱበት ቀን | የተፈቀደበት ቀንና የደብዳቤ ቁጥር | እንዲለቀቅ የተፃፈለት አካል | ዕቃው በውዴታ ውዴታ ተለቆ ደረጃውን ሳያሟላ ገበያ ላይ የዋለ ግን ሚ/ር መ/ቤቱ እርምጃ ያልወሰደ መሆኑ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አመርቲ ኮፊ ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግል ማህበር፣ ሌጋ ፍሬሰንበት አስመጪና ላኪ፣ አቶ ዘካሪያስ ለቹ | ሚስማር | ግንቦት 1 ቀን 2006፣ ሚያዚያ 13/2006 እና ሚያዝያ 1/2006 | ግንቦት 1/2006 ዓ.ም በቁጥር 01-1-34/1418፣ ሚያዝያ 14/2006 ዓ.ም በቁጥር 01.1.34/1313 እና ሚያዝያ 07/2006 ዓ.ም. በቁጥር 01.1.34/1269 | ለኮሜት ተወካይ ጽ/ቤት | በውዴታ ግዴታ ገብተው የተለቀቀ |
| 2 | አህመድ አብደላ | የሽንት ቤት ሳሙና | -- | መጋቢት 3/2006 በቁጥር 01.1.34/1013 | ሚ/ር መ/ቤቱ ለኮሜት ተወካይ ጽ/ቤት መለቀቁን በግልባጭ ያሳወቀበት | በውዴታ ግዴታ ገብተው የተለቀቀ |
| 3 | ፋሲል ክፍለእየሱስ ኃይሌ /አይዞን ትሬዲንግ ካምፓኒ/ | ቆርቆሮ | በ27/10/2006 | ሐምሌ 22 ቀን 2006 በቁጥር 01.1.34/2364 | ለኮሜት ተወካይ ጽ/ቤት | በውዴታ ግዴታ ገብተው የተለቀቀ |
| 4 | የአቃቂ ጨርቃጨር ፋብሪካ ኃ.የተ.የግ.ማህበር | ጥቅል ቆርቆሮ | -- | መስከረም 28/2007 በቁጥር 01.1.34/3147 | የተለቀቀ ግን መስፈርቱን ባለማሟላቱ ዕርምጃ ያልተወሰደ ለኮሜት ተወካይ ጽ/ቤት ግልባጭ የተደረገ | |
| 5 | ጅኤል ጀነራል ትሬዲንግ | የአርማታ ብር | -- | ታህሣሥ 4/2006 በቁጥር 01.1.34/0397 | የተለቀቀ ግን መስፈርቱን ባለማሟላቱ ዕርምጃ ያልተወሰደ ለኮሜት ተወካይ ጽ/ቤት ግልባጭ የተደረገ | |
| 6 | አቶ ተክሌ ተክሉ | የአርማታ ብረት | -- | ታህሣሥ 4/2006 በቁጥር 01.1.34/0389 | የተለቀቀ ግን መስፈርቱን ባለማሟላቱ ዕርምጃ ያልተወሰደ ለኮሜት ተወካይ ጽ/ቤት ግልባጭ የተደረገ | |
| 7 | የኢትዮጵያ የሸቀጦች ድምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት | 13400 ካርቶን የገላ ሳሙና | ጥር 26/2006 | በ27/05/2006 | ለኮሜት ተወካይ ጽ/ቤት እንዲለቀቅለት የተመራ | የለቀቀ |
| 8 | ወ/ሮ ዝናሽ ሙላት ብርሃኔ /አስመጪ | የገላ ሳሙና | -- | | የደሴ ቅ/ጽ/ቤት እርምጃ እንዲወሰድ በ11/06/2006 በቁጥር ደሴ.0264/08/011/06 | ገበያ ላይ የዋለ |

| ተራ ቁ. | የአስመጪው ድርጅት ስም | የገባው ዕቃ | እንዲለቀቅ ያመለከቱበት ቀን | የተፈቀደበት ቀንና የደብዳቤ ቁጥር | እንዲለቀቅ የተፃፈለት አካል | ዕቃው በውዴታ ውዴታ ተለቆ ደረጃውን ሳያሟላ ገበያ ላይ የዋለ ግን ሚ/ር መ/ቤቱ እርምጃ ያልወሰደ መሆኑ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ለሚ/ር መ/ቤቱ ያሳወቀ መሆኑ | |
| 9 | አቶ ሙባረክ ፋሪስ ሱለይማን አስመጪ | Ballasted Compact Fluorescent Lamp | -- | -- | የደሴ ቅ/ጽ/ቤት እርምጃ እንዲወሰድ በ11/06/2006 በቁጥር ደሴ.0266/08/01/06 ለሚ/ር መ/ቤቱ ያሳወቀ መሆኑ | ገበያ ላይ የዋለ |
| 10 | አቶ እስማኤል ረዳ ሁሴን አስመጪ | የገላ ሳሙና | -- | -- | የደሴ ቅ/ጽ/ቤት እርምጃ እንዲወሰድ በ11/06/2006 በቁጥር ደሴ.02651/08/01/06 ለሚ/ር መ/ቤቱ ያሳወቀ መሆኑ | ገበያ ላይ የዋለ |
| 11 | አቶ ሽኩር ዋበላ ሁሴን አስመጪ | አምፖል | -- | -- | የደሴ ቅ/ጽ/ቤት እርምጃ እንዲወሰድ በ11/06/2006 በቁጥር ደሴ.0267/08/01/06 ለሚ/ር መ/ቤቱ ያሳወቀ መሆኑ | ገበያ ላይ የዋለ |
| 12 | አልሳህባ ኃ.የተ.የግል ማህበር | ዘኒ የልብስ ሳሙናዎች | -- | -- | ታህሣሥ 2006 በቁጥር 01.1.34/0425 | በውዴታ ግዴታ ገብተው የተለቀቀ |
| 13 | ኢስት ስቲል ኃላ.የተ.የግ.ኩባንያ | የድንጋይ ከሰል | መስከረም 24 ቀን 2006 በቁጥር 02/1/35/110 | መጋቢት 29/2006 በቁጥር 01.1.34/1207 | ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን | ለአንድ ጊዜ ብቻ እንዲያስገባ |
| 14 | አቶ ፈድሉ አብደላ ሙደሲር | Telephon Cable and Electic Cable | -- | ግንቦት 21/2006 በቁጥር 01.1.34/1520 | አቶ ፈድሉ አብደላ ሙደሲር | በውዴታ ግዴታ ተለቆ ደረጃውን ያላሟላ |
| 15 | ሷሊሃ አሊ መሀመድ የህንፃ መሣሪያ አስመጪ | 135 የውሃ ፖምፖች | የSGS ሠርተፊኬት ማቅረብ አለመቻላቸውን በጥር 15 ቀን 2007 ስለአመለከቱ | 18 ጥር/2007 በቁጥር 1.1.34/4044 | በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት | በውዴታ ግዴታ ገብተው የተለቀቀ |
| 16 | ሚፍታህ አብዶ አስመጪ | 160 የውሃ ፓምፖች | የSGS ሠርተፊኬት ማቅረብ አለመቻላቸውን በጥር 8 ቀን 2007 ስለአመለከቱ | ጥር 15/2007 በቁጥር 01-1-34/4026 | በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት | የተለቀቀላቸው |
| 17 | ፔፕሲ ኮላ ኢንተርናሽናል | የሚረንዳ ብርቱካን ጣምዕም ያለው መጠጥ | ጥቅምት 13/2007 በቁጥር PCL/204/2007 | ጥቅምት 14/2007 በቁጥር 01-1-34/3363 | በንግድ ሚ/ር ገቢና ወጪ ዕቃዎች ጥራት ቁጥጥር ለቦሌ ኤርፖርት ተወካይ ጽ/ቤት | የተለቀቀ |
| 16 | የናሽናል ቢዝነት ሴንተር | የኤሌክትሪክ ዕቃዎች | -- | ህዳር 27/2006 በቁጥር 01.1.34/0291 | ለናሽናል ቢዝነት ሴንተር | በውዴታ ግዴታ ገብተው የተለቀቀ |

**አባሪ 4**

*የንግድ ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 691/2003 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሀገሪቱን ሕጋዊ ሥነልክ ሥርዓት ይዘረጋል፤ መተግበሩን ይቆጣጠራል የሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላትን ያስተባብራል ቢልም በሚኒስቴር መ/ቤቱ የአውቶ ቦቴ ቬሪፊኬሽን ማዕከል የቬሪፊኬሽን ሰርተፊኬት ሰጥቶ በየጊዜው የቁጥጥርና የክትትል ሥራ ባለመሠራቱ ከሚ/ር መ/ቤቱ ከተሠጠ ሰርተፊኬት ውጪ በተጭበረበረ ሠርተፊኬት ሲሰሩ ቆይተው ለሶስት ወር እገዳ ተደርጐባቸው እገዳው ተነስቶ በተለዋጭ ሰርተፊኬት ሥራቸውን እንዲሠሩ የተደረጉ ነገር ግን ለፈጸሙት የማጭበርበር ወንጀል ሚኒስቴር መ/ቤቱ በህግ አግባብ እንደሚጠየቁ ቢገልጽም እርምጃ ካልተወሰደባቸው ውስጥ በናሙና ተመርጠው ከታዩት ውስጥ፡-*

| ተ. ቁ. | የሰሌዳ ቁጥር | የሻሲ ቁጥር | የቬሪፊኬሽን መለያ ቁጥር | የተሽከርካሪው ባለቤት | የተሸቀበው የነዳጅ መጠን | ንግድ ሚኒስቴር ሚ/ር እገዳው እንዲነሣለት የፃፈበት ቀን | የደብዳቤ ቁጥር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ኢ.ት 3-5295 ኢ.ት 3-17540 | WJME3TRS40 C249027 TT-0933-12 | 1617 እና VRT/07-9825 የተሳቢው 1618 እና ይእፍ/07-9826 | አቶ ልዑል በርሂ | 940 ሊትር፣ 1070 ሊትር | የካቲት 4/2007 ዓ.ም | 011-34/4198 |
| 2 | ኢ.ት 3-01175 ET ኢ.ት3-07891 ET | 072058 19T97-14645 | VRT/07-9983 VRT/07-9982 | አቶ አብርሃም ደስታ | 1890 ሊትር፣ 1272 ሊትር | የካቲት 16/2007 | ቁ011-34/24296 |
| 3 | ኢ.ት3-35525/108 65 ET | WJME3TRS30 C182288/TST-3A-0027-07 | 1724 እና VRT/07-9945 | አባይነህ ተመስገን እና ኤዜድ /ያተ/የግ/ማ/ | 1734 ሊትር | የካቲት 17/2007 | 01-01-34/4307 |
| 4 | ኢ.ት3-07024 ET | WJME3TPT00C 059911 | 0891 እና VRT/07-9920 | ወ/ሮ ሶስና አሰፋ | | የካቲት 09/2007 | ቁ.011-34/4235 |
| 5 | ኢ.ት3-22864 ET ኢ.ት3-08892 ET | WJMAIVPU00C 126057 RM26CF17.67. 5228758 | 1670 እና VRT/07-9887 1671 እና VRT/07-9888 | አቶ አየለ የሸንበል | 2634 ሊትር፣ 3397 ሊትር | የካቲት 09/2007 | ቁ.011-34/4236 |
| 6 | ኢ.ት3-07017 ET ኢ.ት3-04066 ET | WJME3TPT00C 059788 TT-0101-99 | 1032 እና VRT/07-9863 1033 እና VRT/07-9864 | አቶ ግርማ ሙሴ | 3910 ሊትር፣ 4365 ሊትር | የካቲት 09/2007 | ቁ.011-34/4234 |
| 7 | ኢ.ት3-34958 ET ኢ.ት3-11568 ET | WJME3TRS30 C178607 MMI/TFT/0069A | 0868 እና VRT/07-9852 0869 እና VRT/07-9862 | አቶ ዓለሙ ለእሜንጐ | 2904 ሊትር | የካቲት 09/2 | ቁ.011-34/4233 |
| 8 | ኢ.ት3-33129 ET | WJME3TPR006 155168 | 1631 እና VRT/07-9842 | አቶ ቴዎድሮስ ተስፋዬ | 830 ሊትር | የካቲት 05/2007007 | ቁ.011-34/4211 |
| 9 | ኢ.ት3-00010 ET | TT-0384-02 | 1632 እና VRT/07-9843 | ወ/ሮ የሽእመቤት ገ/ሃና | 820 ሊትር | የካቲት 05/2007007 | ቁ.011-34/4212 |